# በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

የሕንፃ መመሪያ

መመሪያ ቁጥር 5/2003

ግንቦት 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

## ማ ው ጫ ገጽ


| | | |
|---|---|---|
| | የሕንፃ መመሪያ | 1 |
| | ክፍል አንድ ጠቅላላ | 1 |
| 1. | አጭር ርእስ | 1 |
| 2. | ትርጓሜ | 1 |
| 3. | የተፈፃሚነት ወሰን | 4 |
| | ክፍል ሁለት አስተዳደር | 5 |
| 4. | ማመልከቻና ፕላን ስለማቅረብ | 5 |
| 5. | የፕላን ስምምነት | 7 |
| 6. | የፕላን መገምገሚያ ጊዜ | 7 |
| 7. | ፕላን ስለማፀደቅ | 8 |
| 8. | ፕላን ውድቅ ስለማድረግ | 9 |
| 9. | በግንባታ ወቅት ፕላንን ስለማሻሻል | 9 |
| 10. | የግንባታ ፈቃድ | 9 |
| 11. | የግንባታ ፈቃድ ስለመጠየቅ | 10 |
| 12. | የሕንፃ ሹም | 15 |
| 13. | አገልግሎት መግዛት | 16 |
| 14. | የይግባኝ ሰሚ ቦርድ | 16 |
| 15. | ትዕዛዝ አለማክበር | 19 |
| 16. | ስለማስታወቂያ | 19 |
| 17. | ስለ ተቆጣጣሪዎች | 20 |
| 18. | ቁሳቁስ | 21 |
| 19. | የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ | 21 |
| 24. | የአገልግሎት ለውጥ ስለማድረግ፣ ስለማስፋፋት፣ እድሳት ወይም ጥገና ስለማድረግ እና ስለማፍረስ | 26 |
| 25. | የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠር | 27 |
| 26. | የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮች ስለመቅጠር | 28 |
| | ክፍል ሶስት፡ የመሬት አጠቃቀም፣ ተጓዳኝ ጥናቶች እና ዲዛይኖች | 29 |
| 27. | የመሬት አጠቃቀም እና ተጓዳኝ ጥናቶች | 29 |
| 29. | አርክቴክቸር ወይም ሥነ ሕንፃ | 36 |
| 30. | ስትራክቸር/ውቅር | 40 |
| 31. | ሳኒተሪ | 41 |
| 32. | ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ | 41 |
| 33. | ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ ዝግጅቶች | 42 |
| | ክፍል አራት በህንፃ ግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚኖርባቸው የደህንነት ጥንቃቄዎች | 44 |
| 34. | በግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች | 44 |
| 35. | መወጣጫዎች እና መሰላሎች | 46 |
| 36. | የማፍረስ ሥራ | 48 |
| 37. | ስለ ከፍታ እና የጣሪያ ላይ ሥራዎች | 49 |
| 38. | የመሬት ውስጥ ሥራዎች | 50 |
| 39. | ስለ ኬሚካሎች፣ ፈንጂዎች እና መርዛማ ቁሳቁሶች | 53 |
| 40. | ስለ አልባሳት | 54 |
| 41. | የእሣት አደጋ ስለ መከላከል | 54 |
| 42. | ስለ የመጀመሪያ እርዳታ አሠጣጥ | 56 |
| 43. | ስለ አደጋ ማምለጫ መንገዶች | 56 |
| 44. | ስለ ሠራተኞች እና የሥራ ቦታዎች ደህንነት አጠባበቅ | 57 |
| 45. | የሚደርሱ አደጋዎችን ስለ መመዝገብ እና ማሳወቅ | 58 |
| | አምስት | 58 |
| | የውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን | 58 |
| 46. | የውሃ አቅርቦት | 58 |
| 47. | የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ | 59 |
| 48. | የጎርፍ ውሀ ወይም የዝናብ ውሃ አወጋገድ | 60 |
| 49. | የኢንዱስትሪ ዝቃጭ | 61 |
| 50. | የውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ | 61 |
| 51. | የእሳት ማጥፊያ ተከላ | 61 |
| 52. | የእሣት መከላከል የውሃ አቅርቦት | 62 |
| 53. | የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር | 62 |
| 54. | መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ | 62 |

# የሕንፃ መመሪያ

በአገራችን  በመካሄድ ላይ ያለውን የሕንፃ ግንባታ ሥርዓት ባለው እና ደረጃውን በጠበቀ መንገድ እንዲመራ ለማድረግ፣ የሕዝብን ጤንነትና ደህንነት ለማረጋገጥ፣ እና  በመላ ሀገሪቱ ተፈጻሚነት የሚኖረው ምቹ የግንባታ ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ እንዲሁም የሕንፃ ግንባታን ዝርዝር አፈጻጸምና የአሰራር ሂደቶችን ለአገልግሎት ሰጪውም ሆነ ለተገልጋዩ ግልጽ በማድረግ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ አሠራር በመዘርጋት የሕንፃ  አዋጁን እና ደንቡን ማስፈፀም የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን  ሚኒስቴር  በህንፃ ደንብ ቁጥር  243/2003 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን  መመሪያ አውጥቷል ፡፡

## ክፍል አንድ ጠቅላላ

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ መመሪያ "የህንጻ መመሪያ ቁጥር 5/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ፍቺ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

   2.1 **"ሚኒስቴር"** ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ማለት  ነው፣

   2.2 **"ሕንፃ"**  ማለት ለመኖሪያ፣ ለቢሮ፣ ለፋብሪካ ወይም ለማንኛውም ሌላ አገልግሎት የሚውል  ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ግንባታ ማለትታ ነው፣

   2.3 **"የሕንፃ ሹም"** ማለት የሕንፃ አዋጁን፣ የማስፈፀሚያ ደንቡንና ይህንን መመሪያ እእንዲያስፈጽም በከተማ አስተዳደር ወይም በተሰየመ አካል የተሾመ ሰው ማለት ነው፣

   2.4 **"የተመዘገበ ባለሙያ"** ማለት ሥልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ በዲዛይን ወይም በኮንስትራክሽን የባለሙያነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት ማለት ነው፣

   2.5 **"የተመዘገበ ሥራ ተቋራጭ"** ማለት ሥልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ የሥራ ተቋራጭነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ድርጅት ማለት ነው፣

   2.6 "ምድብ "ሀ" ሕንፃ" ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት 7 ሜትር ወይም ከዚያ በታች የሆነ ባለአንድ ፎቅ ሕንፃ ወይም ማንኛውም ከሁለት ፎቅ በታች የሆነ የግል መኖሪያ ቤት ማለት ነው፣

   2.7 "ምድብ "ለ" ሕንፃ" ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት ከ7 ሜትር በላይ የሆነ ወይም ከመሬት ወለል በላይ ባለሁለት ፎቅና ከሁለት ፎቅ በላይ የሆነና በምድብ "ሐ" የማይሸፈን ሕንፃ ወይም በምድብ "ሀ" የተመደበ እንደ ሪል ስቴት ያለ የቤቶች ልማት ማለት ነው፣

2.8 "**ምድብ "ሐ" ሕንፃ**" ማለት የሕዝብ መገልገያ ወይም ተቋም ነክ ሕንፃ፣ የፋብሪካ ወይም የወርክሾኘ ሕንፃ ወይም ከመሬት እስከ መጨረሻው ወለል ከፍታው ከ12 ሜትር በላይ የሆነ ማናቸውም ሕንፃ ማለት ነው፣

2.9 "**ግንባታ**" ማለት አዲስ ሕንፃ መገንባት ወይም ነባር ሕንፃን ማሻሻል ወይም አገልግሎቱን መለወጥ ማለት ነው፣

2.10 #**ጊዜያዊ ግንባታ**; ማለት የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት የሚገነባ እና የተሰጠው የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ የሚነሳ የሕንፃ ግንባታ ማለት ነው፣

2.11 #**ኮንትራታዊ ጊዜያዊ ግንባታ**; ማለት በጊዜያዊ ይዞታ ላይ የይዞታው ዘመን እስከሚያበቃ ድረስ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚገነባ ጊዜያዊ ግንባታ ማለት ነው፣

2.12 #**ወቅታዊ ጊዜያዊ ግንባታ**; ማለት በተለያዩ ማህበራዊ፣ የበዓል እና ልዩ ልዩ ዝግጅቶች በከተማው ባሉ ክፍት ቦታዎችና መንገዶች ላይ የሚተከሉ ተነቃቃይ መጠለያዎችን ለማቆም የሚጠየቅ ጊዜያዊ ግንባታ ማለት ነው፣

2.13 #**ተጓዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ**# ማለት በይዞታ ላይ ከህጋዊ ግንባታ ጋር ተያይዞ የሚገነባ እና ግንባታው እንደተጠናቀቀ የሚነሳ ወይም የሚፈርስ የመጠለያ ግንባታ ማለት ነው፣

2.14 "**አስጊ ሕንፃ**" ማለት ግንባታው አስተማማኝ ያልሆነ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ለእሳት አደጋ የተጋለጠ ወይም ለጤና ጠንቅ የሆነ ሕንፃ ማለት ነው፣

2.15 "**የተሰየመ አካል**" ማለት አዋጁን" የማስፈፀሚያ ደንቡንና ይህንን መመሪያ እንዲያስፈጽም በየክልሉ ፣በአዲስ አበባና ድሬዳዋ አስተዳደር የሚሰየም አካል ማለት ነው፣

2.16 "**ሰነድ**" ማለት ከሕንፃ ዲዛይንና ግንባታ ጋር በተያያዘ የሚያስፈልግ ወይም የተዘጋጀ ኘላን፣ ሪፖርት፣ የዋጋ ግምት ወይም ማንኛውም የቴክኒክ እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚያስረዳ ማለት ነው፣

2.17 "**የግል መኖሪያ ሕንፃ**" ማለት ለአንድ ቤተሰብ መኖሪያነት የሚያገለግል አንድ ወይም ከአንድ በላይ ክፍሎች፣ የመፀዳጃና የማብሰያ አገልግሎቶች ያሉት ሆኖ በመኖሪያው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ የመኪና ማቆሚያንና ለመኖሪያነት የሚውሉ ከዋናው ቤት የተነጠሉ ክፍሎችን ሊጨምር ይችላል፣

2.18 "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፣

2.19 "**ኘላን**" ማለት የአንድ ሕንፃን መጠን፣ ዓይነትና፣ ስፋት እንዲሁም ሕንፃው የሚሠራበትን ቁሳቁስና የአገነባብ ዘዴን የሚያሳይ ንድፍ ወይም ሞዴል ሲሆን የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒታሪ፣ የኤሌክትሪካል፣ የሜካኒካል፣ የእሳት መከላከልና የሌሎች ሥራዎችን ንድፍ ሊያካትት ይችላል፣

2.20 "**ክልል**" ማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፣

2.21 "**የማስቆሚያ ትዕዛዝ**" ማለት በአንድ የሕንፃ ግንባታ ቦታ የሚካሄድ ሥራ እንዲቋረጥ ወይም እንዲቆም በሕንፃ ሹም የሚሰጥ ትዕዛዝ ማለት ነው፣

2.22 "ፎቅ" ማለት በሁለት ወለሎች መካከል ወይም ከላይ ሌላ ወለል ከሌለ በወለሉና በኰርኒስ መሃል ያለው የሕንፃ ክፍል ማለት ነው፣

2.23 "የከተማ አስተዳደር" ማለት በሕግ ወይም በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ውክልና የከተማ አስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል ማለት ነው፣

2.24 "ከተማ" ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም 2000 ወይም ከዚያ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 50% የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ማለት ነው፣

2.25 "የሕንፃ ተቆጣጣሪ" ማለት በሕንፃ ሹሙ ሥር በመሆን በከተማው መስተዳደር ክልል የሚካሄዱ ግንባታዎችን ሕጋዊነትና የተሰጠውን ፈቃድ በሚመለከት በቅርብ የሚቆጣጠር ባለሙያ ማለት ነው፣

2.26 "የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ" ማለት ከግል መኖሪያ ህንፃ ውጪ የሆነ እና በርካታ ተጠቃሚዎችን የሚስብ የቲያትር ቤት፣ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት፣ የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ ሰዎች ለአምልኮ የሚሰበሰቡበት፣ የሕዝብ መዝናኛና የትምህርት ቤት፣ የከፍተኛ ትምህርት ማዕከል፣ የህክምና አገልግሎት መስጫ፣ የገበያ ማእከል፣ እንደ ፋብሪካ ያሉ የማምረቻ ተቋማትና ተመሳሳይ ሕንፃ ማለት ነው፣

2.27 "ትንታኔ" ማለት ኘላን ለማዘጋጀት የሚሰራ ስሌት ወይንም ኘላንን ለመደገፍ የሚዘጋጅ ማብራሪያ ማለት ነው፣

2.28 "የኘላን መረጃ" ማለት በአንድ ቦታ ሊገነቡ የሚችሉ ወይንም ለቦታው የተፈቀዱ የአገልግሎት አይነቶችን፣ ለቦታው የተፈቀደ የህንፃ ከፍታን፣ በቦታው አካባቢ የሚያልፉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን፣ነባራዊ እና የታቀዱ መጠኖችን ወይንም ስፋቶች፣ ወዘተ የሚያሳይ መረጃ ማለት ነው፣

2.29 "የኘላን ስምምነት" ማለት ለህንፃ ግንባታ የቀረበ እቅድ ከከተማው ኘላን ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ስምምነት ማለት ነው፣

2.30 "ምዝገባ" ማለት የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ለቀረበ ኘላን የሚደረግ ምዝገባ ማለት ነው፣

2.31 "የምዝገባ ቁጥር" ማለት ለተፈቀደ ፐላን የሚሰጥ ምዝገባ ቁጥር ማለት ነው፣

2.32 "የኘላን ማሻሻያ" ማለት በነባሩ ኘላን ለህንፃው ምድብ የተጠየቁ ኘላኖችን ትንታኔ ሙሉ ለሙሉ መከለስ ሳያስፈልግ የሚደረግ ማስፋፊያ ወይንም ማሻሻያ ማለት ነው፣

2.33 "የሥራ እርከን" ማለት የግንባታ ሥራዎች ከመጀመራቸው በፊት ለህንፃ ሹሙ ማስታወቂያ የሚቀርብባቸው የህንፃ ግንባታ ሥራ ደረጃዎች ናቸው፣

2.34 "ሪል እስቴት" ማለት ለሽያጭ፣ ለኪራይ ወይም ለሊዝ አገልግሎት እንዲውል የተገነባ ህንፃ ማለት ነው፣

2.35 "የአገልግሎት ለውጥ" ማለት አንድ ሕንፃ ያለውን ነባር አገልግሎት በሌላ ዓይነት አገልግሎት መለወጥ ማለት ነው፣

2.36 "**የግንባታ ፈቃድ**" ማለት አንድ የሕንፃ ግንባታ ለማካሄድ ለሚፈልግ አካል ሕንፃውን ለመገንባት የሚያስችሉትን ዝርዝር መስፈርቶች እንደተሟሉ በከተማው ሹም ተረጋግጦ ግንባታ እንዲያካሄድ ፈቃድ መሰጠቱን የሚገልፅ ማስረጃ ማለት ነው፣

2.37 "**የቆጥ ወለል** (Mezanin)" ማለት በአንድ ወለል ከፍታ ውስጥ ያለና የወለሉን 40 በመቶ የማይበልጥ ስፋት ያለው ወለል ማለት ነው፣

2.38 "**መሰረታዊ ግንባታ**" ማለት የአንድ ግንባታ ሙሉ መዋቅር፤ የውስጥና የውጭ ግድግዳ ሥራ፤ የውጭ በርና መስኮት ሥራ እና የጣሪያ ልባስ ሥራ ሲጠናቀቅ ማለት ነው፣

2.39 "**ማስታወቂያ**" ማለት በህንፃ ዲዛይን እና ግንባታ ወቅት የከተማው አስተዳደር፣ የተሠየመ አካል ወይም የሕንፃ ሹም ለሕንፃው ባለቤት ወይም የሕንፃው ባለቤት ለተጠቀሱት አካላት የሚያቀርበው የጥያቄ ትዕዛዝ፣ የመረጃ የማስጠንቀቂያ ሠነድ ማለት ነው፡፡

2.40 "**ገንቢ**" ማለት ግንባታ ለማከናወን ፈቃድ የወሰደ ግለሰብ ወይም የሥራ ተቋራጭ ማለት ነው፣

2.41 "**አዋጅ**" ማለት የኢትዮጵያ ሕንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ማለት ነው፣

2.42 "**ደንብ**" ማለት የሕንፃ አዋጅን ለማስፈፀም የወጣ ደንብ ቁጥር 243/2003 ማለት ነው፣

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

3.1 ይህ መመሪያ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፣

3.1.1 በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ቆጠራ ከ10ሺ.ህ ህዝብ በላይ ነዋሪ ባለባቸው ከተሞች፣

3.1.2 የነዋሪዎቻቸው ቁጥር ከ10ሺ.ህ በታች በሆኑና ተፈፃሚ እንዲሆንባቸው በሚመለከተው ክልል በሚወሰኑ ከተሞች፣

3.1.3 ከከተማ ውጪ በሚገኙ ህዝብ የሚገለገልባቸው ሕንፃዎች፣የኢንዱስትሪ ወይም የዘመናዊ እርሻ ተቋሞችና ሪል ስቴቶች፣

3.2 ይህ መመሪያ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፣

3.2.1 አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በተጠናቀቀ ሕንፃ፣

3.2.2 አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በተሰጠ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ በመካሄድ ላይ በሚገኝ በማንኛውም ሕንፃ፣

3.2.3 ከሀገር ደህንነት ጋር በተያያዘ የሕንፃ አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆንበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወሰን ሕንፃ፣

3.3 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.2(3.2.2) ድንጋጌ ቢኖርም፣

3.3.1 አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በወጣ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ መሠረት በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሆኖ ግንባታው አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተጠናቀቀ ከሆነ፣

3.3.2 አዋጁ ከመፅናቱ በፊት የተጠናቀቀ እና አዋጁ ከፀና በኋላ የአገልግሎት ለውጥ፣ የማስፋፋት ወይንም የማፍረስ ጥያቄ በሚቀርብበት ህንፃ ላይ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ተፈፃሚ እንዲሆንበት ማድረግ ይችላል።

## ክፍል ሁለት አስተዳደር

### 4. ማመልከቻና ኘላን ስለማቅረብ

4.1 ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው በቅድሚያ የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፣

4.2 ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው አገልግሎት ለማግኘት ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል የግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ 001 በመሙላት እና የፕሮጀክቱን ኘላን በማያያዝ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፣

4.3 የግንባታ ኘላን በሚቀርብበት ወቅት መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች የግንባታ ፈቃድ አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ የማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ በግልፅ መዘርዘር አለባቸው፣

4.4 ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ኘላኖች እና ማስረጃዎች፤

4.4.1 ለሁሉም የህንጻ ምድቦች ተቀባይነት ያለው የይዞታ ባለመብትነት ማስረጃ፣

4.4.2 ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የሕንፃ ግንባታ የሚካሄድበትን ቦታ የሚያሳይ ከከተማው ኘላን ላይ የተወሠደ አካባቢውን የሚያሳይ ኘላን ቅጂ፣

4.4.3 የኮንክሪት ጣሪያ ለሌላቸው የምድብ “ሀ“ ህንፃዎች የአርክቴክቸር እና የኤሌክትሪክ ፕላኖች፣

4.4.4 የኮንክሪት ጣሪያ ላላቸው የምድብ “ሀ“ ህንፃዎች የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር እና የኤሌክትሪክ ፕላኖች፣

4.4.5 ለሕንፃ ምድብ “ለ” የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪክ ፕላኖች እና የአፈር ምርመራ ሪፖርት፤

4.4.6 ለሕንፃ ምድብ “ሐ” የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪክ፣ የእሳት አደጋ መከላከያ ፕላን፣ ትንታኔ እና ሪፖርት እና ሁለትና ከሁለት ወለል በላይ ከፍታ ላላቸው የአፈር ምርመራ ሪፖርት፣

4.4.7 አሳንሰር እና ለአየር ዝውውር ሰው ሰራሽ አማራጮችን የሚጠቀሙ ህንፃዎች የኤሌክትሮ መካኒካል ፕላኖች እና ትንታኔዎች፣

4.4.8 በአዋሳኝ ባሉ ሥፍራዎች የሚገኙ ዋና መንገዶችና የታወቁ ቦታዎችን ሥም የሚገልጹ መረጃዎች፣

4.4.9 በአዋሳኝ ቦታዎች የሚገኙ ግንባታዎች ከመሬት በላይ እና በታች ያላቸው የወለል ብዛት ፣ ከጋራ ወሰን ያላቸው ርቀት እና ከምድር ወለል በታች ያላቸው ጥልቀት ፣

4.4.10 ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የህንጻውን ጠቅላላ የወለል ስፋት የሚገልጽ ሰንጠረዥ፣

4.4.11 የአማካሪ ግዴታ መግቢያ ቅጽ 010 በአማካሪ ወይም ዲዛይኑን ባዘጋጀው ባለሙያ የተፈረመ

4.4.12 ለሁሉም የህንፃ ምድቦች የህንፃውን ፕላን ያዘጋጁ ባለሙያዎች የምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ ናቸው።

4.5 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 4.4 (4.4.9) ላይ የተገለፀው የአዋሳኝ ቦታዎች መረጃ በከተማው አስተዳደር በሚዘጋጅ የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ ቅፅ 008. አጐራባቹን በማስሞላት የሚቀርብ ይሆናል፤

4.6 የግንባታ ፈቃድ በተጠየቀበት ይዞታ የሚገኝ የአጐራባች ባለይዞታ ይዞታውን በሚመለከት የሚቀርብለትን ቅጽ መሙላት ይኖርበታል፤

4.7 የሚቀርቡ ፕላኖች መዘጋጀት የሚኖርባቸው በዲዛይን ባለሙያዎች እና አማካሪዎች ምዝገባ መመሪያ መሠረት የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚያሟሉና እና ባለሙያዎችን ለመመዝገብና ለመፍቀድ ሥልጣን በተሰጠው አካል በተመዘገቡ ባለሙያዎች መሆን ይኖርባቸዋል።

4.8 የኘላን አቀራረብ፤

4.8.1 ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርብ ዲዛይንና ተዛማጅ ሠነድ በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ ወይም በክልሉ የሥራ ቋንቋ የተፃፈ መሆን አለበት፣

4.8.2 የፕላን መለኪያዎች በሜትሪክ ሲስተም እና በግራፊክስ ስታንዳርድ የልኬት አፃፃፍ መቅረብ አለባቸው፣

4.8.3 የሚቀርቡ ዲዛይኖች በ 4 ቅጂ ሆነው እንደአስፈላጊነቱ ቢያንስ በ $A_3$ መጠን እና ቢበዛ በ$A_1$ መጠን የተዘጋጁ ሆነው በፕላን ኮፒ (Blue print) ወይም በባለ 80 ግራም ነጭ ወረቀት ንድፍ መሆን ይኖርበታል፣

4.8.4 የጽሑፉ ሰነድ በ$A_4$ መጠን መሆን አለበት፤ ለምድብ "ለ" እና "ሐ" የኤሌክትሮኒክስ ኮፒ በተጨማሪነት እንዲቀርብለት የሕንፃ ሹሙ ሊጠይቅ ይችላል፣

4.8.5 በኘላን ወይም በንድፍ መገለጽ ያልቻሉ ዝርዝር መግለጫዎች በኘላኑ ላይ በጽሑፍ መመልከት ይኖርባቸዋል፣

4.8.6 ለሁሉም ሕንፃዎች የወለሉ ከፍተኛ የጎን ስፋት ከ30 ሜትር የማይበልጥ ከሆነ ፕላኖቹ በ1፡50 ሚዛን እንዲሁም የሳይት ኘላኖቹ በ1፡200 ሚዛን እንዲሁም የወለሉ ከፍተኛ የጎን ስፋት ከ30 ሜትር በላይ ከሆነ ፕላኖቹ በ1፡100 ሚዛን እንዲሁም የሳይት ኘላኖቹ በ1፡500 ሚዛን መዘጋጀት ይኖርበታል፣

4.8.7 ዝርዝር ፕላን (Detail Plan) ለሚዘጋጅላቸው ንድፎች በ1፡10፣ 1፡20፣ ወይም 1፡25 ሚዛን ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል፣

4.8.8 ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርቡ ኘላኖች ዝርዝር የኘላን ምድቡ የሚጠይቀውን በማሟላት መለኪያቸው በሜትሪክ ሲስተም ወጥ ሆኖ መገለጽ ይኖርበታል፣

## 5. የኘላን ስምምነት

5.1 አዲስ፣ ተጨማሪ ወይም የማሻሻያ ግንባታ ለማከናወን የሚፈልግ ሰው የህንፃውን ዲዛይን ከማዘጋጀቱ በፊት የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፣

5.2 የፕላን ስምምነት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በቅጽ 003 መሠረት ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፣

5.3 በማመልከቻ ቅጹ ላይ ተሞልቶ የሚቀርብ ጥያቄ ለአዲስ ግንባታ የሚጠየቅ ስምምነት ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ቅጂ፣ ለነባር ግንባታ ማሻሻያ ከሆነ፤

5.3.1 የይዞታ ማረጋገጫ ቅጂ፣

5.3.2 የነባሩ ሕንፃ ፕላን ቅጂ፣

5.3.3 የነባሩን ሕንፃ አቀማመጥ የሚያመለክት ሳይት ፕላን /የምድረ ግቢ ኘላን/ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

5.4 የከተማ ፕላን ለተዘጋጀላቸው ከተሞች የፕላን ስምምነቱ በከተማው መሪ ፕላን ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣

5.5 የፕላን ስምምነቱ በሚመለከተው ሃላፊ ተፈርሞ እና በመ/ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ለጠያቂው አካል መሰጠት ይኖርበታል፣

5.6 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5.5 በተመለከተው መሠረት የተሰጠ የፕላን ስምምነት ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ለ12 ወራት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

## 6. የኘላን መገምገሚያ ጊዜ

6.1 ማናኛውም ለግንባታ ሥራ የተዘጋጁ ኘላኖች ለየሕንጻ ምድቡ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ መገምገም አለባቸው፣

6.2 ለአንድ የሕንጻ ዓይነት የተዘጋጁ ፕላኖችን ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜ፤

6.2.1 ከሪልስቴት ውጪ ላለ በምድብ “ሀ” ስር ለሚካተት ሕንፃ የኘላኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከ15 የሥራ ቀናት፣

6.2.2 በምድብ “ለ” ስር ለሚካተት ሕንፃ የኘላኖች መገምገሚያ ጊዜ ከ7 የሥራ ቀናት፣

6.2.3 በምድብ “ሐ” ስር ለሚካተት ሕንፃ እና በምድብ “ለ” ውስጥ ለሚካተቱ የሪል ኤስቴት ህንጻዎች ኘላኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከ21 የሥራ ቀናት የበለጠ መሆን የለበትም፡፡

6.3 ከፕሮጀክቱ ስፋት ወይም ውስብስብነት የተነሳ ተጨማሪ ጊዜ ለሚሹ ስራዎች የህንጻ ሹሙ ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለተሰየመው አካል ለፕላን ግምገማ ተጨማሪ ጊዜ ቅጽ 24 በመሙላት መጠየቅ ይኖርበታል ፡፡

6.4 ለግምገማ የሚቀርብ ዲዛይን መሻሻል የሚስፈልገው ከሆነ መሻሻል ያለበትን በማመልከት ለአመልካቹ በደብዳቤ መገለጽ ይኖርበታል ፡፡

## 7. ኘላን ስለማፀደቅ

7.1 የሕንፃ ሹሙ ከላይ ንዑስ አንቀጽ 6.2 ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት የቀረበውን የኘሮጀክቱን ዲዛይንና ሰነድ ከመሪ ኘላኑ እና ከዲዛይን ስታንዳርድ መስፈርቶች ጋር በማገናዘብና በመመርመር የተሟላ ሆኖ ሲያገኝ በግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጽ 002 ላይ የግንባታ ፈቃድ ውሳኔ ሥር የሚገኙትን መረጃዎች ሞልቶ ያፀድቃል ፡፡ የፀደቁትን ሰነዶች በአንደኛው ኮፒ ላይ "ተፈቅዷል" የሚል ማህተም፤ በሁለተኛው ኮፒ ላይ "ለክትትል ብቻ " የሚል ማህተም ተደርጎባቸው ለአመልካቹ ይሰጣሉ፣ ሦስተኛው ኮፒ ከፋይል ጋር ይያያዛል፣

7.2 ከላይ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 7.1 በተመለከተው መሠረት የፀደቀ ፕላን የምዝገባ ቁጥር እና የፀደቀበትን ቀን የያዘና የሕንፃ ሹሙ ፊርማ እና ማሕተም ያረፈበት መሆን ይኖርበታል፣

7.3 የግንባታ ፈቃድ የማያስከለክሉና እርማት ተደርጎባቸው የሚታለፉ ግድፈቶች፤

7.3.1 በስትራክቸር ዲዛይን ላይ ለውጥ የማያመጡ እና የተዘነጉ ንድፎች፣

7.3.2 በግንባታ ሂደት ላይ ተጽዕኖ የማይፈጥሩ የተዘነጉ ልኬቶች ማስተካከያ የተደረገባቸው፣

7.3.3 የክፍሎችን ስፋትና አጠቃቀም ለማሳየት የሚቀመጡ የመጠቀሚያ ቁሳቁስ ንድፎች ናቸው፡፡

7.4 ደረጃ በደረጃ ወይም በየምዕራፉ ለመገንባት የቀረበ ፕላን፤

7.4.1 የመጀመሪያው የግንባታ ደረጃ ከመሪ ኘላኑ ዝቅተኛ የሕንፃ ከፍታ ሳያንስ የግንባታ ፈቃዱ ሊሰጥ ወይም ሊፀድቅ ይችላል፣

7.4.2 ለክትትልና ለመጠቀሚያ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ ያመች ዘንድ በግንባታ ፈቃድ ሰነድ ላይ ደረጃ በረጃ ለመገንባት የታቀደው በግልፅ ተለይቶ በሚፈቀደው ፕላን ላይ መመልከት ይኖርበታል፣

7.5 የተወሰነ ማሻሻያ የሚያስፈለግ ከሆነ በተቀመጠው የጊዜ ስታንዳርድ ገደብ ውስጥ በህንፃ ሹሙ በተፈረመ ደብዳቤ መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች ተዘርዝረው ለአመልካቹ ይገለፅለታል፡፡

## 8. ፕላን ውድቅ ስለማድረግ

8.1 ከህንፃ አዋጁ፣ ከማስፈፀሚያ ደንቡና ከዚህ መመሪያ ጋር የማይጣጣም የግንባታ ፕላን በህንፃ ሹሙ ውድቅ ይደረጋል፣

8.2 ለምርመራ የቀረበው ዲዛይን የግንባታ ፈቃድ መስፈርት የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ ፈቃዱ የተከለከለበትን ምክንያት ዝርዝር በግንባታ ፈቃዱ መጠየቂያ ቅጽ ላይ ተሞልቶና "አልተፈቀደም" የሚል ማህተም ተደርጐበት ለባለጉዳዩ ተመላሽ ይደረጋል፣

## 9. በግንባታ ወቅት ፕላንን ስለማሻሻል

በግንባታ ወቅት የዲዛይን ማሻሻያ ስራ ሲያስፈልግ የፕላን ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ 22 በመሙላት የተሻሻለውን ፕላን ግንባታ ከመካሄዱ በፊት ጥያቄውን ለህንጻ ሹሙ በማቅረብ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የሚከተሉት በህንጻ ሹሙ መጽደቅ ሳያስፈልጋቸው የግንባታ ሥራ ለውጥ ማሳወቂያ ቅጽ 17 በመሙላት እና በማሳወቅ መሻሻል የሚችሉ የፕላን አካላትና ዲዛይኖች፤

9.1 በፕላን ላይ የሰፈሩ የልኬት ጉድለት ወይም ስህተት፣

9.2 የውስጥ ማከፋፈያ ግድግዳ የተጨማሪ ጭነት በማይፈጥር ቁሳቁስ መለወጥ፣

9.3 የኤሌትሪክ ነጥቦች ሳይቀየሩ የሚደረግ የኤሌክትሪክ መስመር አቅጣጫ ለውጥ ስራ፣

9.4 የክፍል ውስጥ ማሥጌጥ ሥራ፣

9.5 በፕላን ላይ በከፊል ወይም በጥቅል የተገለፀና ዝርዝር መስፈርታቸው ወይም መለኪያቸው ያልተካተተ ስታንዳርድ ያላቸው የፋብሪካ ውጤቶች፣

9.6 በንድፍ ላይ በግንባታ ወቅት በመሐንዲሱ እንደሚወሰኑ የተገለጹ ሌሎች ስራዎች፣

9.7 የውስጥ ክፍሎች የወለል ንጣፍ ሥራ፣ከሕዝብ መገልገያ ውጪ ለሆኑ ሕንጻዎች ፣

9.8 የጣራ ልባስ፣ የኮርኒስ፣ የአሸንዳና ጎረንዳዮ ቁሳቁስ ለውጥ፣

9.9 የግቢ ማስዋብ ሥራ ናቸው፡፡

## 10. የግንባታ ፈቃድ

10.1 የፀደቀ ፕላን እንደ ግንባታ ፈቃድ ያገለግላል፣

10.2 የግንባታ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የግንባታ ሥራዎች፤

10.2.1 አዲስ የግንባታ ሥራ፣

10.2.2 ከውስጥ የቀለም ቅብ እና የማጠናቀቂያ ሥራዎች ውጪ ያሉ የጥገና እና የእድሳት ስራዎች

10.2.3 ግንባታ የማስፋፋት እና የማሻሻል ሥራ፣

10.2.4 ግንባታ የማፍረስ ሥራ፣

10.2.5 የሕንፃ አገልግሎት ለውጥ፣

10.2.6 የጊዜያዊ ግንባታ ናቸው፡፡

10.3 የግንባታ ፈቃድ ወጪ ሆኖ የሚሰጠው ለአመልካች ወይም ለህጋዊ ወኪል ብቻ ነው፣

10.4 አንድ የግንባታ ፈቃድ እንዲያገለግል በተሰጠበት የጊዜ ገደብ ውስጥ መሠረታዊ የግንባታ ሥራ ካልተጠናቀቀ የግንባታ ጊዜ ማራዘሚያ ቅጽ 23 በመሙላት ጥያቄ ማቅረብና ፈቃድ ማውጣት አለበት፣

10.5 ቀደም ሲል የተሰጠ የግንባታ ፈቃድ በተለያየ ሁኔታ እንዲለወጥ ሲወሰን በአዲስ ተተክቶ ለባለይዞታው ይሰጣል፣

10.6 የግንባታ ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ በግንባታ ሥፍራው እንቅስቃሴ ካልተጀመረ ፈቃዱ ውድቅ ይሆናል፣ የግንባታ እንቅስቃሴ ተጀምሯል የሚባለው የመሠረት ቁፋሮና ለመሠረት ግንባታ የሚያስፈልግ ብረት ዝግጅት ሲጀመር ነው፡፡

10.7 ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊታገድ ይችላል፣

10.7.1 ግድፈት እያለበት በስህተት የፀደቀ ፕላን ሆኖ ሲገኝ፣

10.7.2 የግንባታ ፈቀድ ማመልከቻ የተሳሳተ መረጃ ከያዘ፣

10.7.3 ግንባታው ተቀባይነት ካለው ገደብ በላይ የሆነ የአካባቢ ብክልት የሚያስከትል መሆኑ ሲደረስበት የሕንፃ ፈቃዱ ይታገዳል/ይከለከላል፡፡

10.8 የግንባታ ፈቀድ ሳያስፈልጋቸው የሚከናወኑ ሥራዎች የውቅር አካላትን የማያናጉና አርክቴክቸራል ቅርፁን (form) የማይቀይሩ የውስጥ ቀለም ቅብ፣ የመስታወት መቀየር፣ ቀላል ክብደት ባላቸው የሚገነቡ የውስጥ ማከፋፈያ ግድግዳዎች፣ ነባር የመብራትና የሳኒታሪ መገጣጠሚያዎችን የመለወጥ ሥራ ናቸው፡፡

## 11. የግንባታ ፈቃድ ስለመጠየቅ

### 11.1 አጠቃላይ

11.1.1 ማንኛውም ሰው አዲስ፣ ተጨማሪ፣ የማሻሻያ፣ ጊዜያዊ ግንባታ፣የመጠቀሚያ ፈቃድ ወይም የማፍረስ ሥራ ለማከናወን ሲያቅድ በቅድሚያ የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል ይኖርበታል፣

11.1.2 አዲስ" ተጨማሪ" የማሻሻያ፣የመጠቀሚያ ፈቃድ፣ጊዜያዊ ግንባታ ወይም የማፍረስ ሥራ ለማከናወን የሚቀርብ የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ለአዲስ ለማስፋፊያ ወይም ለማሻሻያ ግንባታ በቅፅ 001 " ለግንባታ እድሳት ፈቃድ በቅፅ 005 " ለግንባታ ማፍረስ ፈቃድ ቅጽ 006፣ ለአገልግሎት ለውጥ ቅጽ 007፣ ለጊዜያዊ ግንባታ ቅጽ 020 በመሙላት የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ፣ በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ እና የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተያዘ ወይም የሚተዳደር ከሆነ በሃላፊ ተፈርሞ እና የድርጅቱ ማህተም አርፎበት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል፣

11.1.3 ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ስለወሰንተኞቹ ትክክለኛ መረጃ በወሰንተኛ ግንባታ መግለጫ ቅጽ 008 ላይ ወሰንተኛውን በማስሞላትና በማስፈረም ማቅረብ አለበት፣ ቅፁን ለመሙላት ፈቃደኛ በማይሆን ወሰንተኛ የከተማ አስተዳደሩ ቅፁን የማስሞላት ሃላፊነት አለበት፣

11.1.4 ወሰን ላይ የሚገነባ የምግብ ማብሰያና መሰል አገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ግድግዳ የእሳት ቃጠሎን በተሻለ ሁኔታ መከላከል በሚችል ድፍን የግድግዳ ቁሳቁስ መገንባት አለበት፣ ጭስ እና እንፋሎት ወደወሰነተኛ መውጣት የለበትም ::

11.1.5 በተለያዩ አካባቢዎች የሚገነቡ አንድ ዓይነት ስታንዳርድ ፕላኖች ያላቸው ግንባታዎች የየራሳቸው የግንባታ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፣

11.1.6 ደረጃ በደረጃ በመገንባት አገልግሎት ላይ ለማዋል ለሚታቀድ ሕንጻ የሚቀርብ የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ደረጃ በደረጃ ለመገንባት የታቀደው በፕላኖች ላይ በግልጽ በመመልከት መቅረብ ይኖርበታል፣

11.1.7 በተለያዩ ይዞታዎች ላይ ለሚገነቡ ሕንፃዎች የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብ መሟላት ያለባቸው፣

11.1.7.1 የፕላን ስምምነት ማስረጃ

11.1.7.2 የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ፣

11.1.7.3 በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 4.4 ላይ በተመለከተው መሠረት ለየምድቡ የተዘረዘሩ ኘላኖች ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

11.1.8 ማንኛውም ወሰን ላይ የሚገነባ የሕንጻ ዲዛይን ጥናት በንዑስ አንቀፅ 11.1.4 ከተመለከቱት በተጨማሪ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ማካተት ይኖርበታል፣

11.1.8.1 ወለልና በላይ ያለው ማንኛውም ግንባታ (የምድር በታች ወለል ቢኖረውም ባይኖረውም) ከወሰን ሁለት ሜትርና ከዚያ በታች ተጠግቶ የሚሰራ ከሆነ በቅድሚያ የወሰን ላይ ግንባታ ቅጽ008 መሙላትና ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፣

11.1.8.2 ለፈቃድ የሚቀርበው ስትራክቸራል ዲዛይን የወሰንተኛውን ነባር ህንፃ መዋቅር ይዘት ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፤

11.1.8.3 የሚቀርበው የዲዛይን ሠነድ የወሰንተኛውን ነባር ህንፃ መጠን ለምሳሌ ጭነት (Load) ከግምት ያስገባበት አግባብ ማመልከት አለበት፣

11.1.8.4 በወሰንተኛ ነባር ግንባታ ደህንነት ላይ ምንም አይነት መናጋት እንዳይፈጠር በቁፋሮና በግንባታ ሂደት መወሰድ የሚኖርበትን የሚያሳይ የጥንቃቄ ንድፍ ለፍቃድ ከሚቀርበው ሰነድ ጋር መቅረብ አለበት፣

11.1.9 አየር ማስገቢያ ሳይኖረው ብርሃን ብቻ የሚያስገባ ግንባታ ወሰን ላይ ለመሥራት ለዚሁ ተብለው በተዘጋጁና አሳልፊው በማያሳዩ ውፍረታቸው ከ5 ሳ.ሜ የማያንስ የመስታወት ግርግዳ መጠቀም ይቻላል ። ይህም በሚቀርበው ዲዛይን ላይ በግልጽ መጠቀስ ሲኖርበት ወሰን ላይ የተሰራ ከሆነ ወሰንተኛው እንደማንኛውም ድፍን የግድግዳ አካል አስጠግቶ ሊሰራበት ስለማይከለከል የብርሃን ማስገቢያ መስፈርት ለሚጠየቅበት ተጨማሪ ወይም አማራጭ የብርሃን ምንጭ ማመልከት አለበት፣

11.1.10 ማንኛውም ሠው ግንባታውን እስከ ወሠን አስጠግቶ ማከናወን ይችላል ሆኖም ወሠን ላይ ለመገንባት ያቀደ ሰው፡፡

11.1.10.1 በአዋሳኙ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሚያደርገውን የመከላከያ ዘዴዎች ለአጐራባቹ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

11.1.10.2 ግንባታው ተጀምሮ እስኪጠናቀቀ ድረስ በአጐራባቹ አደጋና ችግር በማያስከትል ሁኔታ መከናወን አለበት፡፡

11.1.10.3 በማንኛውም ጊዜ ወሰንተኛው ግንባታውን እንዲከታተል መፍቀድ አለበት፡፡

11.1.10.4 በማንኛውም የግንባታ ወቅት ለሚፈጠር ችግር ገንቢው ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡

11.1.1 በአዋጁ፣ በደንቡ እና በዚህ በመመሪያ እና በሌሎች የማስፈጸሚያ ሰነዶች ላይ የተገለፁትን መስፈርቶች ያላሟላ የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ በግንባታ መጠየቂያ ቅጽ ላይ በተመለከተው ቦታ ያልተሟላበትን ምክንያት በመግለፅ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፣

## 11.1. የእድሳት ፈቃድ

11.2.1 በታሪካዊ ቅርስነት የተመዘገቡና ታሪካዊ እሴት ያላቸው ሕንጻዎች ለማደስ በቅድሚያ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፣

11.2.2 ማንኛውም የግንባታ እድሳት ለማግኘት የሚፈለግ ሰው ፈቃድ ለማግኘት ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል የግንባታ እድሳት ማመልከቻ ቅጽ 005 በመሙላት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፣

11.2.3 የግንባታ እድሳት ማመልከቻ ቅጽ የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ ፣በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተያዘ ወይም የሚተዳደር ከሆነ በድርጅቱ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጎበት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል ፣

11.2.4 ከግንባታ እድሳት መጠየቂያ ቅጽ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሠነዶች፤

ሀ) የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣

ለ) የሚታደሰውን የህንጻ አካል ገጽና ቁስ (Elevation & Building Material) ነባር ሁኔታና የህንጻውን አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍና ዝርዝር መግለጫ መቅረብ ይኖርበታል፣

ሐ) ግድግዳ ወይም ጣራ የሚጋሩ ወሰነተኞች ካሉ በሚጋሩት ወሰን በኩል ስለሚካሄደው የእድሳት ስራ የወሰነተኛውን ንብረት ደህንነት ያገናዘበ ጥናት መቅረብ ይኖርበታል፣

11.2. የግንባታ ማፍረስ ፈቃድ

11.2.1. ማንኛውም ግንባታ ለማፍረስ የሚፈልግ ሰው ፈቃድ ለማግኘት ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ 006 በመሙላት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፣

11.2.2. የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ፣ በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተያዘ ወይም የሚተዳደር ከሆነ በድርጅቱ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጎበት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል፣

11.2.3. የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ለማግኘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰነዶች ተሟልተው ከግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ጋር መቅረብ አለባቸው&

ሀ. ቦታው በአመልካች ስም የተመዘገበ ለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ፣

ለ. ከሚፈርሰው ህንፃ ጋር ተያይዘው የነበሩ የመብራትና የውሃ አገልግሎቶች መቋረጣቸውን ወይንም መነሳታቸውን የሚገልጽ ማረጋገጫ፣

ሐ ሕንጻው ከእዳና እገዳ ውል ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

መ. ግድግዳ ወይም ጣራ የሚጋሩ ወሰንተኞች ካሉ በሚጋሩት ወሰን በኩል ስለሚካሄደው የማፍረስ ሥራ የወሰንተኛውን ንብረት ደህንነት ያገናዘበ ጥናት፤

ሠ. በታሪካዊ ቅርስነት የተመዘገቡና ታሪካዊ እሴት ያላቸው ሕንጻዎች ለማፍረስ በቅድሚያ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት ስምምነት መቅረብ ይኖርበታል፡

11.3.4 ከተጎራባች የሚጋሩት ግድግዳ ወይም ጣሪያ ካለ ፈቃድ ጠያቂው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (11.3.3) (መ) መሠረት የቀሪ ግንባታውን ደህንነት ለመጠበቅ የገባውን ግዴታ የሚዘረዝር የግንባታ ማስታወቂያ ቅጽ 009 ለአጎራባቹ እንዲደርሰው ይደረጋል፣

11.3.5 የግንባታ ማስታወቂያ የደረሰው ወሰንተኛ በማፍረስ ሥራ ወቅት ገንቢውን በግዴታ ውሉ ላይ ከተጠቀሰው ውጭ በመፈፀሙ ወይም በሌላ ምክንያት የነባር ህንፃ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር ተፈጽሟል በማለት የሚያቀርበው አቤቱታ ሲኖር ወዲያውኑ የግንባታ ስራውን በማስቆም አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎ ውሳኔ ይሰጣል፣

11.3.6 የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜ እንደ ህንፃው ዓይነት በከተማው አስተዳደር ይወሰናል፣

11.3. የነባር ግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ

11.3.1. የሕንጻ ሹም የከተማውን የኢንቨስትሜንት ቦታዎች ፍላጎት እና የከተማውን ፕላን ዕቅድ እያገናዘበ የነባር ግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፣

11.3.2. የነባር ግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀውን ቅጽ 001 ሞልቶ የፕላን ስምምነት፣ ቀደም ሲል የተሰጠ የግንባታ ፈቃድ ሙሉ ሠነድ እና የማሻሻያ ዲዛይን ሠነዶች አያይዞ ማቅረብ አለበት፣

11.3.3. የነባር ግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ በሚቀርብበት ይዞታ ላይ የሚገኝ ግንባታ በሙሉ በግልጽ ተለይቶ በንድፉ ላይ መታየት ይኖርበታል፣

11.3.4. በይዞታ ውስጥ የግንባታ ፈቃድ ደንብ እና መመሪያን የማይጠብቁ ተነጣጥለው የተሰሩ ግንባታዎች በነባር ግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ ላይ ተመልክተው የማሻሻያ ፈቃዱ እንደማይመለከታቸው በፈቃዱ ላይ በግልጽ ተጠቅሶ መፃፍ አለባቸው፣

11.3.5. የነባር ግንባታ ማሻሻያ ሥራ የማስፋፋት ስራን የሚጠይቅ ከሆነ፤

ሀ) የፕላን ስምምነት ማስረጃ፣

ለ) የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ፣

ሐ) በይዞታው ላይ የሚገኘውን ነባር ህንጻ የሚያሳይ ፕላን ቅጂ፣

መ) ከዚህ ቀደም ወጪ የተደረገ የግንባታ ፈቃድ ሙሉ ሰነድ እና የማሻሻያ ዲዛይን ሰነዶችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

11.4. የምሽት ግንባታ ሥራ ፈቃድ

11.4.1. ማንኛውንም ከምሽቱ አንድ ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ሰው የምሽት ግንባታ ሥራ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ 029 በመሙላት ማመልከት ይኖርበታል፣

11.4.2. የምሽት መገንቢያ ፈቃድ ሲጠየቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፤

ሀ) የአካባቢውን ነዋሪ ፀጥታ የማያናጋ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ) ለህገወጥ ግንባታ አመቺ ሁኔታ የማይፈጥር እና ተቆጣጣሪ መገኘት ያለበት አይነት የግንባታ ሥራ አለመሆኑ መረጋገጥ፣

ሐ) የግንባታ ማስጠንቀቂያ ወይም ማስቆሚያ ትዕዛዝ ያልተሰጠበት መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

11.4.3. የሕንጻ ሹም በምሽት ለመገንባት ከሚጠየቁ ሥራዎች ውስጥ ሊፈቀዱ የሚችሉትን ስራዎችና በተጓዳኝ መወሰድ የሚኖርበትን ጥንቃቄ በመዘርዘር ፈቃድ መስጠት ይችላል፣

11.4.4. የምሽት ግንባታ ፈቃድ ያለው ገንቢ ግንባታውን በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማከናወን ይኖርበታል፣ ያለምሽት ግንባታ ፈቃድ የምሽት ግንባታ ማከናወን አይፈቀድም፣

11.4.5. የሕንጻ ሹም በንዑስ አንቀጽ 11.4.2 የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የምሽት ግንባታ ሥራ እንዲበረታታ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡

## 12. የሕንፃ ሹም

12.1. በከተማው አስተዳደር ከንቲባ ወይም በተወከለው ወይም ከተማው ተጠሪ በሆነለት የወረዳ አስተዳዳር አካል የሚሾም ሕንፃ ሹም፣ በአርክቴክቸር፣በሲቪል ምህንድስና፣በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ማኔጅመንት ወይም በተመሳሳይ ሙያ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሆኖ በዲዛይን ዝግጅትና ምርመራ ወይም በግንባታ ሥራ ክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች አግባብነት ያለው ልምድ ሊኖረው ይገባል ፣

12.2. የከተማው አስተዳደር ከንቲባ ወይም የተወከለው አካል ወይም የወረዳው አስተዳዳሪ የህንፃ ሹም ለመሾም ከትምህርትና ከሙያ ዝግጅት መሥፈርት ምዝናው በተጨማሪ፣

12.2.1. በሥራ ዘመኑ የነበረው የሥራ አፈፃፀም፣

12.2.2. መልካም ሥነምግባር ያለው እና ለተለያዩ ሱሶች (ለአልኮልና ለአደገኛ ሱሶች) ተገዥ ያልሆነ፣

12.2.3. የማቀድ፣ የማደራጀት፣ የማስተባበር እና የመምራት ችሎታ ያለው፣

12.2.4. ተግባቢና ቀና አመለካከት ያለው፣

12.2.5. በቡድን የመስራት እና የባለቤትነት ስሜት ያለው፣

12.2.6. ደንበኛ ተኮር የሆነና የግንኙነት ችሎታ ያለው፣

12.2.7. የማወቅ ፍላጎት ያለውና ችግር ፈቺ የሆነ፣

12.3. በሙያው ትጉህና ሰርቶ የማሰራት ችሎታ ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

12.4. የህንፃ ሹም በከተማው አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገነቡ፣ ከከተማ ክልል ውጭ ሆነው ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው እና እንዲቆጣጠራቸው የተወከለባቸው ሕንፃዎች ላይ በሕንፃ አዋጁ በማስፈፀሚያ ደንቡና በዚህ መመሪያና በሌሎች ሕጎች መሠረት እየተገነቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደርጋል፣

12.5. የሕንፃ ሹሙ በአዋጁ፣ በደንቡ እና በዚህ መመሪያ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የሚቃረኑ ሆነው የተገኙ ግንባታዎች እንዲቆሙ፣ እንዲስተካከሉ ወይም እንዲፈርሱ ማዘዝ ይችላል፣

12.6. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (12.5) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕንፃ ሹሙ አስተዳደራዊ መቀጮ በመጣል እና ማስተካከያ መደረጉን በማረጋገጥ የግንባታ ማስቀጠያ ውሣኔ ይሰጣል፣

12.7. የህንፃ ሹሙ ተጠሪነት ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል ነው፡፡ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በሕንፃ አዋጁ፣ በማስፈፀሚያ ደንቡና በዚህ መመሪያ የተሰጡትን መብትና ግዴታዎች ያላከበረን የህንፃ ሹም አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከሥራ ያግዳል፣ ያሰናብታል፣ እንደየጥፋቱ ደረጃ በህግ ተጠያቂ ያደርጋል፣

12.8. የሕንፃ ሹሙ በክልሉ እና ቁጥጥር በሚያደርግባቸው የአስተዳደሩ አካባቢዎች አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያው ተፈፃሚ እንዲሆንባቸው የተደረጉ ሕንፃዎችን በመመልከት እንዲመረመሩና አስጊ ሆነው ከተገኙ በአፋጣኝ እንዲስተካከሉ ወይም ተገቢው የሙያ ሪፖርት ከቀረበ በኋላ እንዲፈርሱ የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል፣

13. አገልግሎት መግዛት

13.1. የሕንፃ ሹሙ በአስተዳደሩ ውስጥ አንድን የተወሰነ ሥራ ለመሥራት የሚችል ባለሙያ የማይገኝ ሲሆን ይህንን ሥራ ሊሰራ ከሚችል የተመዘገበ ባለሙያ ጋር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በመዋዋል ሊያሰራ ይችላል፡፡

13.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13.1 መሠረት ተዋውሎ የሚሠራ ባለሙያ ሥራውን በአዋጁ በደንቡ እና መመሪያ እና በውሉ መሠረት የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡

13.3. የሕንፃ ሹሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13.1 መሠረት ተዋውሎ የሚሠራው ባለሙያ ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣቱን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

13.4. የሕንፃ ሹሙ ለሦስተኛ ወገን ሊሠጥ የሚገባው ሥራው የሚጠይቀው ባለሙያ ቀጥሮ ማሠራት ካልቻለ መሆን ይኖርበታል፡፡

13.5. በሦስተኛ ወገን እንዲከናወን የተደረገን ሥራ የማፅደቅ ኃላፊነት የሕንፃ ሹሙ ይሆናል፡፡

14. የይግባኝ ሰሚ ቦርድ

14.1. የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በሕንፃ አዋጅ፣ ደንብና በዚህ መመሪያ መሠረት ውሣኔ ለመስጠት የሚችል ሙያዊ ብቃት ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ያቋቁማል፡፡ ለሚቋቋመው ቦርድ፤

14.1.1. ሰብሳቢና ፀሐፊ ይሰይማል፣

14.1.2. የሥራ ዘመን ይወስናል፣

14.2. የቦርዱ አባላት፣

14.2.1. ቴክኒካል ጉዳዮችን ለማየት ሙያውና የሥራ ልምድ ያላቸው፣

14.2.2. ከግንባታ ፈቃድ አሠጣጥና ክትትል ጋር ግንኙነት የሌላቸው፣

14.2.3. በመልካም ስነምግባር የሚታወቁ፣

14.2.4. በዲሲፒሊን ጥፋት ተከሰው እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፣

14.3. የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ ከከተማ አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል እና ከሚመለከታቸው ተቋማት የተውጣጡ ቁጥራቸው እንደጉዳዩ ውስብስብነት እና እንደ ከተማው ደረጃ የሚወሰን ሆኖ ከ5 እስከ 7 አባላት ይኖሩታል፡፡

14.4. የቦርዱ የሥራ ዘመን ከከተማ አስተዳደሩ የሥራ ዘመን ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

14.5. የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ አባላት ስብጥርና የሥራ ድርሻ እንደሚከተለው ይሆናል፣

14.5.1. የከተማው አስተዳደር ከንቲባ…………………… ሰብሳቢ፣

14.5.2. የሥራ ተቋራጮች ማህበር ተወካይ........................ አባል፣

14.5.3. በከተማው ከሚገኝ የፍትህ አካል ወይም ከተመሳሳይ ተቋም የሚወከል የህግ ባለሙያ ---------------------------------- አባል፣

14.5.4. በከተማው ከሚገኙ የሠራተኛና የመምህራንና የወጣቶች ማበራት እና ከከተማ ነዋሪዎች የሚመረጡ ተወካዮች .............አባል፣

14.5.5. የከተማው አስተዳደር ተወካይ -------------------------- አባልና ፀሐፊ፡፡

14.6. ማንኛውም ሰው በሕንፃ ሹሙ በተሰጠ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ቅሬታ ካለው የህንፃ ሹሙ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በደረሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ቦርድ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

14.7. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

1. ቦርዱ ግንባታዎችን በተመለከተ በሕንፃ ሹም በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ይኖረል፡፡
2. የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ አቤቱታ በደረሰው በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን የሚመለከትበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በመወሰን ለአመልካቹ ከአምስት የሥራ ቀናት በፊት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. ቦርዱ ለሚቀርብለት የይግባኝ አቤቱታ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም የጉዳዩ ባህሪ ተጨማሪ ጊዜ የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ የውሳኔው ጊዜ ለአንድ ተጨማሪ ወር ሊራዘም ይችላል፡፡
4. ቦርዱ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሌሎች ባለሙያዎችን እገዛ መጠየቅ ይችላል፡፡
5. ቦርዱ ቴክኒክ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
6. ቦርዱ በቀረበለት ይግባኝ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ለአመልካቹ እና ለህንጻ ሹሙ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

14.8. የከተማው አስተዳደር ለቦርዱ አባላት አበል ሊከፍል ይችላል፡፡

14.9. ቦርዱ ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር ይሆናል፡፡

14.10. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በግንባታ ፈቃድ ይግባኝ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ 027 ይሆናል፣

14.11. የቦርዱ ሰብሳቢና ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባራት፣

14.11.1. የቦርዱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር፣

ሀ) ቦርዱን በበላይነት ይመራል፣

ለ) ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ከአባላቱ ውስጥ ስብሰባውን የሚመራ በአስተዳደሩ እንዲወከል ያደርጋል፣

ሐ) ቦርዱ የሚመራበትን የሥራ መመሪያ ከቦርዱ አባላት ጋር ያዘጋጃል፣

መ) አቤቱታዎችን ይቀበላል፣

ሠ) አከራካሪ ጉዳይ ሲያጋጥም ውሣኔ በድምፅ ብልጫ እንዲከናወን ያደርጋል፤ የቦርዱ አባላት የሚሰጡት ድምፅ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ያለበት ወገን አሸናፊ ይሆናል ፣

ረ) ቦርዱ የሚሰጠውን ውሣኔ ለአቤቱታ አቅራቢው፣ ለሕንፃ ሹሙ እና ለከተማው አስተዳደር በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፣

ሰ) በፍርድ ቤት ሲጠየቅ የውሳኔው ቅጂ ይሰጣል፣

ቀ) የቦርዱን በጀት በማዘጋጀት ለከተማ አስተዳደሩ አቅርቦ ያጸድቃል፣

**14.11.2.** የቦርዱ ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር፤

ሀ) የስብሰባ አጀንዳና ቃለ ጉባዔ  እየያዘና በአግባቡ እያዘጋጀ አባላቱ እንዲፈርሙበት ያደርጋል፣

ለ) አስፈላጊ መረጃዎች እና ሰነዶች  በስብሰባ ወቅት ተሟልተው እንዲገኙ ያደርጋል፣

ሐ) ቦርዱ የተሟሉ ሰነዶች እና መዛግብቶች እንዲኖሩት ያደርጋል፣

መ) ከቦርዱ ሰብሳቢ በሚሠጠው መመሪያ መሠረት አጀንዳ ያዘጋጃል፣

ሠ) የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፣

ረ) አቤቱታ የቀረበባቸውን ሰነዶች እና ለምርመራ የተሰበሰቡ መረጃዎችን መዝግቦ ይይዛል፣

ሰ) ውሳኔ የተሰጠባቸውንና ሌሎች ሠነዶችን መዝግቦ በጥንቃቄ ይይዛል፣

14.12. በሕንፃ አዋጁ፣ በደንቡና በዚህ መመሪያ የተመለከቱት በአግባቡ ባለመፈፀማቸው ቅሬታ ያለው ሰው ጉዳዩ እንዲታይለት ለቦርዱ  በቅጽ 019 መሠረት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፣

## 15. ትዕዛዝ አለማክበር

15.1. ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ የአዋጁን፣ የደንቡንና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ማክበር ይኖርበታል፣

15.2. በአዋጁና በደንቡ የተቀመጡተን ድንጋጌዎች እና ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራት

15.2.1. ፍቃድ የተሰጠበት ፕላን ማመልከቻ ኮፒ በግንባታ ቦታ አለመገኘት

15.2.2. የውስጥ አደረጃጀት /የግንባታ ቅድመ ዝግጅት/ ሳያሟሉ ሥራ መጀመር

15.2.3. የተሰጡ የማስተካከያ ትእዛዞችን ካጠናቀቁ በኋላ አለማስታወቅ

15.2.4. የተሰጡ ትእዛዞችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለማከናወን

15.2.5. ከግንባታ ክልል ውጪ የተቀመጠን የግንባታ ቁሳቁስ ወይንም ተረፈ ምርት በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ መሠረት አለማንሳት

15.2.6. ካለ ተቆጣጣሪ ማሰራት

15.2.7. ካለማስታወቂያ ሥራ መጀመር

15.2.8. ያለ ፈቃድ ዕድሳት ማድረግ

15.2.9. ያለፈቃድ የማስፋፋት ሥራ ማከናወን

15.2.10. ያለፈቃድ የማፍረስ ሥራ ማከናወን

15.2.11. በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ ርምጃዎች አለመውሰድ

15.2.12. የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ መጠቀም የመሳሰሉትን ተግባራት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ትዕዛዝ እንዳላከበረ ይቆጠራል።

15.3. ማንኛውም ሰው ከላይ በንዑስ አንቀጽ 15.1 እና 15.2 የተመለከቱትን የማያከብር ሆኖ ከተገኘ በሕንፃ ሹሙ በሚሰጥ የግንባታ ማስቆሚያ ማስጠንቀቂያ ቅጽ 014 መሰረት ትዕዛዝ ግንባታው እንዲቆም፣ ወይም እንዲፈርስ ወይም እንዲስተካከል ይደርጋል፣

15.4. በግንባታ ወቅት ማንኛውንም በህንፃ ሹሙ ወይም በሚወክለው አካል የሚሰጥ ትዕዛዝን አለመቀበል ገንቢው ወይም የህንፃው ባለቤት በግልም ሆነ በጋራ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል ፣

## 16. ስለማስታወቂያ

1. ማንኛውንም በምድብ "ለ" እና "ሐ" የሚገኝ ሕንፃ ለመገንባት የፀደቀ ፕላን ያለው ሰው የየሥራው እርከን የሚጀምርበትን ጊዜ የሚገልጽ ማስታወቂያ የሥራ እርከኑን ከመጀመሩ 5 የሥራ ቀናት አስቀድሞ ለሕንፃ ሹሙ በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል።

16.1. ማንኛውም የፀደቀ ፕላን ያለው ሰው የግንባታ ማስታወቂያ ለቀረበበት የሥራ እርከን ሥራው ከመጀመሩ በፊት ከላይ በንዑስ አንቀጽ 16.1 በተመለከተው መሠረት ለሕንፃ ሹሙ የግንባታ ሥራ ማሳወቂያ ቅጽ 025 ሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፣

16.2. ለምድብ "ለ" እና "ሐ" ህንጻዎች ለአዲስ ግንባታ ማስታወቂያ ሊቀርብባቸው የሚገቡ የስራ እርከኖች የሚከተሉት ናቸው፣

16.2.1. የመሠረት ሥራ ለመጀመር የሚያስችል የቅየሣ ሥራ ሲያጠናቅቅ፣

16.2.2. የመሠረት ኮንክሪት ሙሌት ከመጀመሩ በፊት፣

16.2.3. በየደረጃው ያለ የወለል ኮንክሪት ሙሌት ሥራ ከመጀመሩ በፊት፣

16.2.4. የመጨረሻው የኮንክሪት ሙሌት ሥራ ከመጀመሩ በፊት፣

16.2.5. የውሃ አቅርቦት፣ የሳኒታሪ፣ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ገጠማ ተጠናቆ ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ፣

16.2.6. እንደ ሥራው ዓይነት እና የአሠራር ዘዴ በሕንፃ ሹሙ የሚጠየቁ ተጨማሪ እርከኖች፡፡

16.3. የሕንፃ ሹም ማስታወቂያ ለቀረበበት የሥራ እርከን በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ በግንባታው ቦታ በመገኘት ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

16.4. ለነባር ግንባታ ማሻሻያ እና ማስፋፊያ ሥራ እንደ ሥራው ዓይነት ወይም እንደሚከናወነው ተግባር ማስታወቂያ የሚቀርብበትን የሥራ እርከን የሕንፃ ሹሙ ለገንቢው ያሳውቃል፣

## 17. ስለ ተቆጣጣሪዎች

17.1. ማንኛውም በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመ አካል ማንነቱን የሚገለጽ መታወቂያ የያዘ የግንባታ ሥራ ተቆጣጣሪ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ወይም ግንባታ በሚከናወንበት በማንኛውም ጊዜ እንዲሁም የምሽት ግንባታ ካለ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ በግንባታው ቅጥር ግቢ ተገኝቶ የቁጥጥር ሥራ ማከናወን ይችላል ያከናወነውን የቁጥጥር ተግባር የሰጠውን ትዕዛዝ በግንባታ መከታተያ ቅጽ 13 በመሙላት ለሕንጻ ሹሙ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል ፣

17.2. በማንኛውም ወቅት ወደየትኛውም ይዞታ ለክትትልና ቁጥጥር ተግባር የሚንቀሳቀስ የግንባታ ሥራ ተቆጣጣሪ በዕለቱ ወደ ግንባታ ቦታ መግባት ያስፈለገበትን ምክንያት እና በግንባታው ቦታ ተገኝቶ ያከናወነውን የቁጥጥር ሥራ ዝርዝር፣ የተገኘውን ውጤትና የሰጠውን ለተቆጣጣሪዎች በተለየ እና በግንባታ ቦታ በሚቀመጥ የቁጥጥር መዝገብ ላይ ሞልቶ በማስፈረምና በመፈረም ቅጂውን ለግንባታው ባለቤት ወይንም በግንባታው ቦታ ለሚገኝ ተጠሪ መስጠት አለበት፣የቁጥጥር መዝገብ ተከታታይ ዋና እና ቀሪ የገጽ ቁጥር፣የትእዛዝ መስጫ ቦታ፣የስኬች መስሪያ ቦታ፣ለተቆጣጣሪ ለሥራ ተቋራጭ እና ለአማካሪ የፊርማ ቦታ የያዘ መሆን ይኖርበታል ፣

17.3. የሕንጻ ተቆጣጣሪው የሕንፃ አዋጁን፤ የሕንጻ ደንቡን፤ ይህን መመሪያ እና ተጓዳኝ ሕጐችንና ውሎችን በመተላለፍ የሚካሄድ ግንባታ እንዲቆም ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡ የማስቆሚያ ትዕዛዝ የሚሰጠው በአንቀጽ 17.2 ላይ በተመለከተው መሠረት እና የግንባታ ማስቆሚያ ቅጽ 015 በመሙላት ይሆናል፣

17.4. ያለምንም የፅሑፍ ማስታወሻ የሚደረግ የግንባታ ቦታ ጉብኝትም ሆነ የሚሰጥ የቃል ትዕዛዝ ህጋዊነት አይኖረውም፣

17.5. የህንፃ ሹሙ ወይም የሚወክለው አካል ከግንባታው ባለቤት የግንባታውን ክትትልና ቁጥጥር ሥራ አስመልክቶ ለሚቀርብለት ማስታወቂያ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በግንባታ ክትትል ውሳኔ መግለጫ ቅጽ 016 በመሙላት መልስ መስጠት ይኖርበታል፣

## 18. ቁሳቁስ

18.1. የሕንፃ ሹም በግንባታ ሥፍራ የተቀመጠ ወይም በሕንፃው ሥራ ላይ የዋለ ግብዓት በናሙና ፍተሻ ውጤቱ ተቀባይነት ካጣ እንዲወገድ ወይንም በአጠቃቀሙ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

18.2. በግንባታ ግብዓት ጥራት ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም አደጋ ወይንም ጉድለት የግንባታው ባለቤት ሃላፊነት አለበት፡፡

18.3. ከላይ በአንቀጽ 18.1 እና 18.2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕንፃ ሹሙ ለግንባታው ያገለግላሉ ተብለው የተቀመጡ ወይም ሥራ ላይ የዋሉ የግንባታ ቁሳቁሶች የጥራት ጉድለት እንዳለባቸው በእይታም ሆነ በግንባታ ቦታ በሚደረግ ፍተሻ ካረጋገጠ እንዲወገድ ወይም ማስተካከያ እንዲደረግ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፣

18.4. የግንባታ ቁጥጥር የሚያደርጉ ባለሙያዎች ለግንባታ የሚቀርበውን ቁሳቁስ ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፣

18.5. የሕንፃ ሹሙ ማንኛውም ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ለግንባታ ግብዓት ለሚውሉ ቁሳቁሶች የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊጠይቅ ይችላል፣

## 19. የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ

19.1 በምድብ "ሐ" ስር ለሚካተቱ ህንፃዎች የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ማመልከቻ በቅጽ 018 መሠረት ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፣

19.2 የማመልከቻው ቅፅ በሕንፃው ባለቤት ወይም በህጋዊ ወኪሉ ወይም የመንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ንብረት ከሆነ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጐ መቅረብ አለበት፣

19.3 ከማመልከቻው ቅፅ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች፤

19.3.1. ለአዲስ ግንባታ፣

ሀ) የግንባታ ፈቃድ

ለ) የግንባታ ማስጀመሪያ ሠነድ

ሐ) ግንባታው መጠናቀቁን የሚያረጋግጥ አማካሪ መሐንዲስና የሕንፃው ባለቤት የተፈራረሙበት የርክክብ ሠነድ

መ) የፕላን ማሻሻል ወይም ለውጥ ከተደረገ የተሻሻለውን አካቶ የተዘጋጀ ወይም የተከለሰ ፕላን ቅጂ፣

ሠ) በክትትልና ቁጥጥር ስለማለፉ ከፋይሉ ጋር የሚቀርቡ ሠነዶች ለክትትልና ቁጥጥር የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበት ደረሠኝ ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

19.3.2. ለነባር ሕንፃ ያገልግሎት ለውጥ ወይም ማስፋፋት በማድረግ ለሚቀርብ የመጠቀሚያ ፈቃድ፣

ሀ) የአገልግሎት ለውጥ ፈቃድ የፕላን ስምምነት፣

ለ) ለአገልግሎት ለውጥ የተፈቀዱ ፕላኖች ወይም ዝርዝር ሥራዎች

ሐ) በተፈቀደው ፕላን መሠረት መጠናቀቁን የሚገልፅ የርክክብ ሠነድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

19.3.3. ደረጃ በደረጃ ወይም በየምዕራፉ ለሚደረግ ግንባታ የደረጃ በደረጃ ፈቃድ፣ የመጀመሪያው ደረጃ መጠናቀቁን የሚገልጽ ተቆጣጣሪዎቹ በፊርማቸው ያረጋገጡበት ሠነድ መቅረብ ይኖርበታል፣

19.4 የሕንፃ ሹሙ የቀረበለትን ሠነድ ከላይ በተዘረዘረው አግባብ መሠረት መርምሮ የተሟላ ከሆነ እና ሕንጻው መጠናቀቁን ካረጋገጠ የመጠቀሚያ ፈቃድ ምሥክር ወረቀት ይሠጣል፣

## 20. የቁጥጥር ክፍያ

20.1. በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 16.2 እና 16.4 መሠረት ማስታወቂያ ለቀረበባቸው የምድብ "ለ" እና "ሐ" ሕንፃዎች የሥራ እርከን ለሚደረግ ጉብኝት ወይም ቁጥጥር የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፣

20.2 የክትትል የአገልግሎት ክፍያ መደበኛ ክትትል ለሚደረግባቸው የሥራ እርከኖች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ በመሆኑ ተጨማሪ ክትትል እንዲደረግ በሚጠይቅ የግንባታ ደረጃ ተጨማሪ ክፍያ አይጠየቅም፣

20.3 በቁጥጥር ማስታወቂያ ከቀረበባቸው የሥራ እርከኖች ውጪ ለሚደረግ ድንገተኛ የቁጥጥር ጉብኝት የቁጥጥር አገልግሎት ክፍያ አይፈጸምባቸውም፣

20.4 ለሕንፃ ግንባታ የሚደረግ የቁጥጥር ሥራ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 16.2 ለተመለከቱት ሕንፃዎች በተቀመጡት የሥራ ደረጃዎች መሠረት ይሆናል፡፡

20.5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 20.4 በተመለከተው መሠረት ለሚደረግ የቁጥጥር ሥራ ለየምድቡ የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ፤

(ሀ) ለምድብ ለ/ ህንፃ ብር 400፣

(ለ) ለምድብ ሐ/ ህንፃ ብር 800 ይሆናል፡፡

20.6 ለማንኛውም ግንባታ የቁጥጥር ክፍያ የሚፈፀመው ቁጥጥር የሚደረግበትን የሥራ እርከን ለመጀመር ገንቢው የግንባታ ሥራ ማስታወቂያ ቅጽ 025 ሲያቀርብ ይሆናል፣

20.7 የቁጥጥር አገልግሎት ክፍያው የተፈጸመበት ማስረጃ ወይም ደረሰኝ ቅጂ በግንባታ ፈቃድ ፋይል ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ ይኖርበታል፣

20.8 የቁጥጥር ክፍያ የሚፈፀመው በፋይናንስ ሰርዓት ደንብና መመሪያ መሠረት ይሆናል፣ ከዚህ ውጭ የሚፈፀሙ ክፍያዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፣

## 21. ተመላሽ ክፍያዎች

21.1. ተመላሽ ክፊያ የሚባለው አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ ወይም ክፍያ የተፈፀመበት አገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ወይም አገልግሎቱ ከሚጠይቀው በትርፍነት የተከፈለ ክፍያ ነው፡፡

21.2. አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ እንዲመለስለት የሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን ክፍያው የተፈጸመበትን የአገልግሎት ዓይነት እና ክፍያው ተመላሽ እንዲሆን የተጠየቀበትን ምክንያት በመግለጽ ክፍያ ከተፈጸመበት ደረሰኝ ኮፒ ጋር በማያያዝ ማመልከት አለበት፡፡

21.3. ማንኛውንም ክፍያ አገልግሎት ያልተፈጸመበት መሆኑ ሲረጋገጥ ተመላሽ ይደረጋል፣

21.4. ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ ተመላሽ እንዲሆን በማመልከቻ ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ 26 ሞልቶ የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ፣ የመንግስታዊ፣ የሕዝባዊ እና የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሆነ የድርጅቱ ማህተም ተደርጎ እና በሃላፊ ተፈርሞ መቅረብ ይኖርበታል፣

21.4.1. ክፍያው የተፈፀመበትን የአገልግሎት ዓይነት በመጥቀስ፣

21.4.2. የክፍያ ቅጂ ደረሰኝ በማያያዝ፣

21.4.3. ተመላሽ እንዲሆን የተጠየቀበትን ምክንያት በግልጽ በመፃፍ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

21.5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 21.2 መሠረት ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርብ ጥያቄ ክፍያው ከተከፈለበት ቀን ጀምሮ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም፣

21.6. የተመላሽ ክፍያ አፈፃፀም በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት ይከናወናል፣

## 22. መቀጮ

22.1. የከተማው አስተደደር የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በሚተላለፍ አካል ላይ እንደ ሕንጻ ምድብና እንደ ጥፋቱ ዓይነት አስተዳደራዊ መቀጮ ይጥላል፣ የቅጣት ውሳኔው የሚተላለፈው የቅጣት ውሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ 021 በመሙላት መሆን ይኖርበታል ፡፡ የጥፋቱ አይነትና የቅጣቱ መጠን በህንጻ ደንቡ አንቀጽ 44 መሰረት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የህንፃ ምድብ እና አስተዳደራዊ ቅጣት መጠን (ብር) | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ምድብ ሀ | ምድብ ለ | ምድብ ሐ |
| 1 | ፍቃድ የተሰጠበት ፕላን ማመልከቻ ኮፒ በግንባታ ቦታ አለመገኘት | ---------- | 2000 | 3000 |
| 2 | የውስጥ አደረጃጀት /የግንባታ ቅድመ ዝግጅት/ ሳያሚሉ ሥራ መጀመር | ----------- | 2000 | 3000 |
| 3 | የተሰጡ የማስተካከያ ትእዛዞ ችን ካጠናቀቁ በኂላ አለማስ ታወቅ | 1000 | 2000 | 3000 |
| 4 | የተሰጡ ትእዛዞችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለማከናወን | 1000 | 2000 | 3000 |
| 5 | ከግንባታ ክልል ውጪ የተቀ መጠን የግንባታ ቁሳቁስ ወይ ንም ተረፈ ምርት በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወ ቂያ መሠ ረት አለማንሳት | 1000 | 2000 | 3000 |
| 6 | ካለተቆጣጣሪ ማሰራት | ------------ | 3000 | 5000 |
| 7 | ካለማስታወቂያ ሥራ መጀመር | ------------ | 2000 | 4000 |
| 8 | ያለፈቃድ ዕድሳት ማድረግ | 2000 | 3000 | 5000 |
| 9 | ያለፈቃድ የማስፋፋት ሥራ ማከናወን | 2000 | 3000 | 5000 |
| 10 | ያለፈቃድ የማፍረስ ሥራ ማከናወን | 2000 | 3000 | 5000 |
| 11 | በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃ ዎች አለመውሰድ | ………… | 3000 | 5000 |
| 12 | የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ መጠቀም | ………… | 3000 | 5000 |

22.2. ከዚህ በላይ በተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ያልተመለከቱ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ የህንፃ ሹሙ እንደጥፋቱ ክብደት በሠንጠረዡ ለየህንፃ ምድቡ ከተመለከቱት ቅጣቶች ውስጥ ተመጣጣኝ ነው ብሎ ያመነበትን ቅጣት ይጥላል፡፡

22.3. የተፈጸመው ጥፋት በአዋጁ በተመለከቱት የወንጀል ድንጋጌዎች ስር የሚወድቅ ሆኖ ሲገኝ የሕንፃ ሹሙ ተገቢ ነው ብሎ የሚወስደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጥፊው ላይ የወንጀል ክስ እንዲቀርብበት ለሚመለከተው አካል መምራት አለበት፡፡

22.4. የሚጣለው አስተዳደራዊ መቀጮ ከተደራራቢ ጥፋቶች ወይም የከተማው አስተዳደር ወይም የህንፃ አዋጅ ከሚደነግገው የገንዘብና የእሥራት ቅጣት ነፃ አያደርግም፣

22.5. አስተዳደራዊ መቀጮ መክፈል የግንባታ ሥራውን የማስቆም፣ የማስነሳት ወይም የማፍረስ ርምጃዎችን ከመውሰድ የሚያግድ አይሆንም፣

22.6. በአንድ ጊዜ ለሚፈፀሙ ተደራራቢ ጥፋቶች የቅጣቱ መጠን እንደ ሕንፃው ምድብ ለየጥፋቱ የተመለከተው ድምር ይሆናል፣

## 23. ጊዜያዊ ግንባታ

23.1. አጠቃላይ

23.1.1 ማንኛውም ጊዜያዊ ግንባታ የሚያካሂድ ሰው ግንባታውን ለማከናወን የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፣

23.1.2 የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ጥያቄ መቅረብ ያለበት የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ 020 በመሙላት ይሆናል፣

23.1.3 ለጊዜያዊ ግንባታ ለቀረበ ማመልከቻ የሕንፃ ሹሙ ግንባታው በህንፃ አዋጁ፣ ደንቡና በዚህ መመሪያ መሠረት እንዲከናወን ጊዜያዊ ፈቃድ ይሰጣል፣

23.1.4 የጊዜያዊ ግንባታ አገልግሎት በጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫ ላይ የተጠቀሰው አገልግሎት ይሆናል፣

23.1.5 ማንኛውም  ጊዜያዊ ግንባታ በቀላሉ ሊነቃቀል በሚችል ቁስ የሚገነባ እና የአካባቢውን ውበት እና የተጠቃሚውን ደህንነት በጠበቀ መልኩ መሰራት ይኖርበታል፣

23.1.6 ለተንዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ የሚገነባ አጥር ለአካባቢው ውበት በሚሰጥ ቁሳቁስ መገንባትና ተስማሚ ቀለም መቀባት አለበት፣ ሆኖም በቀለም አቀባብ ከሚፈጠር ቅርጽ /Pattern/ በስተቀር የማስታወቂያ ጹሁፎችን መቀባት አይቻልም፣

23.1.7 ለወቅታዊ ጊዜያዊ ግንባታ የሚተከሉ መጠለያዎች የተለየ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር በመተላለፊያ መንገዶች ላይ መሆን የለበትም፣

23.1.8 አውቶቡስ ማቆሚያ፣ የህዝብ ስልክ መከለያ፣ ለአነስተኛ ጥቃቅን ንግድ ዘርፎች እና ለመሳሰሉ የህዝብ መገልገያ ጊዜአዊ ግንባታ የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫ እና  ዲዛይን መቅረብ አለበት፣

23.1.9 የጊዜያዊ ግንባታ የመጠቀሚያ ዘመን ሲያበቃ ግንባታውን በጊዜያዊ ግንባታው የቀድሞ ባለቤት ወጪ ተነስቶና ቦታው በነበረበት ሁኔታ ተስተካክሎ መለቀቅ አለበት፣

23.2. **የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ አቀራረብ እና የጊዜ ገደብ፤**

23.2.1. ለኮንትራታዊ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ 020 ጋር የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ፣ የጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫ እና የጊዜያዊውን ግንባታ አርክቴክቸራልና እንደአስፈላጊነቱ የስትራክቸራል እና ኤሌክትሪካል ንድፍ ተያይዞ መቅረብ አለበት፣ የግንባታው የጊዜ ገደብ በጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫው ላይ የተጠቀሰው ዘመን ይሆናል፣

23.2.2. ለተጓዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ፣ የዋናው ግንባታ ፈቃድ ኮፒ እና የጊዜያዊ ግንባታውን የቦታ አቀማመጥ እንዲሁም ወደ ግቢ መውጫ መግቢያውን የሚያሳይ ንድፍ መቅረብ አለበት፣ የግንባታው የጊዜ ገደብ የግንባታው መጠናቀቅ ወይንም የግንባታ ፈቃድ የጊዜ ገደብ ይሆናል፣

23.2.3. ለወቅታዊ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ጋር ጊዜያዊ ግንባታው የተፈለገበትን ምክንያት በመግለጽ መቅረብ ይኖርበታል። የዚህ ግንባታ የአገልግሎት ጊዜ ገደብ በከተማው አስተዳደር የሚወሰን ሆኖ የጊዜ ገደቡ ከ7 ቀን መብለጥ የለበትም፣

## 24. የአገልግሎት ለውጥ ስለማድረግ፣ ስለማስፋፋት፣ እድሳት ወይም ጥገና ስለማድረግ እና ስለማፍረስ

24.1. የህንፃ ሹሙ ከአዋጁ፣ ከማስፈፀሚያ ደንቡ እና ከዚህ መመሪያ ጋር እስከተጣጣመ ድረስ የህንፃ አገልግሎት ለውጥ የማድረግ፣ የማስፋፋት፣ እድሳት የማድረግ፣ የመጠገን ወይም የማፍረስ ፈቃድ ይሰጣል፣

24.2. ማንኛውም ባለይዞታ በሕንፃው ላይ የአገልግሎት ለውጥ ለማድረግ፣ ለማስፋፋት፣ እድሳት ወይም ጥገና ለማድረግና ለማፍረስ ሲያቅድ ሥራው ከመጀመሩ በፊት የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፣

24.3. የአገልግሎት ለውጥ ለማድረግ፣ ለማስፋፋት፣ እድሳት ወይም ጥገና ለማድረግና ለማፍረስ የሚቀርብ ጥያቄ በቅጽ 001፣005 ወይም 006 እንደቅደም ተከተላቸው የሚመለከተውን ቅጽ በመሙላት መሆን ይኖርበታል

24.4. የአገልግሎት ለውጥ፣ የማስፋፋት፣ የማደስ፣ የመጠገን፣ ወይም የማፍረስ ሥራ ለማከናወን ሲጠየቅ የሕንፃ ሹሙ ሕንፃው የሚገኝበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ ፕላኖችን፣ የሥራ ዝርዝርን፣ ትንታኔዎችንና ሌሎችንም ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት ሊጠይቅ ይችላል፣

24.5. ማንኛውም የአገልግሎት ለውጥ፣ የማስፋፋት፣ የመጠገን ወይም የማፍረስ ሥራ የሚያከናውን ሰው ሥራውን ማከናወን የሚኖርበት የፕሮጀክት ግምቱን መሰረት በማድረግ ደረጃው በሚመጥን የሥራ ተቋራጭ መሆን ይኖርበታል፣

24.6. ማንኛውም ባለይዞታ የማፍረስ ሥራ ሲያከናውን በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳያስከትልና ማንኛውንም እንቅስቃሴ እንዳያስተጓጉል ቅድመ ጥናት ማድረግ ይኖርበታል፣ ሥራውን ሲያከናውንና ሲያጠናቅቅ ፍርስራሹን በማስወገድና ቦታውን በማስተካከል ወደ ነበረበት ሁኔታ መመለስ አለበት፣

24.7. ማንኛውም ባለይዞታ የማፍረስ ሥራ ለማከናወን ሲያቅድ ምን ምን ሥራዎችን በቅደመ ተከተል ለማከናወን እንዳቀደና ሌላውን ወይም የተጐራባቹን ጥቅም ላለመንካት ያደረገውን ጥናት አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ የማፍረስ ሥራ ከመጀመሩ አስቀድሞ የመሠረተ ልማት አውታሮች መቋርጥ ስለአለባቸው ባለይዞታው ይህንኑ ለሚመለከታቸው ክፍሎች በማሳወቅ መቋርጣቸውን የሚያረጋግጥ መረጃ ማቅረብ አለበት፣

24.8. ማንኛውም ባለይዞታ በጋራ ግድግዳ የሚጠቀምባቸውን ግንባታዎች ለማፍረስ፣ ለመጠገን እና ለማስፋፋት ሲያቅድ ከጋራ ተጠቃሚዎች የጽሑፍ ስምምነት ማቅረብ አለበት፣

24.9. ማንኛውም ባለይዞታ የእድሳት፣ የጥገናና የማስፋፋት ሥራዎችን ለማከናወን ሲያቅድ የሕንጻውን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይ (As built drawings) እና ሕንጻው ለሚፈለገው አገልግሎት ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ለሚሰራው ስራ የሚያስፈልጉትን ፕላኖች እና የስራ ዝርዝር አያይዞ ማቅረብ አለበት፣

24.10. ማንኛውም ባለይዞታ የአገልግሎት ለውጥ ለማድረግ ሲያቅድ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ 007 መሙላት አለበት፣

## 25. የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠር

25.1. ለማንኛውም ምድብ የሕንፃ ዓይነቶች የሚጠየቁ ዲዛይኖች ለሥራው በሚመጥኑ የተመዘገቡ ባለሙያዎች መሠራት አለባቸው፣

25.2. የሚቀጠሩ የዲዛይን ባለሙያዎች የዲዛይን ሥራ ለማከናወን የተመዘገቡና ለበጀት ዓመቱ የታደሰ የባለሙያ ምስክር ወረቀት የያዙ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያላቸው መሆን አለበት ፣

25.3. በአንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 25.2 መሠረት የሚቀጠሩ የዲዛይን ባለሙያዎች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለዲዛይን እና ለቁጥጥር ሥራ ያወጣውን ዝቅተኛ መስፈርት ማሟላት አለባቸው፣

25.4. ለማንኛውም የሕንፃ ምድብ ለሚደረግ የቁጥጥር ሥራ ለየሥራው በሚመጥኑ የተመዘገቡ እና ለበጀት ዓመቱ የታደሰ የባለሙያ የምስክር ወረቀት ባላቸው ባለሙያዎች ቁጥጥሩ መደረግ ይኖርበታል ፣

25.5. ማንኛውም የተመዘገበ የዲዛይን ባለሙያ ወይም ድርጅት ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት ለሰራው ፕላንና የሥራ ዝርዝር ወይንም ሁለቱንም አገልግሎት በጣምራ ሲያከናውን ሊደርሱ ለሚችሉ ጉዳቶች እና ግድፈቶች ከታወቀ የመድህን ድርጅት የጉዳት ማካካሻ ዋስትና ማቅረብ አለበት፣

25.6. የዋስትናው ዓይነትና መጠን በደንቡ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 በተመለከተው መሰረት እንደሚከተለው ይሆናል፣

| ተ.ቁ | የሕንጻ ምድብ | የፕሮጀክት ግምት /ብር/ | የዋስትና መጠን (የፕሮጀክቱን ግምት) | የዋስትና መጠን ጣሪያ /ብር/ | የዋስትና ጊዜ | የዋስትና አቀራረብ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከሪል እስቴት ውጪ ያሉ የምድብ "ለ" ህንጻዎች | 5,000,000 | 10 በመቶ | 500,000 | ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ | ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት |
| 2 | ለሪል እስቴት እና ለምድብ "ሐ" ሕንፃዎች | 2,500,000 | 20 በመቶ | 500,000 | ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ | ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት |
| | | 10,000,000 | 15 በመቶ | 1,500,000 | | |
| | | 20,000,000 | 10 በመቶ | 2,000,000 | | |

25.7. ለዋስትና መጠን ስሌት የሚሆነው የፕሮጀክት ዋጋ ግምት የሚሰላው በህንጻው ጠቅላላ ስፋት እና የህንጻ ሹሙ አዘጋጅቶ በሚያቀርበው እና በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል በሚጸድቀው የየምድቡ የካሬ ሜትር የግንባታ ዋጋ ስሌት መሠረት ይሆናል፡፡

25.8. የፕሮጀክት ዋጋ ለህንጻ ምድቡ በተመለከቱት ሁለት ዋጋዎች መካከል ሲሆን የዋስትና መጠኑ የሚሰላበት የላይኛውን መቶኛ ተመጣጣኝ መለኪያ ንጽጽር (prorate) በፕሮጀክት ዋጋ በማብዛት ይሆናል፡፡

## 26. የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮች ስለመቅጠር

ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ ለማካሄድ የሚፈለግ ሰው ፈቃድ ያለውና የፈቃድ ዘመኑ የታደሰ የሥራ ተቋራጭ መቅጠር ይኖርበታል፣

26.1 የግንባታ ባለሙያዎቹ የግንባታ ሥራ ለማከናወን የተመዘገቡና የሥራ ተቋራጭነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያላቸው መሆን አለባቸው፣

26.2 የግንባታው ባለቤት ግንባታውን የሚያካሂድለት ሥራ ተቋራጭ መቅጠር ያለበት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ባወጣው የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች እና ሥራ ተቋራጮች ምዝገባ መመሪያ መሠረት ይሆናል፣

26.3 የግንባታው ባለቤት ግንባታውን የሚያካሄድለትን የሥራ ተቋራጭ የገንቢ ግዴታ መግቢያ ቅጽ 012 በማስሞላት ለሕንፃ ሹሙ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

26.4 በማንኛውም የግንባታ ፕሮጀክት በተቋራጭ መመደብ ያለበት ባለሙያ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች እና ሥራ ተቋራጮች ምዝገባ መመሪያ መስፈርት ማሟላት አለበት፣

26.5 ማንኛውም በግንባታ ሥራ ላይ የተሠማራ ባለሙያ ሲቀየር የሥራ ተቋራጩ ለከተማ አስተዳደሩ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

26.6 የግንባታ ሥራውን ለማከናወን ውለታ የገባ የሥራ ተቋራጭ የግንባታ ሥራ ፈቃድ ቅጂ በግንባታ ቦታ ማስቀመጥ አለበት፣

26.7 ማንኛውም የተመዘገበና ሕጋዊ ፈቃድ ያለው የሥራ ተቋራጭ የግንባታ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የገንቢ ግዴታ ቅጽ 012 መሙላት አለበት፣

26.8 ማንኛውም ውል የገባ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ በውለታ ሰነዱ መሰረት ጥራቱ ተጠብቆ ግንባታው ለመከናወኑና በስራ ጥራትና ጉድለቶች ለሚደርሱ ጉዳቶች የግንባታው ስራ ከተጠናቀቀ በኂላ ቢያንስ ለ1 ዓመት የሚቆይ የጉዳት ማካካሻ ዋስትና በደንቡ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት እንደሚከተለው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

| ተ.ቁ | የሕንጻ ምድብ | የፕሮጀክት ግምት /ብር/ | የዋስትና መጠን (የፕሮጀክቱን ግምት) | የዋስትና መጠን ጣሪያ /ብር/ | የዋስትና ጊዜ | የዋስትና አቀራረብ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከሪል ኤስቴት ውጪ ያሉ የምድብ “ለ” ህንጻዎች | 10,000,000 | 20 በመቶ | 2000,000.00 | ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ 1ዓመት የሚቆይ | ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት |
| 2 | ለሪለል ኤስቴት እና ለምድብ “ሐ” ሕንፃዎች | 10,000,000 | 30 በመቶ | 300,000.00 | ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ 1ዓመት የሚቆይ | ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት |
| | | 15,000,000 | 25 በመቶ | 3,750,000.00 | | |
| | | 25,000,000 | 20 በመቶ | 5,000,000.00 | | |

## ክፍል ሶስት፡ የመሬት አጠቃቀም፣ ተጓዳኝ ጥናቶች እና ዲዛይኖች

### 27. የመሬት አጠቃቀም እና ተጓዳኝ ጥናቶች

27.1. ማንኛውም ግንባታ የከተማው ኘላን ያስቀመጠውን የሕንፃና የመሬት አጠቃቀም ንጽጽርን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፣

27.2. የአቪዬሽን ከፍታ ወሠን ባለባቸው ቦታዎች ከተወሠነው ሜትር ገደብ በላይ ምንም ዓይነት ግንባታ መፈቀድ የለበትም፡፡

27.3. ከወለል ከ1.7 ሜትር በላይ ከፍ ባለ ዝግ ወይም ተካፋች መስኮት በተገጠመለት በኩል ያለ ግንባታ ከወሰን ቢያንስ በ1.5 ሜትር ርቀት መገንባት አለበት፣ ከ1.7 ሜትር በታች መስኮት ያለው የግንባታ ገጽ ከወሰን ቢያንስ 2.0 ሜትር መራቅ አለበት፣

27.4. በአንድ የመኖሪያ ይዞታ ተነጣጥለው በተሰሩ ሁለት ብሎኮች ወይንም በከፊል በተያያዙ ሁለት ብሎኮች መካከል በትይዩ በተሠሩ ሁለት የግድግዳ ገጾች፣

27.4.1. አንዱ የግድግዳ ገጽ ከወለል በላይ ከ 1.7ሜትር በታች ተካፋች ካለው ቢያንስ 2 ሜትር፣

27.4.2. አንዱ የግድግዳ ገጽ መስኮት ከወለል በላይ ከ 1.7ሜትር በላይ ተካፋች ካለው 1.5 ሜትር መሆን ይኖርበታል ፡፡

27.5. በአንድ የመኖሪያ ይዞታ ተነጣጥለው በተሰሩ ሁለት ብሎኮች ወይንም በከፊል በተያያዙ ሁለት ብሎኮች መካከል በትይዩ በተሠሩ ሁለት የግድግዳ ገጾች ሊኖራቸው የሚገባ ርቀት፣

27.5.1. አንዱ የግድግዳ ገጽ ተካፋች ካለው ቢያንስ 2.5 ሜትር፣

27.5.2. በሁለቱም የግድግዳ ገጾች ተካፋዮች ቢያንስ 1.5 ሜትር ከፍተት መኖር አለበት፣

27.6. በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ ተግባር ያለው ማምረቻ ወይም ወርክሾፕ ሞተሩ ከወሰን ቢያንስ 6 ሜትር መራቅ አለበት፣

27.7. ከአንድ መንገድ በላይ አዋሳኝ ላላቸው ይዞታዎች ህንፃው ከመንገድ የሚኖረው ርቀት ከህንፃ የፊት ለፊት ገጽታ በኩል ወይም ከዋናው የመዳረሻ መንገድ በኩል ያለው በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 27.3 መሠረት  ሲሆን በሌሎች አዋሳኝ መንገዶች በኩል ያለው ማንኛውም የግንባታ አካል ወይም ተንጠልጣይ ወለል ጭምር፣

27.7.1. ከምድር በላይ እስከ 3 ወለል ላለው 1 ሜትር፣

27.7.2. ለከምድር በላይ ከ4 እስከ 5 ወለል ላለው 1.5 ሜትር፣

27.7.3. ከምድር በላይ ከ6 እና በላይ ወለል ላለው 2 ሜትር መራቅ ይኖርበታል፡፡

27.8. ከወለል ከ1.7 ሜትር በላይ ከፍ ባለ ዝግ ወይም ተካፋች መስኮት በተገጠመለት በኩል ያለ ግንባታ ከወሰን ቢያንስ በ1.5 ሜትር ርቀት መገንባት አለበት፡፡ ከዚህ ውጪ የትኛውም ዓይነት መስኮት ያለው የግንባታ ገጽ ከወሰን ቢያንስ 2 ሜትር መራቅ አለበት፣

27.9. በአንድ የመኖሪያ ይዞታ ተነጣጥለው በተሰሩ ሁለት ብሎኮች ወይንም በከፊል በተያያዙ ሁለት ብሎኮች መካከል በትይዩ በተሠሩ ሁለት የግድግዳ ገጾች ሊኖራቸው የሚገባ ርቀት፣

27.3.1. አንዱ የግድግዳ ገጽ ተካፋች ካለው ቢያንስ 2.5 ሜትር፣

27.3.2. በሁለቱም የግድግዳ ገጾች ተካፋዮች ቢያንስ 1.5 ሜትር ከፍተት መኖር አለበት፣

# 28. ዲዛይኖች

## 28.1. አጠቃላይ

28.1.1. ማንኛውም የህንጻ ዲዛይን የከተማውን መሪ ኘላን መሠረት በማድረግ ደህንነቱ የተረጋገጠ ሆኖ ዲዛይን መደረግ አለበት፣

28.1.2. ማንኛውም ሕንፃ ለሚገኝበት ምድብ የሚያስፈልጉ ፕላኖች በአንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ (25.1) መሠረት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፣

28.1.3. ማንኛውም ፕላን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የዲዛይን ንድፍ የወረቀት መጠን መሠረት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

A0 - 841 x1189 ሚ.ሜ፣

A1 - 841 x 594 ሚ.ሜ፣

A2 - 420 x 594 ሚ.ሜ፣

A3 - 297 x 420 ሚ.ሜ፣

## 28.2. **አርክቴክቸራል ዲዛይን**

28.2.1. ከዚህ በታች የተመለከቱት ንድፎች በአርክቴክቸራል ዲዛይን ተካተው እና አንዳስፈለጊነቱ ከሪፖርት ጋር ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

ሀ) የቦታ አቀማመጥ ኘላን (site plan)፣

በሳይት ፕላኑ ላይ በዋነኛነት መካተት ያለባቸው፤

- ሊሠራ / ሊሻሻል የታቀደውን ሕንፃ አቀማመጥ፣
- ሕንጻው ከወሰን ከመንገድና ከሌሎች ነባር ግንባታዎች ያለውን ርቀት፣
- የመዳረሻ መንገዱ ስያሜና ወደ ህንፃው መግቢያ አመልካች ምልክት ፣
- በይዞታው ላይ የነባር ግንባታ ካለ የነባር ግንባታው አቀማመጥ፣
- የተፈጥሮ መሬት ተዳፋት ኘላን (contour plan) እና የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ቦታ ወይም ከዋናው ፍሳሽ ቆሻሻ መስመር ጋር የሚያገናኝ ከሆነ የማስወገጃ መስመር እና በአቅራቢያ ያለው የመሠረተ ልማት አውታር ዓይነት፣
- የጣሪያ የተፋሰስ አቅጣጫ እና የተዳፋት መጠን እንዲሁም በልኬቱ የተጠቀሱ የመኪና ማቆሚያ፣ የሕዝብ መጠቀሚያ ተቋም ከሆነ የቆሻሻ እና የማቃጠያ ቦታና የሰሜን አቅጣጫ አመልካች ምልክት መካተት ይኖረባቸዋል፣

ለ) የወለል ኘላን (Floor Plan)፣

የሁሉም ወለሎች የወለል ኘላን መዘጋጀት አለበት፣ ፍፁም ተመሳሳይ ወለል ያላቸው (Typical floor) በሚል ተጠቅለሎ ሊቀርብ ይችላል፣ የቆጥ ወለል (mezzanine floor) ካለ ለብቻው መታየት አለበት፣

ሐ) የተቆረጠ የቁም ኘላን (Section)፣

የተቆረጠ የቁም ኘላን (Section) ቢያንስ የጣሪያ ውቅር፣ የምድር በታች ወለል፣ ሁለትና ከዚያ በላይ ያሉ ወለሎችን የሚያገናኝ ክፍተት (open wall) እና የመወጣጫ ደረጃ የሚያሳይ መሆን አለበት ።

መ) የውጭ ገፅታ ኘላን (Elevation)

የውጭ ገፅታ ኘላን የሁሉንም የህንፃ ገፅታዎች የሚያሳይ መሆን አለበት። ሙሉ በሙሉ የማይታይና በሌላ ሕንፃ የተሸፈነ የውጭ ገፅታ በተቆረጠ የቁም ገጽታ ኘላን (Sectional Elevation) መታየት አለበት፣

ሠ) ግልፅ ባልሆኑ እና ተጨማሪ የጎላ ንድፍ በሚጠይቁ የዲዛይን አካላት ላይ ዝርዝር ፕላን (Detail plan) መዘጋጀት አለበት።

ረ) ከላይ በ ለ፣ሐ እና መ ለተገለጹት የወለል ከፍታቸው ከተፈጥሮ ምድር በላይ ወይም በታች መመልከት አለበት፣

## 28.3. ስትራክቸራል ዲዛይን

ከዚህ በታች የተመለከቱት በስትራክቸራል ዲዛይን፣ ንድፍ፣ ስታቲካል ትንታኔ እና የአፈር ምርመራ ጥናት ተካትተው መቅረብ ያለባቸው፣

### 28.3.1. የሶሌታ ዲዛይን ንድፍ፣

ሶሌታውንና ሶሌታው የሚኖረውን የብረት አቀማመጥ በኘላን እና በሁለቱም የቁም አቅጣጫ የሚያሳይ ንድፍ እና የብረት መጠን፣ ርዝመት፣ ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ (Bar schedule) የሚገልጽ መሆን አለበት፣

### 28.3.2. የወጋግራ (Beam) ዲዛይን ንድፍ

ወጋግራው የሚኖረውን የብረት አቀማመጥና በሁለቱም የቁም እና አግድም አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍና የብረት መጠን መግለጫ ሰንጠረዥ የያዘ መሆን አለበት፣

### 28.3.3. የኮለም ዲዛይን ንድፍ፣

የኮለም አግድማዊ ቁርጥ እይታ (Horizontal cross section) እና ኮለሙ የሚኖረውን የብረት አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ እና የሚኖረውን የብረት መጠን፣ ርዝመት፣ ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የሚገልፅ መሆን አለበት፣

### 28.3.4. የመሠረት ዲዛይን ንድፍ፣

ለየመሠረቱ ዓይነት የኘላን፤ የቁም ገጽታ እና መሠረቱ የሚኖረውን የብረት አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ እንዲሁም የሚኖረውን የብረት መጠን ርዝመት ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የያዘ መሆን አለበት፣

28.3.5. **ክብደት ተሸካሚ ግድግዳ** (shear wall)፣

የአርማታ ግድግዳ እንዲኖረው በሚገደድበት የህንፃ አካል በአግድማዊ ዕይታ (Horizontal cross section) እና ግድግዳው የሚኖረው የብረት አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ እና የሚኖረውን የብረት መጠን፣ ርዝመት ርቀትና ብዛት መግለጫ ሰንጠረዥ የሚገለፅ መሆን አለበት፣

28.3.6. **ደጋፊ ግንብ** (Retaining wall)፣

ደጋፊ ግንብ እንዲኖረው በሚገደድበት የሕንፃ አካል የአግድምና የቁም ገፅታ (Horizontal vertical cross section) እና ግንቡ የሚኖረውን አቀማመጥ ስፋትና መጠን የሚያሳይ ንድፍ እና የአርማታ ግድግዳ ከሆነ የሚኖረውን የብረት መጠን ርዝመት ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የሚገልፅ መሆን አለበት፣

28.3.7. **የተገጣጣሚ አካላት ንድፍ**፣

በተገጣጣሚ የሕንፃ አካላት ለሚሠራ ህንፃ የሁሉም የህንፃ አካላት ፕላንና የመገናኛ ዝርዝር ፕላን (Detail plan) መዘጋጀት አለበት፣

28.3.8. **የጣሪያ ከንች ውቅር**፣

የከንች ኘላን የቁም ገፅታና ከተሸካሚ መዋቅሮች ጋር ያለውን ትስስር የሚያሳይ ንድፍ የያዘ መሆን አለበት፣

28.3.9. **ሌሎች መዋቅራዊ ይዘት ያላቸው የግንባታ ክፍሎች ለምሳሌ ደረጃ፣ ፍሳሽ ማጠራቀሚያ፣ ውሃ መጠራቀሚያና መስቀያ ወዘተ አቀማመጥ ስፋትና መጠን የሚያሳይ ንድፍ እና የአርማታ ግንባታ ከሆነ የሚኖረውን የብረት መጠን፣ ርዝመት፣ ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የያዘ መሆን አለበት፡፡**

28.3.10. **ፍዘታዊ ስሌት** (statical calculation)

ለአንድ ኘሮጀክት ዲዛይን ምርመራ የሚቀርብ ስታቲካል ስሌት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

ሀ) የግንባታውን ዲዛይን አጠቃላይ መነሻና ታሳቢዎችን የሚዘረዝር መግቢያ ያለው፣

ለ) ለዲዛይን የተጠቀመበትን የህንፃ ኮድ ስታንዳርድ የሚጠቅስ፣

ሐ) የሁሉም የግንባታ አካላት ስታቲካል ስሌት statical Calculation የሚያሳይ፣

መ) ዲዛይኑ የተዘጋጀበት ፕሮግራም (Soft Ware) የሚጠቅስ መሆን ይኖርበታል፣

28.3.11. **የአፈር ምርመራ ውጤት**፣

የአንድ ኘሮጀክት የግንባታ ቦታ የአፈር ጥናት ተካሂዶ የሚቀርብ የላቦራቶሪ ውጤት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፣

ሀ/ ለምርመራ የሚጠቀምበትን የህንፃ ኮድ ማጣቀሻ፣

ለ/ የአፈር ምርመራና የመሸከም ውጤት መግለጫ፣

ሐ/ የመሠረት ዲዛይን ዓይነት አማራጭ ጥቆማ፣

መ/ ሌሎች የተለዩ ከምድር በታች ያሉ የህንፃ አካላት ዲዛይን አሠራር ጥቆማ የያዘ መሆን ይኖርበታል ፡፡

28.4. **ኤሌክትሪካል እና ሜካኒካል ዲዛይን**

ከዚህ በታች የተመለከቱት በኤሌክትሪካል ዲዛይን ጥናት ተካተው መዘጋጀት አለባቸው፣

28.4.1. የወለል ፕላኖች የኤሌክትሪክ ዲዛይን ንድፍ፣ የኤሌክትሪክ ገመድ የሚሳብባቸው ቱቦዎች፣ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮኒክስ ገመድ የሚዘረጋባቸው ምሰሶዎችና መብራቶች፣ የኤሌክትሪክ መስመር ጭነት ማጠቃለያና የሳይት ፕላን ጭነት መካተት አለበት፣

28.4.2. ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎችን የሚያካትት የኤሌክትሪካል ዲዛይን ሪፖርትና ማጣቀሻ ኮድ መገለጽ አለበት፣

28.4.3. የቦይለር (የውሃ ማሞቂያ፣ የአየር ማስተካከያ (air condition)፣ የአሳንሰር መግለጫ እንዲሁም ግፊት (pump) ዲዛይን ሪፖርትና መግለጫ መቅረብ አለበት፣

28.5. **የፍሳሽ ዲዛይን**

ከዚህ በታች የተመለከቱት በሳኒታሪ ዲዛይን ጥናት መካተት አለባቸው፣

28.5.1. የሁሉም ወለሎች የንፁህ ውኃ አቅርቦት ፕላን፣

28.5.2. የሁሉም ወለሎች የፍሳሽ ማስወገጃ ፕላን፣

28.5.3. የጣራ ፍሳሽ እና የዝናብ ውኃ ማስወገጃ ፕላን፣

28.5.4. የሳይት ሳኒተሪ ዲዛይን ፕላን (የውጭ ንፁህ ውሀ አቅርቦት፣ ፍሳሽ ማስወገጃ፣ ማጣሪያ የዝናብ ውሀ ማስወገጃ ያጠቃልላል)

28.5.5. የሁሉም ወለሎች የእሳት መከላከያ ፕላን፣

28.5.6. ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች የሚያካትት የሳኒተሪ ዲዛይን ሪፖርትና ማጣቀሻ ኮድ መገለጽ አለበት፡

28.6. **የእሳት መከላከያ ስርዓት ንድፍ**

የእሳት መከላከያ ስርዓት ንድፍ ከግንባታ ፈቃድ ሰነድ ጋር እንዲያቀርቡ ለሚጠየቁ ግንባታዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እና ሌሎች ተዛማጅ መስፈርቶች በዲዛይኑ መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

28.6.1. አጠቃላይ መስፈርት

ሀ/ የአደጋ ጊዜ መወጣጫ ደረጃ ፣በሮችና መተላለፊያዎች መጠንና ቀጥተኛነት ደረጃውን የጠበቀ እና ከመሰናክል ነፃ መሆን፣

ለ/ ግንባታው እሳትን መቋቋም ያለበት ሰዓት፣

ሐ/ ጠቋሚ ምልክቶች የሚተከሉበት ቦታና አይነታቸው (በቀን፣ በማታና መብራት በሌለበት ጊዜ ሊታይ የሚችለበት ሁኔታ በተገናዘበ መልኩ)፣

መ/ በየወለሉ የሚቀመጥ ውሃ መርጫ ጥቅል ከውኃ መርጫው ጋር የተገናኘ ውኃ ማጠራቀሚያ እና መብራት በማይኖርበት ጊዜ ሊኖር ስለሚገባው አማራጭ የኃይል ምንጭ፣

ሠ/ የአደጋ ጊዜ ማንቂያ ደወል፣

ረ/ የአደጋ ጊዜ መቆያ ክፍል፣

ሰ/ በግድግዳ ላይ የሚንጠለጠሉ ተንቀሳቃሽ እሳት ማጥፊያዎች አቀማመጥና ከግንባታው አገልግሎት አንፃር ሊነሳ ከሚችለው እሳት ዓይነት ጋር ያለው አግባብነት፣

ሸ/ መብረቅ መከላከያ፣

ቀ/ የመገልገያ ቁሳቁሶች አቀማመጥና የተሰሩበት ቁስ ደረጃ በአደጋ ጊዜ ሊደረስ የሚችለውን አደጋ የሚያባብስ አለመሆኑን ማረጋገጫ፣

በ/ ለምግብ ማብሰያ ክፍል፣ ቦይለር ክፍልና ወርክሾፕ ከዋናው ግንባታ በተለየ የሚደረግ ጥንቃቄ፣

28.6.2. ከላይ በአንቀፅ 28 ንዑስ አንቀፅ 28.6.1 ከተገለፁት በተጨማሪ ለማምረቻና ማከማቻ ተቋማት፣

ሀ/ የመውጫ በሮች ቁጥር የሠራተኛ ብዛት እና የአጠቃላይ ግንባታው ወለል ስፋት መጠን፣

ለ/ እንደማምረቻ ወይም ማከማቻው ባህርይ ጪስ ጠቋሚ፣ ነበልባል ጠቋሚ፣ ሙቀት ጠቋሚ፣ መሣሪያዎች መታየት፣

ሐ/ እንደ ማምረቻ ወይም ማከማቻው ባህርይ በራሱ ጊዜ የሚሰራ የውሀ መርጫ /sprinkler/ እና የአደጋ ጊዜ ማንቂያ ደወል ሊኖረው ይገባል ፡፡

28.6.3. ከላይ በአንቀፅ 28 ንዑስ አንቀፅ 28.6.1 ከተገጹት በተጨማሪ የፈሳሽ ነዳጅና ቡታ ጋዝ ማከማቻ ተቋም

ሀ/ fixed foam installation ያላቸው፣

ለ/ ከሌሎች ተቋማት በተናጠል የተገነባ፣

ሐ/ እሳትን ለመከላከል በራሱ ጊዜ የሚሰራ የውሀ መርጫ (sprinkler)፣

መ/ የፈሳሽ ነዳጅ ቃጠሎ ማጥፊያ ኬሚካል (foam Compound & foam Monitor - trailer)፣

ሠ/ የእሳት አደጋውን ለመከላከል የሚችል በቂ የውኃ ማጠራቀሚያ ጋን ከመጠባበቂያ የኃይል ምንጭ አቅርቦት ጋር፣

ረ/ የአካባቢ የፍሳሽ መስመር ከግቢው ከሚወጣ የፍሳሽ ነዳጅ መጠበቂያ ማካተት ይኖርበታል፡፡

## 29. አርክቴክቸር ወይም ሥነ ሕንፃ

### 29.1. አጠቃላይ

29.1.1. የሕንፃ ዲዛይኖች ከሕንፃ አዋጁ ደንብና መመሪያው ጋር የተገናዘበ መሆን ይኖርበታል፣

29.1.2. የማንኛውም ህንፃ ፕላኑ ሲሠራ ተቀባይነት ያላቸውን ስታንዳርድ መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፣

29.1.3. የዲዛይን ፕሮግራም ሲዘጋጅ የአሰሪውን ፍላጐት የሚሰጠውን አገልግሎት እና ለፕሮጀክቱ የተያዘውን በጀት /አቅም/ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፣

29.1.4. በዲዛይን ዝግጅት ህንጻው ሊሰጠው የታሰበው አገልግሎትና የቦታ አጠቃቀም ኢኮኖሚያዊነትንና አዋጪነትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፣

29.1.5. ለማንኛውም ሕንፃ እንዲገጠም የሚመረጥ አሣንሠር መወሰን ያለበት የተጠቃሚውን ቁጥር፣ የአገልግሎት ዓይነት እና ምቹነትን መሠረት በማድረግ ይሆናል፣

29.1.6. የፕላን አግድም ልኬት የሚነሳው ካልተለሰነው ግድግዳ ጠርዝ ነው፣

29.1.7. የወለል ስፋት በግድግዳ የተያዘውንና በተቀባሪ ቁምሳጥን የተያዘውን ቦታ አያካትትም፣

### 29.2. የክፍል ስታንዳርድ

29.2.1. ማንኛውም የክፍል ስፋት ከ6 ካ.ሜትር ማነስ የሌለበት ሲሆን የየትኛውም ግድግዳ ወርድ ከ2 ሜትር ማነስ አይችልም፡፡ሆኖም የመጸዳጃ ፣ልዩ የአገልግሎት አይነት ያላቸውና በሚገጠምላቸው መሳሪያ ባህሪ ስፋታቸው የሚወሰን ክፍሎች ከ6 ካሬ ሜትር ስፋትና ከ 2ሜ ወርድ አንሰው ሊሰሩ ይችላሉ፣

29.2.2. ከወለል እስከ ኮርኒስ ያለው አነስተኛው የክፍል ቁመት ከ2.5 ሜትር ማነስ የለበትም ሆኖም ሊኖር የሚገባውን የክፍል ቁመት እንደአካባቢው የአየር ፀባይና አንደ አገልግሎቱ እንዲሁም የወለል ስፋቱ የሚወሰን ይሆናል፣

29.2.3. ስላሽ ኮርኒስ ላላቸው ክፍሎች ሰው ሊጠጋበት በሚችልበት በዝቅተኛው በኩል ያለው የክፍል ቁመት ከ2.0 ሜትር ማነስ የለበትም፣

29.2.4. መኝታ ክፍል ለአንድ ሰው 6 ካሬ ሜትር ሲሆን እንደ ሳሎን የሚያገለግል ከሆነ ከ12 ካሬ ሜትር ማነስ የለበትም፣

29.2.5. የቤት ውስጥ የመኪና ማቆሚያ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የመኪና ማቆሚያው ዝቅተኛ የክፍል ቁመት ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይሆናል፣

1. እስከ 10 ለሚደርሱ መኪናዎች 2.10 ሜትር፣
2. ከ10 እስከ 30 ለሚደርሱ 2.30 ሜትር፣
3. ከ30 እስከ 70 ለሚደርሱ 2.50 ሜትር፣
4. ከ70 በላይ 2.60 ሜትር፣

29.2.6. የቆጥ ወለል ክፍል ቁመት ዝቅተኛው 2.1 ከፍተኛው 2.7 ሜትር መሆን ይኖርበታል። ሆኖም የወለሉና የቆጥ ወለሉ የክፍል ቁመት አጠቃላይ ድምር ከ6 ሜትር ከበለጠ እንደ ሁለት ወለል ይታሰባል፣

29.2.7. የክፍል ቁመት ከ6 ሜትር በላይ የሆነ ግንባታ ወለል ብዛት የሚሰላው የክፍሉን አጠቃላይ ቁመት ለ3 በማካፈልና የሚገኘውን ውጤት ወደ ዝቅተኛው ስሌት በማስጠጋት ይሆናል፣

29.2.8. የጣሪያ ላይ ክፍሎች ወለል ስፋት የደረጃ መወጣጫ እና የአሳንሰሩን ወለል ስፋት ድምር ሳይበልጥ ሌሎች ለህዝብ አገልግሎት መስጫነት የማይውሉ ክፍሎች ሊኖሩት ይችላል፣ ከዚህ ስፋት በላይ ክፍሎች ያሉት የጣሪያ ወለል እንደ አንድ ወለል ይታሰባል፣

29.2.9. ማምረቻ ወይም ማከማቻ ወይም የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ ከሆኑ ግንባታዎች ውጭ የዛኒጋባ ጣሪያ ከፍታው (ክፈፍ ሳይጨምር) ከ2.8 ሜትር በላይ የሆነ ጣሪያ እንደ አንድ ወለል ይታሰባል፣

29.3. **የተካፋች ስታንዳርድ**

29.3.1. ማንኛውም ተካፋች ከይዞታ ወደ ውጭ መከፈት አይችልም፣

29.3.2. ወደ ግቢ መግቢያ ቢያንስ ለመኖሪያ 3 ሜትር ለሌሎች 4 ሜትር መጠበቅ ይኖርበታል፣

29.3.3. ከወለል ከ1.7 ሜትር በላይ ከፍ ብሎ ዝግ ወይም ተከፋች መስኮት በተገጠመለት በኩል ያለ ግንባታ ከወሰን ቢያንስ 1 ሜትር ርቅት መገንባት አለበት፣

29.3.4. በልዩ ባሕሪያቸው ተካፋች እንዳይኖራቸው ከሚፈለጉ ክፍሎች በስተቀር ለእያንዳንዱ ክፍል ቢያንስ አንድ በር እና አንድ አየርና ብርሃን ማስገቢያ መስኮት ወይም የተያያዙ አንድ በርና መስኮት መኖር አለበት፣

29.3.5. ለመጸዳጃ ቤት፣ ለሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ ለቤት ውስጥ መጫወቻ አዳራሽ፣ ለዕቃ ማሳያና መሸጫ እና ለመሳሰሉት ለሕዝብ መጠቀሚያ አገልግሎቶች አየርና ብርሃን የሚያገኙበትን ሜካኒካል አማራጮችን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ የአየር ማስተንፈሻ መስመር (Ventilation Duct) በዝርዝር መመልከት እና የAir conditioner መስመር ከመጠባበቂያ የሃይል አቅርቦት ጋር የተሟላ መሆኑን በዲዛይኑ ላይ በግልጽ መታየት ይኖርበታል፣

29.3.6. የመፀዳጃና ባልኮኒ የበር ስፋት ከ70 ሳ.ሜ እንዲሁም ቁመት ከ200 ሳ.ሜ ያነሰ መሆን የለበትም፣

29.4. **የመታላለፊያ ስታንዳርድ**

29.4.1. ማንኛውም ከአንድ ሰው በላይ የሚተላለፍበት ኮሪደር፣ ደረጃ ወይም ራምፕ የጎን ስፋቱ ለሕንፃ ምድብ "ሀ" እና "ለ" ለመኖሪያ 90 ሳ.ሜ ለምድብ "ሐ" ሕንፃዎች ከ120 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፣ የተጣራ የክፍሉ ቁመት ከ200 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፣

29.4.2. የመወጣጫ ደረጃ መርገጫ እና መወጣጫ ምጥጥን መጠበቅ ያለበት ሲሆን መርገጫው ከ25 ሳ.ሜ ማነስ እንዲሁም መወጣጫው ከ20 ሳ.ሜ ከፍታ መብለጥ የለበትም፣

29.4.3. በአንድ ተከታታይነት ባለው የመወጣጫ ደረጃ የተለያዩ የመርገጫ ስፋት ወይም የመወጣጫ ከፍታ መጠን መጠቀም አይቻልም፣ ሆኖም ወደ ውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ወይም ወደ ማሽን ክፍል ወይም ለተመሳሳይ አገልግሎት ለዋሉ ክፍሎች የሚያደርስ ደረጃ ከሆነ ከተጠቀሰው መጠን የተለየ ሊሆን ይችላል፣

29.4.4. ለሕዝብ አገልግሎት የሚውል አሳንሰር ስፋት ከ90 ሳ.ሜ፣ ወርድ ከ150 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፣

29.4.5. ለሕዝብ አገልግሎት የሚውል ህንፃ የምድር ወለል በተሽከርካሪ ወንበር ለሚንቀሳቀሱ አካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆን ከ4.5% ያልበለጠ ተዳፋት የramp መወጣጫ መኖር አለበት፣

29.5. **በርና መስኮት**

29.5.1. የመስኮት ስፋት ከክፍሉ ስፋት ቢያንስ 10% መሆን ያለበት ሲሆን ዝቅተኛው ከ0.2 ሜ.ካ ማነስ የለበትም፣

29.5.2. የበር ስፋት የተጣራ 70 ሳ.ሜ እና ቁመት የተጣራ 200 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፣

29.5.3. የፊት መስታወት ዓይነት (mirror glass) ወይንም ተመሳሳይ ውጤት እንዲኖረው የተደረገ መስታወት ለግንባታ የውጭ አካል አገልግሎት መጠቀም አይቻልም፣

29.5.4. በህንፃ ላይ ለሚገጠሙ የውጭ መስኮቶች አንፀባራቂነት የነዋሪውን ደህንነትና የትራፊክን እንቅስቃሴ የሚያውክ መሆን የለበትም፣

29.5.5. ለህዝብ አገልግሎት ለሚውል ህንፃ ዋና መግቢያ በር ስፋት ከ150 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፣

29.5.6. አየር ማስገቢያ ሳይኖረው ብርሃን ብቻ የሚያስገባና በተጎራባች ወሰን ላይ ስለሚሰራ ግንባታ ውፍረታቸው ከ5 ሳ.ሜ የማንያስ የመስታወት ብሎኬቶችን መጠቀም የሚችል ሲሆን ይህም በሚቀርበው ዲዛይን ላይ በግልጽ መጠቀስ ይኖርበታል፣

29.5.7. የኩሽና፣ የሳሎን እና የመኝታ ክፍል የበር ስፋት ከ80 ሳ.ሜ ቁመት ከ2.0 ሜ. ማነስ የለበትም፣

29.6. **የመኪና ማቆሚያ ስታንዳርድ**

ለማንኛውም ተሽከርካሪ የማቆያ ቦታ እንደ ከተማው ዕድገት እና መልካምድራዊ አቀማመጥ በከተማው አስተዳደር ተጠንቶ በሚዘጋጅ መመሪያ መሠረት ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፣

29.7. **ባልኮኒ**

ሀ) የባልኮኒ መደገፊያ የፍርግርጉ ስፋት ከ0.11 ሜትር መብለጥ የለበትም፣ መደገፊያ ቁመቱ ከ1.05 ሜትር ማነስ የለበትም፣

ለ) በባልኮኒ አካባቢ የሚፈጠርን ፍሳሽ አወጋገድ በዲዛይኑ ላይ መመልከት አለበት፡፡

29.8. **ኮሪዶር፣ የውስጥ ደረጃ**

29.8.1. ኮሪደር ለመኖሪያ ቤት ከ 90 ሳ.ሜትር ያነሰ መሆን የለበትም፣

29.8.2. የደረጃ ስፋት ለውስጥ ደረጃዎች ከ0.75 ሜትር ማነስ የለበትም፣

29.8.3. የውስጥ ደረጃ ስፋት (thread) ከ25 ሣንቲ ሜትር ማነስ ከ30 ሣንቲም ሜትር መብለጥ የለበትም፣

29.8.4. የውስጥ ደረጃ ቁመት (riser) ከ20 ሣንቲ ሜትር መብለጥ የለበትም፣

29.9. **የአጥር ስታንዳርድ**

29.9.1. የአጥር ከፍታ የሚለካው ከተፈጥሮ የምድር ወለል ጀምሮ ነው፣

29.9.2. በሁለት አዋሳኞች መካከል የሚገነባው አጥር ከፍተኛው የግንብ ቁመት 2.5 ሜትር መብለጥ የለበትም፣

29.9.3. ከዋና መንገድ የሚዋሰን አጥር ወደ ውስጥ በሚያሳይ ቁስ ወይም ግንብ ከተሠራ ቁመቱ ለመኖሪያ 1.50 ሜትር፣ ለድርጅት 90 ሳ.ሜ ያልበለጠ ሆኖ ቢያንስ 75% ወደ ውስጥ በሚያሳይ ቁስ እስከ 2 ሜትር ከፍ ማድረግ ይቻላል፣

29.9.4. ለመኖሪያ ከዋና መንገድ በኩል በሚዋሰነው እስከ 70 ሳ.ሜ ቢያንስ 75% ወደ ውስጥ በሚያሳይ ቁስ እስከ 1.5 ሜትር ከፍ ማድረግ ይቻላል፣

29.9.5. ለቢሮ እና ለሌሎች የንግድ ተቋማት 70 ሳ.ሜ መብለጥ የለበትም፣

29.9.6. ለማምረቻ፣ ማከማቻ እና ማህበራዊ ተቋማት 80% ወደ ውስጥ በሚያሳይ ቁስ በመገንባት እስከ 1.5 ሜትር ከፍ ማድረግ ይቻላል፣

29.9.7. ለኢምባሲዎች እና ዲኘሎማቲክ ተቋማት እስከ 2.5 ሜትር በድፍን ቁስ መሥራት የሚቻል ሲሆን ተቋሙ በሚያቀርበው የደህንነት መጠባበቂያ ዘዴ ምርጫ እስከ 3 ሜትር ከፍታ መሸፈን ይቻላል፣

29.10. **ቆሻሻ ማስወገጃ** (Garbage chute)

29.10.1. ከአምስት ፎቅ በላይ ለሚገኙ ሕንፃዎች የደረቅ ቆሻሻ ማስወጃ (Garbage chute) መሠራት አለበት፣

29.10.2. ቆሻሻ ማስወገጃ (Garbage chute) ከመኝታ እና ከሳሎን መገናኘት የለበትም፣ የቆሻሻ ማስወገጃው የሚሠራበት ቁስ ዝገት የሚቋቋም መሆን አለበት፡፡

29.10.3. ማንኛውም የቆሻሻ ማስወገጃ የቆሻሻ መቀበያ ሊኖረው ይገባል፡፡

29.10.4. የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ ለምድብ ሐ ሕንፃ በሳይት ኘላኑ ላይ መታየት ይኖርበታል፡፡

29.11. **አሳንሳር (ሊፍት)**

29.11.1. ከ12 ወለል በላይ ከፍታ ላላቸው ሕንጻዎች ቢያንስ ሁለት አሳንስር መገጠም ይኖርበታል፣

29.112.2. ረጅም ሕንፃ እና ኮሪዶር ያለው ሕንፃ የአሳንሳር አቀማመጥ ማዕከላዊነት የያዘ መሆን አለበት፣

## 30. ስትራክቸር/ውቅር

30.1. የማንኛውም ሕንፃ ውቅር በዲዛይን ደረጃ አስፈላጊ የሆኑና ተቀባይነት ያላቸው የዲዛይን መስፈርቶችን ተመርኩዞ ጠንካራ፤ ምቹ እና አስተማማኝ ሆኖ በመገንባት ያለምንም ሥጋት የሚጠበቀውን አገልግሎት ለተጠቃሚዎች መስጠት አለበት፣

30.2. ስትራክቸር ወይም ውቅር በአገልግሎት ዘመኑ፣

30.2.1. ንፋስ፣ ርእደ መሬት እና የእሣት ቃጠሎን የሚቀቋም:

30.2.2. ከመሸከም አቅሙ መጠን በላይ ክብደት ካለተጫነው በስተቀር ምንም ዓይነት አደጋን እንዲቋቋም ተደርጎ መጠናትና መገንባት አለበት፣

30.3. የመዋቅር ዲዛይን ከአርክቴክቸራል ዲዛይን ጋር መጣጣሙ በቅድሚያ በዲዛይን ወቅት መረጋገጥ ይኖርበታል፣

30.4. የተለያዩ የስትራክቸራል አካላት የአርማታ ሽፋን ውፍረት እንዲሁም የክብደቶች ቅንጅት በአግባቡ መወሰን አለበት፣

30.5. ከአርክቴክቸራል ኘላኑና ከክፍሉ አገልግሎት ከሚሸከመው ክብደት ጋር የኮለሙ፣ የሶሌታና የቢሙ ውፍረትና አቀማመጥ የተገናዘበ መሆን ይገባዋል፣

30.6. የጣራ ውቅር የራሱን ክብደትና የነፋስ ግፊትን እንዲቋቋም ታስቦ ዲዛይኑ መዘጋጀት አለበት፣

30.7. ስትራክቸራል ኘላኖች በስታስቲካል ስሌቱ መሠረት ንድፋቸው መዘጋጀት ይኖርበታል፣

## 31. ሳኒተሪ

31.1. በሕንፃ ላይ ላሉ የመፀዳጃ፣ የመታጠቢያ እና የመገልገያ ክፍሎች በሕንፃ ኮዱ ስታንዳርድ መሠረት በቂ የውሀ አቅርቦት ከነመጠባበቂያው ታስቦ ዲዛይኑ መዘጋጀት ይኖርበታል፣

31.2. የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች መጠን ተቀባይነት ያለውን የስታንዳርድ መስፈርት የተከተለ መሆን አለበት፣

31.3. የሕዝብ መፀዳጃ ግንባታ ከወሰን 2.5 ሜትር ርቆ መገንባት አለበት፣

31.4. የመኖሪያ ቤት መፀዳጃ ከመታጠቢያ ጋር መዘጋጀት አለበት፣

31.5. ለንግድ፣ ለቢሮ፣ ለማምረቻ፣ ማከማቻ እና ለጋራዥ የግንባታ ዓይነት ቢያንስ 4 መፀዳጃና መታጠቢያ መዘጋጀት ይኖርበታል (በ የ500 ሜትር ካሬ ስፋት)፣

31.6. ለትምህርትና ጤና ተቋማት በየ500 ሜትር ካሬ ስፋት 2 መፀዳጃና መታጠቢያ መዘጋጀት ይኖርበታል፣

31.7. ለአዳራሽነት ለመሳሰሉት በ 500 ሜትር ካሬ ስፋት 4 መፀዳጃና እንደ አስፈላጊነቱ መታጠቢያ ሊዘጋጅ ይገባል፣

31.8. የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ከጣሪያው ከፍታ አንድ ሜትር ከፍ ማለትና ከወሰን ቢያንስ 1 ሜትር መራቅ ይኖርበታል፣

## 32. ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ

32.1. ኤሌክትሪካል ዲዛይን ሲዘጋጅ፤

32.1.1. መብራቶቹ ህንጻው ሊሰጠው ከታሰበው አገልግሎት አንፃርና የክፍሎቹ አቀማመጥ በቂ የብርሀን አቅርቦት፣

32.1.2. በክፍሉ ውስጥ በኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ለሚሠጡ መገልገያዎች በቂ የኃይል አቅርቦት መኖሩ በዲዛይን ወቅት መረጋገጥ ይኖርበታል፣

32.2. የኤሌክትሪክ ዲዛይኑ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ የደህንነት ህግ /Safety Rule/ እና የኤሌክትሪክ ዲዛይን ኮዱን መከተል አለበት፣

32.3. ማንኛውም ለሕንፃ ውስጥ ዝርጋታ የሚውሉ የኤሌክትሪክ ቁሳቁሶች የጥራት ደረጃቸውን በጠበቁ ቁሳቁስ መሆን ይኖርበታል፣

32.4. በሕንፃው ላይ የሚገጠሙ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎች የጥራት ደረጃ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠና የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፣

32.5. ማንኛውም የኤሌክትሪክ ዕቃ ዲዛይኑን ባዘጋጀው ባለሙያ/በሚመለከተው አካል ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል፣

32.6. የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ የኤሌክትሪክ ቁሳቁሶች መሆናቸውን ከግንባታ ቦታ ናሙና በመውሰድ ፍተሻ መደረግ ይኖርበታል፣

32.7. ማንኛውም የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታም ሆኑ ቁሳቁሶች በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፣

## 33. ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ ዝግጅቶች

በማንኛውም በሕንፃ ምድብ “ሐ” የሚገኙ የሕዝብ መገልገያ ሕንፃዎች የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝቅተኛ መስፈርትን የሚያሟሉ እና አመቺ መዳረሻዎች ሊኖራቸው ይገባል፡፡

### 33.1. አጠቃላይ

33.1.1 ማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ በሚሆን መልኩ መገንባት ወይም አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች ሊሟላለት ይገባል፣

33.1.2 በተሽከርካሪ ወንበር ለሚጠቀሙ፣ ማየት ለተሣናቸው እንዲሁም በከፊል ለተጐዱ አካል ጉዳተኞች ወደ ህንፃው መዳረሻ ከእንቅፋት የፀዳ መንገድ ሊዘጋጅ ይገባል፣

33.1.3 በማንኛውም የህዝብ መገልገያ ሕንፃ ውስጥ የሚገኝ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተሽከርካሪ ወንበር ወይም በክራንች የሚንቀሳቀሱ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ የመቀመጫ ቦታ በስታንዳርዱ መሠረት ሊዘጋጅ ይገባል፣

33.1.4 ፋብሪካዎች እና የትምህርት ተቋማት፣ የማምለኪያ ቦታ፣ የገበያ ማዕከል ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች የልብስ መቀየሪያና የመፀዳጃ ክፍል ሊኖራቸው ይገባል ፣

### 33.2 ደረጃዎች

33.2.1 መወጣጫ ደረጃዎች በሁለቱም ጎኖች የእጅ መደገፊያ ሊኖራቸው ይገባል፣

33.2.2 የእጅ መደገፊያዎች ከፍታቸው ከወለል በላይ ከፍተኛው 90 ሳ.ሜ ዝቅተኛው 70 ሳ.ሜ ሆኖ ከተዳፋቱ መዳረሻ ቢያንስ 30 ሳ.ሜ አልፎ የተዘረጋ መሆን ይኖርበታል፣

33.2.3 የመወጣጫዎች ደረጃ ስፋት ከ3 ሜትር በላይ ከሆነ በመሃሉ የእጅ መደገፊያ (Handrail) ሊኖረው ይገባል፣

33.2.4 የደረጃዎች መርገጫ ስፋት ከ30 ሳ.ሜ ያላነሰ ከፍታው ከ15 ሳ.ሜ ያልበለጠ መሆን አለበት፣

33.2.5 የደረጃዎች የወለል መርገጫ ከማያንሸራትት ቁስ መሰራት ይኖርበታል፣

### 33.3 ተዳፋት (Ramp)

33.3.1 ማንኛውም ተዳፋት ወይም ራምፕ ተዳፋቱ ከ10% ያልበለጠ ሆኖ ከዋናው ወለል ማከፋፈያ መተላለፊያ (Lobby) ወይም የወለል መዳረሻ ጋር መገናኘት ይኖርበታል፣

33.3.2 የተዳፋቱ መተላለፊያ ጠንካራ ወይም የማይለመጥ እና ከማያንሸራትት ቁስ የተሰራ ሆኖ ከማንኛውም ከሚጋርዱ ነገሮች ነፃ መሆን ይገባዋል፣

33.3.3 ከተዳፋቱ ግራና ቀኝ 45 ሳ.ሜ ያላነሰ ከፍታ ያለው መከለያ ሊኖረው ይገባል፣

33.3.4 የተዳፋቱ የእጅ መደገፊያ ከፍታ ከወለል በላይ ከፍተኛው 90 ሳ.ሜ ዝቅተኛው 70 ሳ.ሜ ሆኖ ከተዳፋቱ መዳረሻ ቢያንስ 30 ሳ.ሜ አልፎ የተዘረጋ መሆን ይኖርበታል፣

33.3.5 የተዳፋቱ ስፋት ከ3 ሜትር በላይ ከሆነ አካፋዩ ላይ ተጨማሪ የእጅ መደገፊያ (Handrail) ሊኖር ይገባል፣

33.3.6 በማንኛውም የተዳፋት መዞሪያ/መታጠፊያ ቦታ አንድ ዓይነት የወለል ከፍታ እና 1.50 ሜትር በ1.50 ሜትር ስፋት ያለው ማረፊያ ቦታ መዘጋጀት ይኖርበታል፣

## 33.4 አሳንሰር

33.4.1 በአንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 33.1.1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከ4 ፎቅ በታች ለአገልግሎቶቹ ተደራሽ የሆነ የተመቻቸ ሁኔታ በሌለበት እና ከ4 ፎቅ በላይ ለሚኖራቸው የሕዝብ መገልገያ ሕንፃዎች ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች አሳንሰር በሕንፃው ውስጥ መገጠም ይኖርበታል፣

33.4.2 የማንኛውም አሳንሰር በር ስፋት ከ90 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፣

33.4.3 ማንኛውም አሳንሰር ከምድር ወለል (Ground floor) የሚነሳ እና ወደ ሁሉም ወለሎች የሚያደርስ መሆን አለበት፣

33.4.4 አሳንሰሩ በሦስቱም የግድግዳ ክፍል በኩል የእጅ መደገፊያ ሊኖረው የሚገባ ሆኖ መደገፊያው ከወለል በላይ ከ80 ሳ.ሜ እስከ 85 ሳ.ሜ ከፍታ ያለው መሆን ይኖርበታል፣

33.4.5 አሳንሰሩ የመጥሪያ ደወል ከወለል ከ90 ሳ.ሜ እስከ 110 ሳ.ሜ እንዲሁም ከግድግዳው ጠርዝ 40 ሳ.ሜ ርቆ የተቀመጠ ሊሆን ይገባል፣

33.4.6 አሳንሰሩ ማየት ለተሳናቸው የአካል ጉዳተኞች አመቺ በሚሆን መልኩ የበር መዘጋትና መከፈት እና የወለል ከፍታን በድምጽ የሚገልጽ መሣሪያ የተገጠመለት እንዲሁም የውስጥ እና የውጭ መጥሪያ ደወል የብሬል ጽሑፍ ያለበት መሆን ይኖርበታል፣

33.4.7 የአሳንሰሩ የውስጥ ርዝመት/ጥልቀት ከ1.30 ሜትር እና የተጣራ ስፋት ከ1 ሜትር ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፣

## 33.5 መግቢያ

33.5.1 የማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ደፍ የወለል ከፍታ ልዩነት ካለው የተዳፋት መወጣጫ መዘጋጀት ይኖርበታል፣

33.5.2 በሕንፃ መግቢያ በኩል ያለው ኮሪዶር ስፋት ከ1.50 ሜትር ያነሳ መሆን የለበትም፣

33.5.3 የሕንፃው ወለል ከማያንሸራትት ቁስ የተሰራ ወይም ክወለል የተያያዘ ምንጣፍ ያለው መሆን ይኖርበታል፣

33.6 በር

33.6.1 በማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ውስጥ የሚገኙ በሮች ስፋት ከ85 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፣

33.7 መፀዳጃ

33.7.1 ለአንድ የህዝብ መገልገያ ሕንፃ ቢያንስ አንድ መፀዳጃ ከአንድ መታጠቢያ ጋር መግቢያ በር አካባቢ ሊዘጋጅለት ይገባል፣

33.7.2 የመፀዳጃ ክፍሉ 1.50 ሜትር በ1.50 ሜትር ስፋት ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፣

33.7.3 የመፀዳጃ ክፍሉ የተጣራ የበር ስፋት ከ90 ሳ.ሜ ማነስ የሌለበት ሆኖ ወደ ውጭ ተካፋች መሆን ይኖርበታል፣

33.7.4 በመፀዳጃ ክፍል ውስጥ በሦስቱም ማዕዘን የእጅ መደገፊያ ያለው ሆኖ መደገፊያው ከግድግዳው ከ8 ሳ.ሜ እስከ 10 ሳ.ሜ ርቆ መዘጋጀት ይኖርበታል፣

33.7.5 የመፀዳጃ ቤቱ መቀመጫ ከ57 ሳ.ሜ እስከ 60 ሳ.ሜ ከወለል በላይ ከፍታ ሊኖረው ይገባል፣

33.7.6 የመፀዳጃ ቤቱ የእጅ መታጠቢያ፣ ማድረቂያ፣ እና የሳሙና ማስቀመጫ ከወለል በላይ ከ50 ሳ.ሜ እስከ 70 ሳ.ሜ ከፍታ ላይ መዘጋጀት ይኖርበታል፣

33.8 የመኪና ማቆሚያ

33.8.1 የሕዝብ መገልገያ ሕንፃዎች ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች የመኪና ማቆሚያ ቦታ ከአመቺ መዳረሻ ጋር ሊዘጋጅላቸው ይገባል፣

33.8.2 ለተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚ የአካል ጉዳተኞች የመኪና ማቆሚያ ቦታ ጠቋሚ ማሳያ ምልክት መዘጋጀት ይኖርበታል፣

## ክፍል አራት በህንፃ ግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚኖርባቸው የደህንነት ጥንቃቄዎች

## 34. በግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች

34.1. አጠቃላይ

34.1.1. የሕንፃዎች ግንባታ በሚከናወንበት ጊዜ ጊዜያዊ ወለሎች፣ ማረፊያዎች፣ ፎርምዎርኮች እና ደህንነት መጠበቂያ መረቦች ሥራው ለሚቆይበት ጊዜ ሁሉ መዘርጋት ይኖርባቸዋል፣

34.1.2. በአንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ (34.1.1) የተመለከተውን የደህንነት መጠበቂያ መረቦች መጠቀም የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ጊዜያዊ ወለል ሥራው በሚሰራበት ከፍታ ልክ መዘርጋት ይኖርበታል፣

34.1.3. በሥራ ቦታዎች ሠራተኞች ለሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ከሚያስፈልጉ ክፍተቶች በስተቀር የስራ ቦታዎችን ሙሉ ለሙሉ የሚሸፍኑ ጊዜያዊ ወለሎች እንዲኖሩ መደረግ ይኖርበታል፣ ክፍተቶቹም በሚገባ ሊከለሉ ይገባል፣

34.1.4. አደጋ ሊያስከትል የሚችል እያንዳንዱ የወለል ክፍተት፣ በአስተማማኝ ሁኔታ መሸፈን ወይም መከለል ይኖርበታል፣ ለክፍተት በተጋለጡ ጎኖች ሁሉ ከለላ ድጋፍ እና የእግር መደገፊያ ጣውላ ሊኖር ይገባል፣ ወይም ከክፍተቱ በታች ለእያንዳንዱ ክፍተት የሚያገለግል የደህንነት መረብ ሊዘረጋ ይገባል፣

34.1.5. በሥራ ቦታዎች ላይ ለሥራ የሚያስፈልጉ ቁሶች (ማቴሪያሎች) ሊወድቁ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል ፣

ሀ) ሠራተኞች ለአደጋ ወደተጋለጡ ቦታዎች እንዳይገቡ ለመከላከል እንዲቻል ቦታዎቹ መዘጋት ወይም መከለል የሚኖርባቸው ሆኖ በተጨማሪም በሁሉም የሥራ ቦታዎች ጎኖች እና አቅራቢያዎች ጎልተው የሚታዩ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች መቀመጥ ይኖርበታል፣

ለ) ለሥራ የሚያስፈልጉ ቁሶች ሊወድቁ በሚችሉባቸው ቦታዎች የመቀለቢያ መድረኮች ሊኖሩ ይገባል፣ መድረኮቹም፣ ከሕንፃው ውጭ ከ3 ሜትር ባላነሰ ርቀት ሊዘረጉ እና ፊታቸውን ወደ ሕንፃው አቅጣጫ አድርገው ወደ ውስጥ ማዘንበል ይኖርባቸዋል፣

34.1.6. የግንባታ ሥራዎች በሰዎች እና በንብረት ላይ የሚደርሱ አደጋዎች እና ጉዳቶችን እንዲሁም የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል እንዲቻል መወሰድ ያለባቸውን ወይንም ለሕይወት ጠንቅ የሚሆኑ ሌሎች ሁኔታዎች እንዳይደርሱ ጥንቃቄን ግምት ውስጥ በማስገባት መገንባት ይኖርባቸዋል፣

34.1.7. የሕንፃዎች ግንባታ በሚከናወንበት ወቅት ወደ ወሰንተኛ ይዞታ እና ወደ መንገድ የሚወድቅ፣ የሚራገፍ ፣ የሚበን እና የሚንጠባጠብ የግንባታ ቁሳቁስ እና መሣሪያ እንዳይኖር ተገቢው መከላከያ መደረግ አለበት፣

34.1.8. በመንገድ ዳር በሚሠሩ ሕንፃዎች አካባቢ ቁሳቁሶች ከላይ ወድቀው ከሥር የሚንቀሳቀስውን መንገደኛ እንዳይጐዱ ከጠንካራ ቁሳቁስ የተዘጋጀ መካለከያ አጥር መዘጋጀት ይኖርበታል፣

34.1.9. ከግንባታ ቦታ የሚወጡ እና ወደ ግንባታ በሚደረግ የመጫን ማውረድ እንቅስቃሴ ምክንያት በመንገድና ከይዞታ ውጪ በአካባቢው ላይ የሚወድቀውንና የሚራገፈውን ቁስና ተረፈ ግንባታ ገንቢው በራሱ ወጪ የማፅዳት ኃለፊነት አለበት፣

34.1.10. ልዩ ፈቃድ ከሌለ በስተቀር አንድን የግንባታ ቁስ ከይዞታ ውጭ ማከማቸት አይፈቀድም፣

## 34.2. በግንባታ ወቅት መደረግ የሚገባቸው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች

ማንኛውም ግንባታ በሚከናወንበት ወቅት፤

34.2.1. በግንባታው አካባቢ ያሉት የመሠረተ ልማት አውታሮች አገልግሎት ከመስጠት መስተጓጎል የለባቸውም፣

34.2.2. የአዋሳኝ ህንፃዎች ደህንነት መጠበቁ መረጋገጥ ይኖርበታል፣

34.2.3. በሜካኒካል መሣሪያዎች ጉድለት ወይም ብልሽት ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስ መሣሪያዎቹ በትክክል መሥራታቸው በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት፣

34.2.4. በህንፃው ዙሪያ የወዳደቁ ማቴሪያሎች እና ቆሻሻዎች እንዲሁም ያለአግባብ የተከማቹ ብናኝ አደገኛ ኬሚካሎች መወገድ አለባቸው፣

34.2.5. በሕንፃ ግንባታ ቦታ ላይ በሰውና በእንስሳት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ከለላ መኖር አለበት፣

34.2.6. ከደረሱ አደጋዎች በመነሣት መንሴያቸውን መተንተን ምልክታ ማካሄድና የናሙና ፍተሻ በማድርግ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፣

## 35. መወጣጫዎች እና መሰላሎች

### 35.1. መወጣጫዎች (Scaffoldings)

35.1.1. ማንኛውም መወጣጫ (Scaffoldings) መሸከም በሚገባው ክብደት መጠን መሠረት ዲዛይን ተደርጐ መጋጀት አለበት፣

35.1.2. በመወጣጫው (Scaffolding) ድጋፎች ጥብቅ መሠረት ወይም ደፎች እንዲኖራቸው እና መወጣጫው የድጋፍ መያ[1] እንዲኖረው ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል፣

35.1.3. በመወጣጫው (Scaffolding) ላይ የሚገኙ የሥራ መድረኮች ስፋት ከ50 ሳ.ሜ ያነሰ መሆን የለበትም፣

35.1.4. በመወጣጫው (Scaffolding) ሥር የሚዘጋጀው ጣውላ፣ ብረት ወይም አጠና ጠንካራ እና ሰዎችን እና ዕቃን የማይጥልና የማያንጠባጥብ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፣

35.1.5. የመወጣጫ ድልድሎችን ለመስራት ጥቅም ላይ የሚውለው የእንጨት ዓይነት አገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት ጥንካሬአቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፣

35.1.6. ቀጥተኛ በሆኑት የፊት እና የኒላ የመወጣጫ ድጋፎች መካከል ያለው ርቀት ከ85 ሳ.ሜ የማያንስ ሆኖ በአንድ ጣውላ ስፋት የሚበልጥ ክፍተት እንዳይፈጠር ተጨማሪ ጣውላዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፣

35.1.7. የሚሰካኩ በወጣጫዎች (Scaffolding) ዲዛይን የሚደረጉት፣ የሚመረቱት እና አገልግሎት ላይ የሚውሉት አምራቾች በሚሰጡት መግለጫ መሠረት መሆን ይኖርበታል፣

35.1.8. መወጣጫዎች መዘርጋት ወይም መፈታት የሚኖራባቸው በሥራው ልምድ ባላቸው ሰዎች ወይም ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ተቆጣጣሪት መሆን አለበት፣

35.1.9. ጉዳት የደረሰበት ወይም የላላ የመወጣጫ አካል ተገቢው እድሳት ተደርጎለት በአስተማማኝ ሁኔታ እስካልተጠናከረ ድረስ አገልግሎት ላይ መዋል የለበትም፣

35.1.10. በግንባታ ቦታ ላይ የሚገኝ መወጣጫ ከአደጋ የተጠበቀ መሆኑ በአሠሪው ወይም በሠራተኞቹ የዕለት ከዕለት ቁጥጥር ሊደረግለት ይገባል፣

35.1.11. በመወጣጫ ድልድሉ ላይ የሚቀመጠው ዕቃ መወጣጫው መሸከም ከሚችለው አቅም በላይ እንዳይሆን ተገቢው ጥናቃቄ መደረግ ይኖርበታል፣

35.1.12. መወጣጫዎች ቀጥ ብለው እና ተስተካክለው መዘርጋት ያለባቸው ሲሆን ከሕንፃው አካል ጋር በእያንዳንዱ 4.5 ሜትር ከፍታ እንዲሁም በየ6 ሜትሩ ርቀት አግድም መታሰር አለባቸው፣

35.1.13. ተንቀሳቃሽ መሰላል መሳይ መወጣጫዎች ከመሬት ወለል ከ5 ሜትር በላይ ለሚሰራ ስራ ጥቅም ላይ መዋል የሌለባቸው ሆኖ ከ5 ሜትር በታች ለሚሠራ ሥራ በአንድ ጊዜ ከሁለት ሠራተኞች በላይ ሊገለገሉባቸው አይገባም፣

35.2. **መሰላሎች**

35.2.1. የእንጨት መሰላሎች አስተማማኝ በሆነ ጥንካሬ የተሰሩ እና በሚሰጡት አገልግሎት ምክንያት የሚደርስባቸውን ጫና መሸከም የሚችሉ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፣

35.2.2. ከእንጨት የተሰሩ መሰላሎች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ቀለም የተቀቡ መሆን ይገባቸዋል፣

35.2.3. ከቦታ ወደ ቦታ ሊዘዋወሩ የሚችሉ ተንቀሳቃሽ መሰላሎች አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት ተገቢው ፍተሻ ሊደረግላቸው ይገባል፣

35.2.4. የላሉ ወይም የተሰበሩ ወይም የጎደሉ መወጣጫዎች ወይም የተሰነጠቁ የጎን ቋሚዎች ያሏቸው መሰላሎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ አይፈቀድም፣

35.2.5. የተንቀሳቃሽ መሰላል የጎን ቋሚዎች የታችኛው ጫፎች ጠንካራ በሆነ እና በተደላደለ መደብ ላይ ማረፍ የሚኖርባቸው ሆነው የጎን ቋሚዎቹ የላይኛው ጫፍ የሚሸከመውን ክብደት ለመደገፍ በሚችል በቂ ጥንካሬ ባለው ደጋፊ አካል እንዲገፉ ማድረግ ይገባል፣

35.2.6. ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ነጠላ ወይም ተደራራቢ ወይም ተቀጣጣይ መሰላሎች እንዳይንሸራተቱ ተንሸራታች ያልሆነ መደብ እንዲኖራቸው ወይም እንዲያያዙ ወይም እንዲታሰሩ መደረግ ይኖርባቸዋል፣

35.2.7. የኤሌትሪክ ፍሰት ባለበት አካባቢ የሚያገለግሉ መሰላሎች ኤሌክትሪክ የማያስተላልፉ ዓይነት ሆነው በመሰላሎቹ እና በኤሌትሪክ አስተላላፊዎቹ መካከል በቂ ክፍት ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣

35.2.8. ከብረት የተሰሩ መሰላሎች ወይም በእንጨት ተሰርተው በሽቦ የተጠናከሩ መሰላሎች በሃይል የተሞላ የኤሌክትሪክ መሣሪያ በአለበት ቦታ ላይ መጠቀም የተከለከለ ነው፣

35.2.9. የመሰላሎች ርዝመት ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት መሆን ይኖርበታል፣

ሀ) ለባለድጋፍ መሰላሎች ወይም ተቀጣይ ለሆኑ ባለድጋፍ መሰላሎች 4.8 ሜትር፣

ለ) ለነጠላ መሰላሎች 9 ሜትር፣

ሐ) ሁለት ተቀጣጣይ ክፍሎች ላሏቸው ተቀጣጣይ መሰላሎች 14.6 ሜትር እና

መ) ከሁለት ተቀጣጣይ ክፍሎች በላይ ላሏቸው ተቀጣጣይ መሰላሎች 20 ሜትር፣

35.2.10. ከ6 ሜትር በላይ ቁመት ያላቸው እንዳይንቀሳቀሱ ተደርገው የተተከሉ መሰላሎች፣

ሀ) ከ6 ሜትር ያልበለጠ ርቀት ያላቸው መቆሚያዎች እንዲኖራቸው መደረግ ይኖርበታል፣

ለ) ከመሰላሉ የታችኛው ክፍል ከ2.5 ሜትር በላይ ለሆነ ከፍታ ሠራተኞች እንዳይወድቁ ለመከላከል የሚስችል የደህንነት መጠበቂያ አጥር (ኬጅ) ሊኖረው ይገባል፣

35.2.11. የማይንቀሳቀሱ መሰላሎች መተከል ያለባቸው በየመሐከላቸው የ3 ሜትር ርቀት እንዲኖር ተደርጎ ሆኖ ከላይ እስከታች ያለው አካላቸው ይህን ርቀት መጠበቅ ይኖርበታል፣

35.2.12. በተተከሉ መሰላሎች ላይ ከሚገኙ መወጣጫዎች በስተጀርባ በትንሹ 1.75 ሜትር ስፋት ያለው ቦታ በቋሚነት እንዲኖር ማድረግ ይገባል፣

35.2.13. ከመሰላሎቹ በላይ መወጣጫዎች እንዳይኖሩ ሆኖ የጎን ቋሚዎቹ ከመሰላሎቹ ማረፊያ በላይ 90 ሳ.ሜ እስከሚቀረው ድረስ መቀጠል ይኖርባቸዋል፣

## 36. የማፍረስ ሥራ

36.1. አንድ ሕንፃ በሚፈርስበት ጊዜ ተያያዥ የሆኑ የቋሚ ግንባታ አካላት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን መሐንዲሱ ካላረጋገጠ በስተቀር ሙሉ ለሙሉ መደገፍ አለባቸው፣

36.2. አንድ ሕንፃን ለማፍረስ ሲወሰን በቋሚው የግንባታ አካል ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሥራዎች ካሉ የማፍረስ ሥራው ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ መቋረጥ አለባቸው፣

36.3. የማፍረስ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ሠራተኞችን ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ መስታወቶች እና ክፈፎቻቸው በቅድሚያ መነሳት ይኖርባቸዋል፣

36.4. የአንድ ሕንፃ የማፍረስ ሥራ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ከላይ ወደ ታች መከናወን ይኖርበታል፣ ግድግዳዎችም አደገኛ ወይም ያልተረጋጋ በሆነ ሁኔታ ቆመው እንዲቀሩ መደረግ የለበትም

36.5. ግድግዳዎች ወይም ሌሎች የግድግዳ ክፍሎች የወለሉን የመሸከም አቅም ባላገናዘበ ሁኔታ በሕንፃው ወለል ላይ እንዲወድቁ ወይም በወለሉ ላይ እንዲቆዩ መደረግ የለበትም፣

36.6. ማንኛውም ሠራተኛ ከታች በሚገኙ ወለሎች ላይ እንዳይገኙ ካልተደረገ ወይም ወደ ወለሎቹ መግባት ካልተከለከለ በስተቀር በወለሉ ላይ ከሚገኝ ክፍተት ጀምሮ በ3 ሜትር ርቀት ውስጥ የሚገኝ የውስጥ ወይም የውጭ ግድግዳ እንዲፈርስ ከመደረጉ በፊት ከወለሉ ክፍተት በታች የሚሆን ጣውላ እንዲኖር መደረግ አለበት፣

36.7. የሚፈርሱ ቁሶች ከሕንፃው ላይ በጥንቃቄ እንዲወርዱ ሆነው ባግባቡ መከማቸት እና መወገድ ይኖርባቸዋል፣

36.8. ፍርስራሽ ማቴሪያሎች እና ሌሎች ቆሻሻዎች በወለሎች ወይም ከሕንፃው ውጭ በቅርብ ርቀት ላይ መጣል የለባቸውም፣

36.9. ከከፍተኛ ፎቆች ላይ ፍርስራሽ ማቴሪያሎች ወደ መሬት ሲወረወሩ ማቴሪያሉ እንዲወድቅ በሚፈለግበት ቦታ ሠራተኞች እንዳይገቡ ቦታው መከለል ወይም መዘጋት ይኖርበታል፣ በተጨማሪም በአካባቢው ላይ የማስጠንቀቂያ ምልክት መደረግ ይኖርበታል፣

36.10. አንድ ሕንፃ በሚፈርስበት ጊዜ ፍርስራሽ ሽክላዎች ወይም ሌሎች የደቀቁ ፍርስራሾችን ለማስወገድ የሚያስችል ማንሸራተቻ ወይም ማስተላለፊያ ሊኖረው ይገባል፣

36.11. ማንሸራታቻዎቹ ወይም ማስተላለፊያዎቹ ባልተቋረጠ ሁኔታ በህንፃው ላይ ሊዘረጉ የሚችሉት ሕንፃዎቹ ከሁለት ፎቅ ያልበለጠ እንደሆነ ብቻ ነው፣

36.12. ከእያንዳንዱ ማስተላለፊያ በታች መዝጊያዎች ወይም ማገጃዎች እንዲገጠሙ እና በማንሸራታቻ የመውጫ አፎች አጠገብ "ተንሸራታች ማቴሪያል" የሚል የማስጠንቀቂያ ምልክት መቀመጥ ይኖርበታል፣

## 37. ስለ ከፍታ እና የጣሪያ ላይ ሥራዎች

### 37.1. የከፍታ ላይ ሥራዎች

37.1.1. ሠራተኞች ከወለል ከ3 ሜትር በላይ ከፍታ ላይ የሚሰሩ ሆኖ ሲገኝ የመጠንጠልጠያ ገመዶች፣የደህንነት መጠበቂያ ቀበቶዎች ወይም የአደጋ መከላከያ መረቦች መቅረብ ይኖርበታል፣

37.1.2. ሠራተኞች ሊወድቁ ወይም ሊንሸራተቱ የሚችሉበት በወለል ላይ የሚገኝ ክፍት ቦታ በከለላ ድጋፍ እና በእግር መደገፊያ ጣውላ መሸፈን ወይም መከደን ይኖርበታል፣

37.1.3. በማንኛውም በከፍታ ቦታ ላይ የመገንባት ወይም የማፍረስ ሥራ የሚሰራ ሠራተኛ ከአደጋ መከላከል የሚያስችሉ የጭንቅላት፣ የእጅ እና የእግር መጠበቂያ ማቴሪያሎችን መጠቀም ይኖርበታል፣

### 37.2. የጣሪያ ላይ ሥራዎች

37.2.1. ማንኛውም የጣሪያ ሥራ በቅድሚያ የታቀደና ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግለት ይገባል፣

37.2.2. በጣሪያ ሥራ ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ሠራተኛ የፊዚካላዊ እና ሳይኮሎጂካዊ ብቃት ያለው፣ በጣሪያ ሥራ ላይ በቂ እውቀት እና የሥራ ልምድ ያለው መሆን ይገባዋል፣

37.2.3. የጣሪያ ሥራ የሠራተኞችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል የአየር ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ መቋረጥ ይኖርበታል፣

37.2.4. ለጣሪያ ሥራ የሚውሉ የመንፏቀቂያ እንጨቶች፣ መረማመጃዎች እና የጣሪያ መሰላሎች ከቋሚ ግንብ ጋር በአስተማማኝ ሁኔታ መታሰር ይኖርባቸዋል፣

37.2.5. የጣሪያ ተሸካሚዎች ወይም ድጋፎች ከጣሪያው ቁልቁለማነት/ዝቅዝቃት ጋር እንዲገጥሙ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የተደገፉ መሆን ይገባቸዋል፣

37.2.6. በጣሪያው ጠርዝ ዙሪያ መንበርከክ ወይም ቁጢጥ ማለት ሲያስፈልግ ሠራተኛው በደህንነት መጠበቂያ ገመድ መጠቀም ይኖርበታል፣ ይህ ካልሆነ ደግሞ በመካከሉ ድጋፍ መኖር አለበት፣

37.2.7. በጣሪያ ላይ ለሚገኙ ክፍት ቦታዎች መዝጊያ ክዳኖች በሙሉ ጠንካራ ከሆነ ቁሳቁስ የተሰሩ ሆነው በትክክል መገጠም ይኖርባቸዋል፣

37.2.8. በቁልቁለታማ ጣሪያዎች ላይ ለሚከናወኑ ሥራዎች አስተማማኝ እና ተስማሚ የመንፏቀቂያ ጣውላዎች ወይም የጣሪያ መሰላሎች ተዘጋጅተው በተገቢው ቦታ እንዲቀመጡ መደረግ ይኖርበታል፣

37.2.9. ረዥም ጊዜ ለሚወስዱ የጣሪያ ሥራዎች ሠራተኛውን ከአደጋ መከላከል የሚያስችሉ ጠንካራ የሆኑ ማገጃዎች ወይም ከለላ ድጋፎች እና እግር እንዳይንሸራተት የሚከላከሉ ጣውላዎች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፣

37.2.10. አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉ ጣሪያዎች ወይም ተሰባሪ ጣሪያዎች ባሏቸው ሕንፃዎች ላይ ወደ ጣሪያው መውጫ አካባቢ የማስጠንቀቂያ ጽሁፍ በግልጽ በሚታይ መልኩ እንዲኖር መደረግ ይኖርበታል፣

## 38. የመሬት ውስጥ ሥራዎች

### 38.1. ጠቅላላ

38.1.1. ማንኛውም የቁፋሮ እና የመሬት ውስጥ ሥራዎች በሚከናወኑበት ወቅት በሠራተኞች ላይ የመውደቅ፣ የአፈር መናድ፣ የውሃ ሙላት እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ አደጋዎች እንዳይደርሱ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፣

38.1.2. ከመሬት በታች ለሚከናወኑ የቁፋሮ ሥራዎች ብርሃን እና አየር ለማስገባት የሚስችሉ ክፍተቶች መኖራቸውን እና የአደጋ ጊዜ መውጫ መንገድ መዘጋጀቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፣

38.1.3. በመሬት ውስጥ የሚዘረጉ የኤሌክትሪክ መሥመሮች በኢትዮጵያ የሕንፃ ኮድ እና ስታንዳርድ በተቀመጡት የአሠራር ሥርዓቶች መሠረት ይሆናል፣

38.1.4. ትላልቅ የቁፋሮ እና የመሬት ውስጥ ሥራዎች ሲከናወኑ የዕለት ከዕለት ቁጥጥር እና ክትትል በተቆጣጣሪ መሐንዲሱ መደረግ ይኖርበታል፣

38.2. **የቁፋሮ ሥራ**

38.2.1. ማንኛውም የቁፋሮ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች መረጋገጥ አለባቸው፣

ሀ) የሚፈለገው የቁፋሮ ሥራ በሚገባ የታቀደ እና የአቆፋፈር ዘዴው በግልጽ ተለይቶ የተቀመጠ መሆን ይኖርበታል፣

ለ) የመሬቱ የተፈጥሮ ሁኔታ በተገቢው ባለሙያ ተመርምሮ መታወቅ ይኖርበታል፣

ሐ) የሚካሄደው የቁፋሮ ሥራ በአካባቢው ላይ የሚገኙትን ሕንፃዎች፣ መንገዶች እና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮችን የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣

መ) በቁፋሮ ወቅት አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የውሃ መስመሮች፣ ከመሬት በታች የቆሻሻ መውረጃ መስመሮች ወይም ቱቦዎች፣ እና የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያዎች በሚመለከተው አካል ቁጥጥር እና ክትትል የሚደረግባቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፣

ሠ) ቁፋሮ የሚካሄድበት ቦታ በጎጂ ኬሚካሎች ወይም ጉዳት ሊያመጡ በሚችሉ አደገኛ ቁሶች ያለመበከሉ በሚመለከተው አካል  መረጋገጥ ይኖርበታል፣

ረ) የተቆፈሩ ጉድጓዶች ጎን በሠራተኞች ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ከከባድ ዝናብ፣ ከመሬት መንሸራተት እና ከፈንጂዎች መፈንዳት በኂላ በተገቢው ባለሙያ ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፣

ሰ) የተቆፈረውን ጉድጓድ እንዲናድ ወይም እንዲንሸራተት የሚያደርጉ ከባድ መሣሪያዎች እና ማሽነሪዎች እንዲሁም የማምረቻ ተቋማት በአካባቢው መቀመጥ ወይም መተከል አይኖርባቸውም፣

ሸ) እግረኞች እና ተሽከርካሪዎች የተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ እንዳይገቡ የመከለያ አጥሮች እና የማስጠንቀቂያ ማስታወቂያዎች ተዘጋጅተው መተከል ይኖርባቸዋል፣

38.2.2. ከሚቆፈረው ቦታ በቅርብ ርቀት እስከ ሁለት ሜትር የሚገኙ ዛፎች፣ ቋጥኞች እና ሌሎች ቁሶች የቁፋሮው ሥራ ከመጀመሩ በፊት መነሳት ወይም መወገድ ይኖርባቸዋል፣

38.2.3. ማንኛውም ሠራተኛ ከ1 ሜትር በላይ ጥልቀት ባለው ቁፋሮ ውስጥ እንዲገባ የሚፈቀድለት፣

ሀ) የተቆፈሩ ጉድጓዶች ጎን አደጋ እስከማያስከትል ቦታ ድረስ እንዲያዘነብሉ ሲደረግ፣

ለ) በተቆፈረው ጉድጓድ ጎኖች ብረቶችን በመትከል፣ ድጋፎችን በመስራት ወይም ወሽመጦችን ወይም ቦዮችን በመስራት ጥበቃ ሲደረግላቸው እና

ሐ) ሠራተኞች በሌሎች አስተማማኝ ዘዴዎች የተጠበቁ ሆነው ሲገኙ ብቻ ይሆናል፣

38.2.4. በሚቆፈረው ቦታ አቅራቢ የሚገኙ የሕንፃዎች መሠረቶች ሊሸረሸሩ ይችላሉ ተብሎ ሲገመት የቁፋሮው ሥራ በአጫጭር ክፍልፋዮች እንዲሰራ እና የህንፃዎቹ ግድግዳዎች በአስተማማኝ ሁኔታ መደገፍ ወይም መታሰር ይኖርባቸዋል፣

38.2.5. ሠራተኞች ከ1.2 ሜትር በላይ ጥልቀት ባላቸው የተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ ሲገቡ በቅርብ ርቀት በሚገኙ ቦታዎች መሰላሎች እንዲኖሩ መደረግ ይኖርበታል፣ መሰላሎቹ ከተቆፈረው ጉድጓድ የታችኛው አካል ጀምሮ ከጉድጓዱ አናት በላይ ከ90 ሳ.ሜ ባላነሰ ከፍታ መዘርጋት ይኖርበታል፣

38.2.6. በተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ የሠራተኞችን መውደቅ ለመከላከል ጉድጓዶቹ አስተማማኝ በሆኑ ድጋፎች ወይም ማገጃዎች መከለል አለባቸው፣

38.2.7. በቁፋሮ ወቅት ተንቀሳቃሽ መሣሪዎችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መሣሪዎቹ ከመንደርደራያዎች ላይ ተንሸራተው እንዳይወድቁ በመንደርደሪያዎቹ ላይ ጠርዞች መሠራት ይኖርበታል፣

38.3. በተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ ለመግባት እና ከቁፋሮው የሚወጡ ማቴሪያሎችን ለማስወገድ ሲፈለግ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፣

38.3.1. ወደ ተቆፈሩ ጉድጓዶች ለመግባት የሚያገለግሉ መረማመጃዎች፣

ሀ) ከጠንካራ ጣውላ ወይም ላሜራ ወይም ተመሣሣይ ጥንካሬ ካላቸው ቁሳቁስ የተሰሩ ሆነው ከ60 ሳ.ሜ ያላነሰ ስፋት ሊኖራቸው ይገባል፣

ለ) ከድልድል በላይ ከ1.2 ሜትር በላይ ጥልቀት ካላቸው ከለላ ወይም አጋጅ ድጋፎች መሰራት ይኖርበታል.

ሐ) ድልድሎቹ በስድስት ሜትር ቁመት ውስጥ ከአንድ የበለጡ ሆነው ሲገኙ መረማመጃዎቹ በችካሎች መጠናከር ይኖርባቸዋል፣

38.3.2. ማንኛውም በቁፋሮ ሥራ ላይ የተሰማራ ሠራተኛ ከቁፋሮው የወጣውን ማቴሪል ከተቆፈሩ ጉድጓዶች ጠርዝ ጀምሮ በ1.2 ሜትር ርቀት ውስጥ ማከማቸት አይኖርበትም፣

38.3.3. ከተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ የወጡትን ማቴሪሎች ለማስወገድ ጥቅም ላይ የሚውሉ የማዘለያ ዕቃዎች ወይም ባልዲዎች የመደገፊያ አካላቸው እንዳይነቀሉ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፣

## 39. ስለ ኬሚካሎች፣ ፈንጂዎች እና መርዛማ ቁሳቁሶች

### 39.1. ኬሚካሎች

39.1.1. በግንባታ ቦታ ላይ በሠራተኛው ጤናና ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ኬሚካላዊ ቁሶች በየጊዜው ሊመረመሩ እና ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፣

39.1.2. በሥራ ቦታ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ኬሚካላዊ ቁሶች በተቻለ መጠን አደጋ ሊያደርሱ በማይችሉ ተለዋጭ ቁሶች እንዲተካ ማድረግ ያስፈልጋል፣

39.1.3. አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ኬሚካላዊ ቁሶች በአንድ የሥራ ቦታ የሚገኙ ከሆነ በሠራተኞች ጤንነት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል የሚያስችሉ ርምጃዎች መወሰዳቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፣ የሚወሰዱት ርምጃዎች፣

ሀ) የሥራ ቦታን በተስማሚ ሁኔታ ዲዛይን ማድረግ እና ሥራው ዙሪያውን ዝግ በሆነበት ሁኔታ እንዲሰራ ወይም እንዲከለል ማድረግ፣

ለ) ለአደጋ የሚጋለጡትን ሠራተኞች ወይም ለአደጋ የሚያጋልጠው ሥራ የሚሰራበትን ጊዜ መቀነስ፣

ሐ) የነፍስ ወከፍ የመከላከያ አልባሳትን መጠቀም.

መ) ተቀጣጣይ እና አንፀባራቂ ቁሶችን እንዲሁም ለመገልገያነት የሚውሉ ኬሚካሎችን ከሥራ ቦታ አካባቢ ማራቅ የመሳሰሉትን ያካትታል፣

### 39.2. ስለ ፈንጂዎች

39.2.1. በሥራ ቦታ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፈንጂዎች በሚመለከተው አካል ተቀባይነት ያለው ካልሆነ በስተቀር ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፣

39.2.2. ማናቸውም በግንባታ ሥራ ላይ ፈንጂ የማፈንዳት ሥራዎች መከናወን የሚችሉት በፈንጂ ተቆጣጣሪ አካላት በሚወጡ መመሪያዎች እና ደንቦች መሠረት ይሆናል፣

39.2.3. የፈንጂ ማፈንዳት ሥራዎች በሚከናወኑበት ጊዜ የፈንጂ ተቆጣጣሪ ባለሙዎች ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ ይኖርባቸዋል፣

### 39.3. መርዛማ (toxic) ቁሳቁሶች

በግንባታ ሥራዎች ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ነገር ግን ለጤና ጉጂ የሆኑትን እንደ ሲሚንቶ፣ ላይም፣ የምስጥ ማጥፊያ ኬሚካል፣ ቶክሲክ የሆኑ ቀለሞች፣ ፖሊሽ (ማፅጂያ) ማድረጊያ አሲድ፣ የሆኑትን ቁሳቁሶች አጠቃቀም እና አያያዝ ላይ በቂ ጥንቃቂ መደረግ አለበት፤

## 40. ስለ አልባሳት

40.1. በማንኛውም በግንባታ ቦታ ላይ የተሰማራ ሠራተኛ ከዚህ በታች የተመለከቱትን የግንባታ ቦታ የአደጋ መከላከያ አልባሳት መጠቀም ይኖርበታል፤

40.1.1. የጭንቅላት መከላከያ ቆብ፣

40.1.2. የሥራ ጫማ፣

40.1.3. የሥራ ልብስ ማድረግ ይኖርበታል፣

40.2. ማንኛውም በግንባታ ቦታ ላይ ጉብኝት የሚያደርግ ሰው የጭንቅላት መከላከያ ቆብ ማድረግ ይኖርበታል፣

40.3. ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ አሠሪ በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀጽ 40.1 እና 40.2 የተመለከተቱትን አልባሳት በሥራ ቦታው ላይ እንዲገኙ እና ሠራተኞችም የማድረግ ግዴታ አለበት፣

40.4. ማንኛውም አሠሪ በሥሩ የሚተዳደሩ ሠራተኞች በአንቀፅ 40 በንዑስ አንቀጽ 40.1 የተመለከቱትን አልባሳት በሥራ ቦታቸው ላይ መጠቀማቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፣

40.5. በማንኛውም ሥራ ቦታ ላይ ሠራተኞች ለግል ንብረቶቻቸው ማቆያ የሚያገለግል ቁም ሳጥን ለእያንዳንዱ ሠራተኛ በአሠሪው ሊዘጋጅለት ይገባል፣

## 41. የእሣት አደጋ ስለ መከላከል

41.1. ስለ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪዎች

41.1.1. ሁሉም (አውቶማቲክ መርጫ መከላከያ መሣሪያ የተገጠመላቸውን ጨምሮ) የሥራ ቦታዎች ከጥንቃቄ ጉድለት የሚከሰቱ እሳቶችን ለመከላከል እና ለማጥፋት የሚያስችሉ ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ሊኖራቸው ይገባል፣

41.1.2. እነዚህ ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ሙሉ ለሙሉ ተሞልተው እና አገልግሎት መስጠት በሚያስችላቸው ሁኔታ ተዘጋጅተው በተመደበላቸው ቦታ ላይ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፣

41.1.3. አገልግሎት ላይ የሚውሉ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ሥልጣን ባለው አካል ፈቃድ የተሰጣቸው መሆን ይገባቸዋል፣

41.1.4. የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች የእሳት አደጋ በሚፈጠርበት ጊዜ ሊደረስባቸው በሚችሉ ግልጽ እና ከመሰናክል ነፃ በሆኑ አካባቢዎች በሚገኙ መስቀያዎች ወይም ድጋፍ ባላቸው ማስቀመጫዎች ላይ መሰቀል ወይም መቀመጥ ይኖርባቸዋል፣

41.1.5. የእሳት ማጥፊያ መሣሪዎች በተመደበላቸው ቦታ መገኘታቸውን፣ በአካላቸው ላይ የደረሰ ጉዳት መኖሩን እና አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ ላይ መገኘታቸውን ለማረጋጥ የሚያስችል ምርመራ ከአንድ ዓመት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ መሣሪያዎቹ በሚቀመጡበት ወይም በሚሰቀሉበት ቦታ ሊደረግላቸው ይገባል፣

41.1.6. የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች በሚቀመጡበት ወይም በሚሰቀሉበት ቦታ የመሣሪያዎቹ ዓይነት፣ የሚሰጡት አገልግሎት እና በትክክል መጠቀም የሚያስችሉ መመሪያዎች በሚታዩ እና በቀላሉ በሚነበቡበት ሁኔታ ተጽፈው መለጠፍ ይኖርባቸዋል፣

41.2. ስለ እሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች

41.2.1. ማንኛውም ሕንፃ በእሳት አደጋ ጊዜ ሠራተኞች እንዲያመልጡ የሚያስችሏቸው መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፣

41.2.2. በማንኛውም ህንፃ እያንዳንዱ ፎቅ ላይ በተለያዩ አቅጣጫዎች የተዘጋጁ ሁለት የእሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፣

41.2.3. ሁሉም የእሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች በተገቢው መንገድ ጥበቃ የተደረገላቸው እና ማንኛውም እንቅስቃሴ ከሚገድቡ ወይም ከሚያውኩ መሰናክሎች ነፃ መሆን አለባቸው፣

41.2.4. ተንሸራታች ከሆኑ በሮች በስተቀር ሁሉም የሕንፃው በሮች ወደ ውጭ እንዲከፈቱ ሆነው መሰራት ይኖርባቸዋል፣

41.2.5. ሠራተኞችን ከሕንፃው ውስጥ ወይም ሕንፃው ከሚገኝበት ግቢ ለመውጣት የሚስችሉ በሮች በቀላሉ እንዳይከፈቱ በሚያደርጋቸው ሁኔታ መቆለፍ ወይም መታሰር የለባቸውም፣

41.2.6. በማናቸውም ክፍሎች ውስጥ የሚከማቹ ዕቃዎች በክፍሉ ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች የእሳት አደጋ በሚፈጠርበት ወቅት ለማምለጥ የሚያስችላቸው ነፃ የመተላለፊያ መንገድ እንዲኖር በሚያስችል ሁኔታ መዘጋጀት ወይም መደራጀት ይኖርባቸዋል፣

41.2.7. ማንኛውም በሕንፃ ውስጥ የሚገኝ ሠራተኛ በእሳት አደጋ ጊዜ ለማምለጥ የሚያስችለውን መንገድ እና በአደጋ ጊዜ መከተል ስለሚኖርበት ስርዓት ተገቢው ሥልጠና ማግኘት ይኖርበታል፣

41.3. ስለ ተቀጣጣይ ቁሳቁሶች

41.3.1. የተቀጣጣይነት ባህርይ ያላቸው የግንባታ ቁሳቁሶች ለእሳት በሚጋለጡ ቦታዎች መከማቸት አይኖርባቸውም፣

41.3.2. በግንባታ ሥራ ውስጥ በቀላሉ በእሳት የሚቀጣጠሉ ቁሶችን ወይም ፈሳሾችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ሀ) ተቀጣጣይ ነገሮች እንዳይቀጣጠሉ ለመከላከል የሚያስችል ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል፣

ለ) ተቀጣጣይ ቁሶችን ለመሸከም፣ ለማስተላለፍ እና ለማከማቸት የሚያገለግሉ የመያዣ ዕቃዎች በጥንቃቄ መጠበቅ እና መታሰር ይኖርባቸዋል፣

## 42. ስለ የመጀመሪያ እርዳታ አሠጣጥ

42.1. በማንኛውም የሥራ ቦታ ላይ የመጀመሪያ የእርዳታ አገልግሎት መስጫ ቁሳቁስ ክፍል በአሰሪው መደራጀት ይኖርበታል፣

42.2. በሥራ ቦታ ውስጥ የመጀመሪያ የህክምና መስጫ ቦታን የሚያመለክቱ ምልክቶች በግልፅ በሚታዩ ቦታዎች መለጠፍ ወይም መተከል ይኖርበታል፣

42.3. በሥራ ቦታ ላይ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ላይ የደረሰበትን አደጋ ወይም ጉዳት በተመለከተ አግባብ ባለው መ/ቤት ተዘጋጅቶ በተፈቀደ ፎርም መመዝገብ ይኖርበታል፣ አሠሪውም በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት መመዝገቡን የማረጋገጥ እና የምዝገባ ዝርዝሩን ወደ ሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፣

42.4. ማንኛውም አሠሪ በሥራ ቦታ ላይ በከባድ ሕመም ወይም አደጋ የተጎዳን ሠራተኛ ወደ ሕክምና ተቋም የመውሰድ ሃላፊነት አለበት፣

42.5. በግንባታ ቦታዎች ለድንገተኛ አደጋ አገልግሎት የሚሠጡ የሕክምናና የአምቡላንስ አገልግሎት ተቋማት አድራሻዣቸው መመልከት አለባቸው፣

## 43. ስለ አደጋ ማምለጫ መንገዶች

43.1. ማናቸውም የሥራ ቦታዎች ለሥራው እንደየሥራው አካባቢ ተገቢ የሆኑ እና ከአደጋ የተጠበቁ የመግቢያ እና የመውጪያ መንገዶች ሊኖራቸው ይገባል፣

43.2. በሥራ ቦታ የሚገኙ ሠራተኞች፣ መሣሪያዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶች ከአደጋ በተጠበቀ ሁኔታ ሊንቀሳቀሱ በሚችሉበት ሁኔታ መዘጋጀት አለባቸው፣

43.3. በአዳራሾች ወይም በሌሎች ክፍሎች የሚገኙ መተላለፊያዎች እና በየሕንፃው ውስጥ ከክፍል ወደ ክፍል ለመዘዋወሪያ ወይም ለመውጫ እና መግቢያ የሚያገለግሉ መተላለፊያዎች እንደአስፈላጊነቱ በወለል ምልክቶች እንዲለዩ መደረግ ይኖርበታል፣

43.4. ድንገተኛ አደጋ በሚፈጠርበት ወቅት እና መደበኛ የመውጫ መንገዶች አደገኛ ሆነው ሲገኙ ወይም ከአገልግሎት ውጭ ሆነው ሲገኝ ለማምለጥ የሚያስችሉ የድንገተኛ አደጋ ማምለጫ ዘዴዎች በቅድሚያ ሊዘጋጁ ይገባል፣

43.5. የአደጋ መውጫ በሮች ወይም መንገዶች ፈጣን የመውጫ አገልግሎት እንዲሰጡ በሚያስችል ሁኔታ ሊዘጋጁ፣ ምልክት ሊደረግባቸው እና ብርሃን ሊኖራቸው ይገባል፣

43.6. የአደጋ ጊዜ መውጫ በሮች መከፈት የሚኖርባቸው የበሮቹ ውዝዋዜ በሚፈልገው የቦታ ስፋት ወደ ያዙ ወለሎች እና የደረጃ ማረፊያዎች በኩል ሆኖ ወደ ሁለቱ ተቃራኒ አቅጣጫዎች የሚወዛወዙ በሮች ሲገጠሙ አሳልፎ ለማየት በሚያስችል ክፍተት መሆን ይገባቸዋል፣

## 44. ስለ ሠራተኞች እና የሥራ ቦታዎች ደህንነት አጠባበቅ

### 44.1. የሠራተኞች ደህንነት

44.1.1. የታወቀ አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ችግር ያለበት ሰው በግንባታ ሥራ ላይ እንዲመደብ መደረግ የለበትም፣

44.1.2. ማንኛውም የግንባታ አሰሪ ወይም ተቆጣጣሪ ወይም ሠራተኛ በሰዎች ጤንነት እና ደህንነት ላይ አደጋ በሚያስከትል ሁኔታ አስካሪ መጠጦች ጠጥቶ ከተገኘ ወደ ሥራ ቦታ መግባት ወይም ሥራው ወደሚገኝበት ቦት ላይ መቆየት አይፈቀድም፣

44.1.3. ማንኛውም በሥራ ቦታ ላይ የሚገኝ ሠራተኛ በሠራተኞች ላይ አደጋ ሊያስከትል በሚችል መልኩ እንደ ግብግብ፣ አላስፈላጊ ሩጫ እና ዝላይ እንዲሁም ቀልዶችን በሰዎች ላይ መሞከር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ረብሻ ላይ መሳተፍ የለበትም፣

44.1.4. ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ቦታው ላይ ደህንነቱን እና ጤንነቱን ለመጠበቅ የተሰጡትን መሣሪያዎች በአግባቡ መያዝ እና መጠቀም ይኖርበታል፣

44.1.5. አሠሪው የሠራተኞቹ ደህንነት እና ጤንነት ሊያስጠብቁ የሚችሉ የመከላከያ መሣሪያዎች እና ሌሎች አልባሳት እንዲያገኙ ማድረግ እና በስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ይገባዋል፣

### 44.2. የሥራ ቦታዎች ደህንነት

44.2.1. ማንኛውም አሠሪ የሥራ ቦታዎች በሠራተኞች ደህንነት እና ጤንነት እንዲሁም በሕብረተሰቡ እና በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ማድረግ ይኖርበታል፣

44.2.2. አሠሪው በሁሉም የሥራ ቦታዎች የደህንነት መጠበቂያ ሥነ-ስርኣቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን በየጊዜው ማረጋገጥ ይኖርበታል፣

44.2.3. ማንኛውም የሥራ ቦታ ከቆሻሻ የፀዳ እና በጽዳት የሚጠበቅ መሆን ይኖርበታል፣

44.2.4. ማንኛውም የሥራ ቦታ ለወንዶች እና ሴት ሠራተኞች መገልገያ የሚሆኑ እና በተለያየ ቦታ የተገነቡ ጊዜያዊ የመታጠቢያ እና የንፅህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፣

44.2.5. ማንኛውም የሥራ ቦታ ከመንግስት ዋና ምንጭ ወይም በሚመለከተው አካል ፍቃድ ካገኘ ሌላ የተለየ ምንጭ የተገኘ በቂ እና ለጤና ተስማሚ የሆነ የመጠጥ ውሃ ሊኖረው ይገባል፣

44.2.6. በሥራ ቦታዎች የሚገኙ ለእሣት አደጋ እና ለበሽታ የሚያጋልጡ ደረቅ ቆሻሻዎች በወቅቱ መወገድ አለባቸው፣

44.2.7. በግንባታው አካባቢ ብክለት እንዳይከሰት ጊዜያዊ የፍሳሽ ማከማቻ እና ማስወገጃ መዘጋጀት አለበት፣

44.2.8. ህዝብ በሚተላለፍበት መንገድ የሚከማች የግንባታ ቁሳቁስ ከከተማው አስተዳደር ፈቃድ ካልተሠጠ በስተቀር ማከማቸት አይፈቀድም፣

44.2.9. ከሀምሣ እና ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች በሚሠሩባቸው ማናቸውም የሥራ ቦታዎች የደህንነት እና የጤንነት ሁኔታዎችን የሚከታተል የደህንነት መኮንን ሊኖር ይገባል፣ የደህንነት መኮንኑ፣

ሀ) የሥራ ቦታ የደህንነት እና ጤንነት አጠባበቅ የሙያ ሥልጠና የተሰጠው ሊሆን ይገባል፣

ለ) ከሥራ ተቆጣጣሪዎች ጋር በመመካከር በአሠሪው የተቀመጡትን የደህንነት እና ጤንነት ተግባራትን ያከናውናል፣ በሠራተኞች መተግበሩንም ይቆጣጠራል፣

## 45. የሚደርሱ አደጋዎችን ስለ መመዝገብ እና ማሳወቅ

45.1. ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ቦታ ላይ የደረሰበትን አደጋ ወይም የደረሰበትን አደገኛ ሁኔታ ለአሰሪው ወይም ለተቆጣጣሪው ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

45.2. በሥራ ምክንያት የሚደርሱ አደጋዎች እና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎች እንዲሁም አደገኛ ክስተቶች ተመዝግበው ለዚሁ ሥራ በተመደበ ሰው በአግባቡ መያዝ ይኖርባቸዋል፣

45.3. በሥራ ቦታ ላይ ተመዝግበው የተያዙ መረጃዎች ተጠብቀው የሚቆዩበት ጊዜ ቢያንስ ከ10 ዓመት ቢበዛ ደግሞ ከ20 ዓመት መብለጥ የለበትም፣

45.4. ማንኛውም በሥራ ቦታ ላይ የሚደርስ አደጋ በ3 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ አለበት፣ ሪፖርቱ የሚከተሉትን የሚካትት ይሆናል፣

45.4.1. የአደጋውን መፈጠር እና የአደጋውን ባህሪይ ዓይነት፣

45.4.2. አደጋው የደረሰብትን ጊዜ እና ቦታ፣

45.4.3. አደጋው የደረሰበት ሠራተኛ ሙሉ ስም እና አድራሻ፣

45.4.4. የአሠሪው ድርጅት ሙሉ ስም እና አድረሻ፣

45.4.5. ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ የህክምና እርዳት ማግኘት ያለማግኘቱን፣ ካገኘ ሕክምና ያደረገለትን ሐኪም ስምና አድራሻ፣

45.5. አደጋው የሞት አደጋን የሚስከትል ሆኖ ሲገኝ በስልክ ወይም በማናቸውም ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች አደጋው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፣

# አምስት
# የውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን

## 46. የውሃ አቅርቦት

46.1. ማንኛውም ህንጻ ለተገልጋዩ በቂና ንጹህ የውሃ አቅርቦት እንዲኖረው ተደርጎ መሰራት አለበት፣

46.2. በቂ የውሃ አቅርቦት እና ስርጭት ማለት ለእያንዳንዱ ሰው ለመጠጥ፣ ለገላ መታጠቢያ፣ ለልብስ እና መገልገያ እቃዎች ማጠቢያ፣ ለምግብ ማዘጋጃ፣ ለመጸዳጃ ቤት አገልግሎት፣ ለአትክልት ማጠጫ የሚበቃ ሊሆን ይገባል፣

46.3. ለሰዎች አገልግሎት የሚውል የማንኛውም ህንጻ የውሃ አቅርቦት እና ጥራት አገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስታንደርዶች ያሟላ መሆን ይኖርበታል፣

46.4. ለምድብ "ሐ" ህንጻ ተጠቃሚዎች የሚውል የተጠቃሚውን ፍጆታ ሊያሟላ የሚችል የውሃ አቅርቦትና ለመጠባበቂያ የሚውል በቂ የውሃ መከማቻ ሊኖረው ይገባል፣

46.5. ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የሚዘጋጁ የውሃ አቅርቦት መስመሮች ዲዛይኖች እና የመጠቀሚያ ቁሳቁሶች ቁጠባዊ የውሃ አጠቃቀምን መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፣

46.6. የውሃ መጠራቀሚያ ገንዳዎችና የስርጭት መስመሮች ለቁጥጥርና ለጽዳት ተደራሽ ሆነው መገንባት አለባቸው፣

46.7. የውሃ አቅርቦት ሳኒቴሽን የግንባታ እና ስርጭት ዘዴዎች በኢትዮጵያ የህንጻ ኮድ ስታንዳርድ እና በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን መስፈርት ሊከናወን ይገባል፣

## 47. የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ

47.1. አንድ ግንባታ በሚካሄድበት አቅራቢያ የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ካለ የከተማው መስተዳድር ወይም የሚመለከተው አካል በማስፈቀድ የሚገነባውን ሕንጻ የቆሻሻ መስመር ከአካባቢው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጋር መገናኘት ይችላል ፣

47.2. አንድ ግንባታ በአካባቢው የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ከሌለ በግቢ ውስጥ ፍሳሽን ለማስወገድ ተቀባይነት ባለውና የሚመለከታቸውን አካላት መስፈርቶች እንዲያሟላ ተደርጎ መሰራት አለበት፣

47.3. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መሥመር በአዋሳኝ መንገድ ላይ የሚገኝ ከሆነ በአቅራቢያው ባለ ሌላ መንገድ ላይ ከሚገኝ መሥመር ጋር መገናኘት ይችላል፣

47.4. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ገንዳ ፍሳሹን ወደ አፈር ውስጥ እንዳይሰርግ ወይም እንዳያሳልፍ ሆኖ መገንባት አለበት፣

47.5. በአዋሳኝ መንገድ የቆሻሻ ፍሳሽ መሥመር ከሌለ ወይም የቦታ ተፈጥሮአዊ ተዳፋት የህንጻ አቀማመጥ የማይፈቅድ ከሆነ ደረጃውን የጠበቀ የፍሳሽ ማስወገጃ ጉድጓድ /ሲስፑል/ ሴፕቲክ ታንክ የውስጥ ጉድጓድ ገጽ ከማንኛውም ወሰን 150 ሴ.ሜ. ርቆ በይዞታ ውስጥ መገንባት ይችላል። ሆኖም የታችኛውና የላይኛው ሶሌታ አርማታ እንዲሁም ግድግዳው ውሀ የሚያስርግ ሆኖ የተሰራና የመዋቅር ዲዛይኑ ከቀረበና በሚመለከተው አካል ከተፈቀደ ከወሰን እስከ 50 ሳ.ሜ ተጠግቶ መስራት ይቻላል፣

47.6. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ገንዳ ማስተንፈሻ ቱቦ መውጫ ከወሰን በአንድ ሜትር ርቀት መተከል አለበት፣

## 48. የጎርፍ ውሀ ወይም የዝናብ ውሃ አወጋገድ

48.1. ማንኛውም ባለይዞታ በግቢው ውስጥ የሚፈጠርን የዝናብ ውሀ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የጎርፍ ውሀ ማስወገጃ መስመር ማገናኘት አለበት፣

48.2. ለጎርፍ አደጋ በተጋለጡ ቦታዎች የሚከናወን ግንባታ የጎርፍ መከላከያ ያለው ሆኖ መገንባት አለበት፣

48.3. ወሰን ተጠግቶ የሚሰራ ቤት ጣራ ፍሳሽ ወደራስ ይዞታ አቅጣጫ መሆን አለበት፡፡ የጣራውን ፍሳሽ ወደ ወሰንተኛው አቅጣጫ አድርጎ ለመገንባት ማንኛውንም የጣራ ፍሳሽና ጠፈጠፍ እንዲከላከል ተደርጎ ከተሰራ 60 ሳ.ሜ ከፍታ ባለው መሸፈኛ ግድግዳው ተከልሎ መሰራት አለበት፣

48.4. የዝናብ ውሀ አወጋገድ ሥርዓት ውሃው በቀላሉ ሊወገድ በሚችልበትና ውሃ በማያቁርበት ሁኔታ እና የወሰንተኛን ነባር ግንባታ ደህንነት በሚጠብቅ መልኩ መገንባት አለበት፣

48.5. የዝናብ ውሃ ማስወገጃ በአዋሳኝ መንገድ ላይ ከሚገኝ ጎርፍ ማስወገጃ መረብ ጋር መገናኘት አለበት፡፡ ሆኖም ከቦታው ተፈጥሯዊ ተዳፋት አንፃር የሚዘረጉ የፍሳሽ መስመሮች በመዳረሻ መንገድ በኩል ለማውጣት የማይቻል ከሆነ ፍሳሹ ሊሄድ በሚችልበት በኩል ባለ የተጎራባች ይዞታ አሳልፎ ማገናኘት ይቻላል፡፡ ይህም ፍሳሹን ተቀብሎ ላሳለፈው ተጎራባች አመቺ በሆነ አቅጣጫ መሆን ያለበት ሲሆን ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ የማይሄድ ከሆነ ስታንዳርዱን ጠብቆ በአመልካች ወይም አሳላፊው ወጪ ይገነባል፡፡ ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ የሚሄድ ከሆነ እያንዳንዱ ባለይዞታ የየራሱን ወጪ ይሸፍናል፣

48.6. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተጨማሪ ግንባታዎች በማድረግ ተዳፋቱን ወደ ራስ ይዞታ በኩል በመቀየር ወይም በጥልቀት በመቆፈር መስመሩን በራስ ይዞታ ላይ መዘርጋት ካልተቻለ በተጎራባች ይዞታ ማሳለፍ ይቻላል፡፡ ሆኖም በቦታው ልዩ የመሬት አቀማመጥና በአዋሳኝ ካሉት ነባር ግንባታዎች ነባራዊ ይዘት ምክንያት በተናጠል መታየት የሚኖርባቸውን ፍሳሽ መስመር ግንባታ ይዘት እና አቅጣጫ የህንፃ ሹሙ ውሳኔ ይሰጣል፣

48.6.1. ከ50 ሳ.ሜ በታች ሙሌት፣

48.6.2. ከ150 ሳ.ሜ ጥልቀት እና ከ20 ሜትር ርዝመት በታች ቁፋሮ፣

48.7. አንድ ይዞታ ብቻ አቋርጦ ለሚሄድ የዝናብ ውሃ ፍሳሽ መስመር ቢያንስ በ20 ሳ.ሜ የኮንክሪት ቱቦ ወይም ቦይ መሰራት አለበት፡፡ ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ ለሚሄድ የቱቦው መጠን እንደ ርዝመቱ የሚጨምር ይሆናል፡፡ ሆኖም መስመሩ በ2% ተዳፋት፣ በ40 ሳ.ሜ ጥልቀት እና በየ25 ሜትር ርዝመት ወይንም በማንኛውም የመስመር እጥፋት ላይ የመቆጣጠሪያ ገንዳ እንዲኖረው ሆኖ መሰራት አለበት፣

48.8. በተዳፋታማ ቦታ ላይ የሚገኙ ቤቶች የዝናብ ውኃን አንዱ ከሌላው ተቀብሎ የማስተላለፍ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

48.9. በዝናብ ውሃ መስመር ሌላ ቆሻሻ ፍሳሽ መልቀቅ አይፈቀድም፣ ከዝናብ ውሃ ጋር በሚመጣ ቆሻሻ ምክንያት መስመሩን የማጽዳት ሃላፊነት የአሳላፊው ሲሆን ተቀባዩ አሳላፊውን ለዚህ ጉዳይ ወደ ግቢው እንዲገባ የመፍቀድና የመስመሩን ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 49. የኢንዱስትሪ ዝቃጭ

49.1. ማንኛውንም የኢንዱስትሪ ዝቃጭ በቅድሚያ ሳይታከምና ጉጂ አለመሆኑ በሚመለከተው ሳይረጋገጥ ወደ ማንኛውም ፍሳሽ ማስተላለፊያ መለቀቅ የለበትም፣

49.2. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ዝቃጭ የሚያመነጭ ተቋም ወይም ድርጅት አወጋገዱን በተመለከተ ለአካባቢ ባለሥልጣን ወይም ለሚመለከተው አካል ጥናቱን አቅርቦ ፈቀድ ማግኘት ይኖርበታል፣

49.3. የኢንዱስትሪ ዝቃጮችን ለማከምና ወደ ማንኛውም የፍሳሽ ማስወገጃ ለመልቀቅ፣ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፣

49.4. የኢንዱስትሪ ዝቃጮቹ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ መያዝና ጉጂነት ያላቸው ንጥረ ነገሮች ተጣርተው እና ታከመው መለቀቅ ይኖርበታል፣

49.5. ዝቃጭ የሚያመነጩ ተቋማት በከተማው አስተዳደርና በሚመለከተው አካል የአካባቢ ብክለትን እንዳያስከትሉ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፣

## 50. የውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ

50.1. ከከተማው አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል መመሪያና ፈቃድ ውጭ ማንኛውም ሰው ውሃ አልባ ቆሻሻዎችን በየትኛውም ሥፍራና መስመር ማስወገድ ወይም እንዲወገድ ማድረግ የለበትም፤

50.2. የከተማው አስተዳደር ውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎችን የሕዝቡን ጤንነት በጠበቀ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፤

50.3. ኬሚካል ወይም ዝግ ቆሻሻ ማስወገጃ በሚኖርበት ጊዜ ቆሻሻውን ከዕቃው ለማስወገድ በአስተዳደሩ ተቀባይነት ባለው አወጋገድ ዘዴ መከናወን ይኖርበታል፡፡

## 51. የእሳት ማጥፊያ ተከላ

51.1. ለምድብ ለ እና ሐ ሕንፃዎች ለእሳት አደጋ መከላከል የሚረዱ መሣሪያዎች የሚተከሉበትን የሚያሳይ ኘላን መቅረብና በሚመለከተው አካል መፅደቅ ይኖርበታል፣

51.2. የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎች ተከላ በኘላኑና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት መከናወንና በተከላ ወቅትም ክትትል ሊደረግበት ይገባል፣

51.3. የመሣሪያዎቹ ተከላ እንደተጠናቀቀ ፍተሻ መደረግና መስራታቸው በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፣

51.4. የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎቹ የጥራት ደረጃ በሚመለከተው አካል ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፣

51.5. በውኃ ለሚሠሩ የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎች የውኃ ማከማቻ ሊኖራቸው ይገባል፣

51.6. የውኃ መስመር ደረጃውን በጠበቀ የውኃ ማስተላለፊያ ቧንቧ መዘርጋት ይኖርበታል፣

51.7. የውኃ ማጠራቀሚያ ጋኑም ሆነ መስመሮቹ ለቁጥጥር የሚያመቹ መሆን አለበት፣

## 52. የእሣት መከላከል የውሃ አቅርቦት

52.1. የእሣት መከላከያ የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ በቅድሚያ ለከተማው አስተዳደር በማመልከቻ መጠየቅ አለበት፣

52.2. የከተማው አስተዳደር የእሣት አደጋ መከላከያ እስኪደርስ ድረስ ለትላልቅና ለምድብ "ሐ" ህንፃዎች መጠባበቂያ የሚሆን ከተገቢው መሣሪያ ጋር የውሃ አቅርቦት ሊኖር ይገባል፣

52.3. የተቋሞች ወይም ድርጅቶች የእሣት መከላከያ መሣሪያውና የውሃው አጠቃቀም ከከተማው አስተዳደር የእሣት አደጋ መከላከያ መስፈርቶችና ሕጐች ጋር የተጣጣመ መሆን ይገባዋል፣

52.4. የከተማው አስተዳዳር እሣት ለመከላል የሚቀርበውን የውሃ አቅርቦት ጥያቄ እንደ ህንፃው ዓይነት፣ ከፍታው የሕንፃው ስፋት መሠረት የውሃ አቅረቦትን ሊወስን ይችላል፤

## 53. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን መመሪያ በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

53.1. በአገር አቀፍ የሚሰራባቸው ልዩ ልዩ ኮዶችን ያዘጋጃል፣

53.2. ለየሕንፃ ምድቦቹ የሚያገለግሉ የዲዛይን እና የኮንስትራክሽን ስታንዳርዶችን፣ የዲዛይን፣ የኮንስትራክሽን እና የቁጥጥር ዘዴ መመሪያዎች ሞዴል ለክልሎች ያዘጋጃል፣

53.3. መመሪያው በክልሎችና በከተሞች ተከብሮ መፈጸሙን ይቆጣጠራል፣

53.4. ከሌሎች አግባብ ካላቸው የፌዴራል መንግሥቱ አካላት በጋር በመቀናጀት ክልሎችና ከተሞች መመሪያውን ለማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣

## 54. መመሪያውን ስለማሻሻል

54.1. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መመሪያውን ያሻሽላል፡፡

## 55. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከግንቦት 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት 2003 ዓ.ም

መኩሪያ ኃይሌ
የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
ሚኒስትር

1. የግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ……………………………………………..ቅፅ 001
2. የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት……………………..……………………….ቅፅ 002
3. የፕላን ስምምነት መጠየቂያ ማመልከቻ…………………………………..…..ቅፅ 003
4. የግንባታ እርከን ማሳወቂያ …………………………………………………………..ቅፅ 004
5. የግንባታ እድሳት ፈቃድ መጠየቂያ……………………………………………….ቅፅ 005
6. የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ……………………………………………………………..ቅፅ 006
7. የአገልግሎት ለውጥ መጠየቂያ ማመልከቻ ………………………………… ………..ቅፅ 007
8. የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ………………………………………..……………..ቅፅ 008
9. የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ ……………………………………..……………..ቅፅ 009
10. የአማካሪ ግዴታ መግቢያ ………………………………………………..…………..ቅፅ 010
11. የአሠሪ ግዴታ መግቢያ……………………………………………………………….ቅፅ 011
12. የገንቢ ግዴታ መግቢያ ……………………………………………………..………..ቅፅ 012
13. የግንባታ መከታተያ ቅጽ……………………………………………………..……..ቅፅ 013
14. የግንባታ ማስቆሚያ ማስጠንቀቂያ ………………………………………………..ቅፅ 014
15. የግንባታ ማስቆሚያ ……………………………………………………..…………..ቅፅ 015
16. የግንባታ ክትትል ውሳኔ መግለጫ …………………………………………………..ቅፅ 016
17. የግንባታ ሥራ ለውጥ ተጨማሪ ማሳወቂያ………………………………………….ቅፅ 017
18. የግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ መጠየቂያ……………………………………………..ቅፅ 018
19. የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ……………………………………………………………..ቅፅ 019
20. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ………………………………………………..…………..ቅፅ 020
21. የቅጣት ውሳኔ ማሳወቂያ /ደንብ ማስከበር/……………………………………..ቅፅ 021
22. የፕላን ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረቢያ……………………………………..…………..ቅፅ 022
23. የግንባታ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ…………………………………………….ቅፅ 023
24. ለፕላን ግምገማ ተጨማሪ ጊዜ መጠየቂያ …………………………………………..ቅፅ 024
25. የግንባታ ሥራ እርከን ማሳወቂያ………………………………………………..…..ቅፅ 025
26. አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ መጠየቂያ …………………………………....ቅፅ 026
27. ይግባኝ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ማሳወቂያ ……………………………………………..ቅፅ 027
28. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ……………………………………..ቅፅ 028
29. የምሽት መገንቢያ ፍቃድ………………………………………………………..ቅፅ 029

ሴሪ ቁጥር -------------
ቅጽ 001

አርማ

የ ........................................... ክልል

የ.......................................... ከተማ አስተዳደር

# የግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ

## በአመልካች የሚሞላ

1. ግንባታው የሚካሄድበት አድራሻ

ከተማ ................................ ክፍለ ከተማ ................................ ወረዳ/ቀበሌ ................................

ልዩ መጠሪያ/መንገድ ..................................... የቤት ቁጥር ------------------ የኘሎት ቁጥር --------------

2. የግንባታ ፈቃድ የተጠየቀበት የግንባታ አገልግሎት

የግል መኖሪያ ☐ ሱቅ ☐ ቢሮ ☐ ሆቴል ☐ ማምረቻ ☐

አፓርታማ ☐ መጋዘን ☐ የጤና ተቋም ☐ የትምህርት ተቋም ☐

የመሠረተ ልማት ዓይነት ☐ ሌሎች ☐

3. የግንባታ ዓይነት

አዲስ ግንባታ ☐ ማሻሻያ/ማስፋፊያ ☐ የግንባታ ፈቃድ ማራዘሚያ ☐

ነባር ከሆነ የቀድሞው የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ ፈቃድ የወጣበት ቀን ☐

የግንባታው ወጪ ☐ የወለል ብዛት ☐

ከመሬት በላይ ያለው ከፍታ በሜትር ☐ ከምድር በታች የወለል ብዛት ☐

ከምድር በታች ያለው ጥልቀት በሜትር ☐

**የወሰን ላይ የግንባታ ይዘት ዝርዝር መግለጫ**

…………………………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………………………..

…………………………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………………………..

4. **የአማካሪው ድርጅት**

| ሥም | | ደረጃ | | አድራሻ | | ስ.ቁ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|

የዲዛይኑ ዝርዝር መግለጫ

**ለግንባታ ፈቃድ የቀረበ የዲዛይን ዓይነት**

| የዲዛይኑ ዓይነት | ዲዛይኑን ያዘጋጀው ባለሙያ ስም | የባለሙያው የምዝገባ ቁጥር | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| አርክቴክቸራል | | | |
| ስትራክቸራል | | | |
| ኤሌትሪካል | | | |
| ሳኒታሪ | | | |
| ሜካኒካል | | | |

5. እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ከዚህ በላይ የተጠየቀውን መረጃ አንብቤና አገናዝቤ የሰጠሁት መረጃ እውነት እና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ብሰጥ እና በዚህም ምክንያት ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ ኢንዲሁም በዚህ ማመልከቻ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውም የፕላን ስምምነት እና የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የግንባታ ፈቃዱ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ፡፡

| የግንባታ ፈቃድ ጠያቂው ስም | | ስልክ ቁጥር | |
|---|---|---|---|
| የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር | | ፊርማ | |
| ቀን | | | |

## 7. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ

**ለምርመራ የቀረበ ሠነድ (የ× ምልክት ያድርጉ)**

| የህንፃ ምድብ | ሀ | | ለ | | ሐ | |
|---|---|---|---|---|---|---|

የፕላን መረጃ [ ] ገጽ ኤሌትሪካል [ ] ገጽ የወሰን ስምምነት መረጃ [ ] ገጽ

አርክቴክቸራል [ ] ገጽ ሳኒታሪ [ ] ገጽ የባለሙያ ግዴታ [ ] ገጽ

ስትራክቸራል [ ] ገጽ ሜካኒካል [ ] ገጽ የሊዝ/ይዞታ ውል [ ] ገጽ

ስታቲካል ካልኩሌሽንና
የአፈር ምርመራ /ጥራዝ/ [ ] ጥቅል ግምት [ ] ሌላ/ዓይነቱ ይገለጽ [ ]

የመዳረሻ መንገድ [ ] የይዞታው ስፋት [ ]

የቀረበው ሠነድ ለግንባታ ፈቃድ የተሟላ ነው [ ] አይደለም [ ]

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር [ ] የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ቁ. [ ]

ፈቃዱን መቀበያ ቀጠሮ 1 [ ] 2 [ ]

መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም [ ] ፊርማ [ ]

ቀን [ ] ሰዓት [ ]

**ማሳሰቢያ፣ ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር /ፋይል ጋር ይያያዛል፡**

ሴሪ ቁጥር ------------
ቅጽ 002

አርማ

የ ........................................ ክልል

የ......................................... ከተማ አስተዳደር

# የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት

1. የባለይዞታው ስም [ ] የካርታ ቁ. [ ]

አድራሻ ክ.ከ [ ] ወረዳ/ቀበሌ [ ] ስልክ ቁ. [ ]

የግብር ከፋይ መለያ ቁ. [ ]

2. ግንባታው የሚገኝበት

አድራሻ ክ.ከ [ ] ወረዳ/ቀበሌ [ ] ብሎክ ቁ. [ ]

ፕሎት ቁ. [ ] የቤት ቁ. [ ] የካዳስተር ቁ. [ ]

የመንገድ/ጎዳና ስም [ ]

3. የግንባታው አገልግሎት [ ]

4. የወለል ብዛት [ ] ከመሬት በላይ [ ] ከመሬት በታች [ ]

5. የግንባታው ወጪ [ ]

6. የተሰጠበት ቀን [ ]

7. የግንባታው ዓይነት አዲስ [ ] ማሻሻያ [ ] የአገልግሎት ለውጥ [ ]

8. የግንባታ ፈቃድ ውሳኔ

..........................................................................................................................

..........................................................................................................................

..........................................................................................................................

..........................................................................................................................

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለተገለፀው ግንባታ የቀረበው ሠነድ ተመርምሮ ግንባታው እንዲካሄድ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ተፈቅዷል | | አልተፈቀደም | |

9. ያልተፈቀደበት ምክንያት

…………………………………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………………………………..

………………………………………………………………………………………………………………………

10. የግንባታ ምስክር ወረቀት አካል የሆኑ አባሪ ሠነዶች

አርክቴክቸራል ☐ ገጽ ስትራክቸራል ☐ ገጽ ኤሌክትሪካል ☐ ገጽ ሳኒታሪ ☐ ገጽ

መካኒካል ☐ ገጽ የባለሙያ ግዴታ ቅጽ ☐ ገጽ የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ ☐ ገጽ

የቀድሞ ግንባታ ፈቃድ ቁ. (ነባር ግንባታ ከሆነ) ☐ የዚህ ፈቃድ አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁ. ☐ ፈቃድ የተሰጠበት ቀን ☐

| የግንባታ ፈቃድ መርማሪ ባለሙያ | የግንባታ ፈቃዱን ያፀደቀው ሃላፊ |
|---|---|
| ስም ………………………………………………. | ስም ……………………………………………… |
| ፊርማ …………………………………………….. | ፊርማ …………………………………………… |
| ቀን ………………………………………………… | ቀን …………………………………………… |

<u>ማሳሰቢያ</u>

1. ይህ ቅጽ በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ ‹‹ተፈቅዷል›› እና ‹‹ለክትትል›› ከሚሉ ሁለት የዲዛይን ሠነድ ኮፒዎች ጋር ለግንባታው ባለቤት የሚሰጥ ሲሆን አንድ ኮፒ ከፋይል ጋር የሚያያዝ ይሆናል፡፡
2. ይህ ቅጽ በሃላፊ ተፈርሞ በመ/ቤቱ ማህተም ካልተረጋገጠ ዋጋ አይኖረውም፡፡

3 በዚህ ይዞታ ላይ ከዚህ በፊት ወጪ የተደረገ የግንባታ ፈቃድ በዚህ ተተክቷል፡፡

ሴሪ ቁጥር -------------
ቅጽ 003

አርማ

የ........................................ ክልል

የ........................................ ከተማ አስተዳደር

# የፕላን ስምምነት መጠየቂያ ማመልከቻ

## በአመልካች የሚሞላ

1. ግንባታው የሚካሄድበት አድራሻ

ከተማ ................ ክፍለ ከተማ ---------------- ወረዳ/ቀበሌ ...............

ልዩ መጠሪያ/መንገድ ...................... የቤት ቁጥር ................. ኘሎት ቁጥር -------------------------

2. የፕላን ስምምነቱ የተጠየቀበት የግንባታ አገልግሎት

የግል መኖሪያ ☐ ሱቅ ☐ ቢሮ ☐ ሆቴል ☐ ማምረቻ ☐

አፓርታማ ☐ መጋዘን ☐ የጤና ተቋም ☐ የትምህርት ተቋም ☐

ሌሎች ☐

የህንፃው ከፍታ ከመሬት በላይ በሜትር ☐ ከመሬት በታች በሜትር ☐

የወለል ብዛት ከመሬት በላይ ☐ ከመሬት በታች ☐

3. የፕላን ስምምነት የተጠየቀበት የግንባታ ዓይነት

አዲስ ግንባታ ☐ ማሻሻያ/ማስፋፊያ ☐ የአገልግሎት ለውጥ ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ የግንባታ ፈቃድ የወጣበት ቀን ☐ የግንባታው ወጪ ☐

4. የፕላን ስምምነት የተጠየቀበት ግንባታ አዲስ ከሆነ

ሙሉ ለሙሉ በአንዴ የሚገነባ ☐ ደረጃ በደረጃ የሚገነባ ☐

የይዞታ ማረጋገጫ ሠነድ ቁጥር ☐

5. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ

**ለምርመራ የቀረበ ሠነድ**

የግንባታው አድራሻ

መረጃ ብሎክ ቁ. [ ] ፓርሴል ቁ. [ ] X [ ] Y [ ]

የመሬ ፕላን መስፈርት መረጃ [ ]

ይዞታው የሚገኝበት መደብ [ ]

ለይዞታው የተመደበ የመሬት አጠቃቀም [ ] ማህበራዊና ማዘጋጃ ቤታዊ [ ] ቅይጥ [ ]

አረንጓዴ ለባሽ [ ] ማዕከል [ ] ማምረቻና ማከማቻ [ ] መናሃሪያ [ ] ለመጠባበቂያ [ ]

ሌላ [ ] የህንፃ ከፍታ [ ] አነስተኛው [G+ ]

ከፍተኛው [G+ ] ጣሪያ ከፍታው በሜትር [ ] የግንባታው ይዞት ንፅፅር [ % ]

የመዳረሻ መንገድ ደረጃ [ ]

በይዞታው ላይ ወይም አጠገብ የተዘረጋ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት አውታር መረጃ

የውሃ መስመር [ ] የፍሳሽ ማስወገጃ [ ] የኤሌክትሪክ መስመር [ ] የቴሌ መስመር [ ]

ተጨማሪ መግለጫ [ ]

የፕላን መረጃ ቁ. [ ] ቀን [ ]

መረጃውን የሰጠው ባለሙያ ስም [ ] ፊርማ [ ]

ያፀደቀው `ላፊ

ስም [ ] ፊርማ [ ]

6. እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የፕላን ስምምነት ጠያቂ ከዚህ በላይ የተጠየቀውን መረጃ አንብቤና አገናዝቤ የሰጠሁት መረጃ እውነት እና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ብሰጥ እና በዚህም ምክንያት ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ ኢንዲሁም በዚህ ማመልከቻ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውም የፕላን ስምምነት እና የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የፕላን ስምምነቱ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ፡፡

የፕላን ስምምነት ጠያቂው ስም [ ] ስልክ ቁጥር [ ]

ሞባይል [ ] የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/ካለ [ ]

ፊርማ [ ]

__ማሳሰቢያ__.ይህ መረጃ እንደይዞታ ማረጋገጫነት አያገለግልም 2. ለፍቃድ የሚቀርብ ዲዛይን በዚህ መረጃ መሠረት መሆን አለበት 3. ይህን መረጃ አግባብና ህጋዊ ለሆነ አገልግሎት የመጠቀም ሃላፊነት የፕላን መረጃ ጠያቂው ነው ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር /ፋይል ጋር ይያያዛል፡

ሴሪ ቁጥር ------------
ቅጽ 004

አርማ

የ.......................................... ክልል

የ.......................................... ከተማ አስተዳደር

# የግንባታ እርከን ማሳወቂያ

1. አድራሻ

የባለቤት ሥም ____ ክ/ከ ____ ወረዳ/ቀበሌ ____

የኘሎት ቁጥር ____

የቤት ቁ. ____ የግንባታው አገልግሎት ____ የሕንፃ ምድብ ____

የግንባታ ፈቃድ ቁ. ____ የወለል ብዛት ____ ከመሬት በላይ ____ ከመሬት በታች ____

የግንባታው ጥቅል ግምት ____ ግብር ከፋይ መ.ቁ ____

የሥራ ተቋራጭ ____ ደረጃ ____ ተቆጣጣሪ ____

የምዝገባ ቁ. ____ አማካሪ ____ ዘርፍና ደረጃ ____

2. ግንባታው ያለበት ደረጃ /የሥራ እርከን

